# የህወሓት ታሪክ እና የተኮላሸው አላማው



አቶ አስገደ ገ/ስላሴ

ከዛሬ 37 ዓመት በፊት ትግራይን ጨምሮ መላው ኢትዮጵያ በድቅድቅ ጨለማ ስለመዋጧ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የባነነበት ዘመን ነበር። ያ ዘመን። እናም ከእለታት አንድ ቀን ከህወሓት መስራች አንዱ፣ የአካባቢዬ ሰው አቶ አየለ ገሠሠ (የበረሀ ስማቸው ስሁል ይባላል) የፖለቲካ ትግል ስለማድረግ አነጋገሩኝ። አዲስ አበባ ከሚገኙ ጥቂት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም ጋር በጉዳዩ ላይ እንደተነጋገሩና ድርጅት መስርቶ መታገሉ አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘባቸውንም ጨምረው ነገሩኝ። አቶ አየለ ገሠሠ-ስሁል። በዚህም የታሪክ አጋጣሚ ነው የህወሓት መስራች ከሆኑት ውስጥ አንዱ ልሆን የቻልኩት።

በእለተ ሀሙስ 1967ዓ.ም የካቲት 11 ቀን 11 የህወሓት መስራቾች ከምሽቱ ሶስት ስአት ጉዞ ጀመርን። ከሽሬ ተነስተን ወደ ደደቢት በረሀ። ያንን የዴሞክራሲ እና የነፃነት ጉዞ በምሽት የጀመርንበት ምክንያት ከመነሻችን ሽሬ ከተማ ጀምሮ በርካታ መንደሮችን ማቋረጥ ስለነበረብን ከእይታ ለመከለል ነው።

እናም በጨለማ ተጓዝን፤ ለአራት ሰዓት ያህል ተጉዘን ከለሊቱ ስምንት ሰዓት ላይ መንደሮችን ጨርሰን ወጣን። ‹‹ማይቂል›› ጫካ ደረስን። ከሽሬ በተነሳን በ3ኛው ቀንም ህዝባዊ አብዮት ያቀጣጠልንበት ታሪካዊው ደደቢት በረሃ ገባን።

አቤት! ጊዜው እንዴት ይሮጣል? መቼም ያ እለት ከነገ ወዲያ 37 አመት የሚሞላው ቢሆንም እንኳ እያንዳንዱ ትዕይንት በአይነ ህሊናዬ ይታየኛል። አንዳች የዘነጋሁት የለም።

አስራ አንዳችን ማን ማን ነበርን? … እኔ ፣ ስሁል ገሠሠ፣ አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘረአፅዮን፣ ስዩም መስፍን፣ ቀለበት ታዬ፣ ፀሐዬ አረፋይኔ፣ አግአዚ ገሠሠ፣ አብተው ታከለ፣ ሙሉጌታ ሀጎስ እና አምባዬ ወ/ጊዮርጊስ (ከአረጋዊ በስተቀር የሁላችንም ስም የበረሃ ስም ነው) ስንሆን፤ የታጠቅነው መሳሪያ አንድ ሳንጃ አልቤን፣ አንድ ካርባይን፣ አንድ ቶምሶን፣ አንድ ምንሽር፣ አንድ ጓንዴና አንድ ሽጉጥ በአቃላይ 6 አሮጌ መሳሪያዎች ብቻ ናቸው። አሁን በነዚህ አሮጌ መሳሪያ እስከአፍንጫው የታጠቀው የወታደር መንግስት ይንበረከካል? እስቲ እንየዋ!

የትግሉ አላማ

እኔ የአፄ ኃ/ሥላሴ የኮማንዶ ወታደር አባል ስሆን፣ የያዝኩትም የራሴን ጠመንጃ ነው። እንግዲህ በትግራይ ምድር የፖለቲካ ትግል ለመጀመር ውስጥ ውስጡን ሀሳብ የነበረው በአፄው መውደቂያ ዋዜማ አካባቢ ነበረ። ነገር ግን የአፄው መንግስት ወድቆ ደርግ ሲተካ ገና ከጠዋቱ የደርግ ፋሽስታዊ ባህሪ ጎልቶ ወጣ። ይህን ጊዜም ከደርግ ጋር በሰላማዊ መንገድ መታገል እንደማይቻል ግልፅ ሆነ። መፍትሄውም ብረት ብቻ እንደሆነ ገባን። ብረትም አነሳን።

በወቅቱ የተፃፈ ህገ ደንብም ሆነ የፖለቲካ ፕሮግራም ባይኖረንም እያንዳንዳችን ለህዝባችን ልማት ፍትህ እና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መታገል እንዳለብን ተግባብተናል። ይሄ ግን ብዙ አልዘለቀም። ከሽሬ የተነሳነው አስራ አንዳችንን ጨምሮ፣ ለስልጠና ወደ ኤርትራ የተላኩት ሰባቱ መስራች አባላት ስልጠናቸውን በሰኔ ወር 1967 ጨርሰው ከመጡ በኋላ አዲስ የፖለቲካ አመለከካከት ተከሰተ። በደደቢት በረሀ።

ይሄውም የተነሳንለት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት፣ ልማት እና ፍትህ ቀርቶ፣ ‹‹ከአማራ የጭቆና ቀኝ አገዛዝ ነፃ በመውጣት፣ የትግራይ ሪፖብሊክን መመስረት›› በሚል የተወሰኑ የተማሪ ታጋዮች ያነሱት ሀሳብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ጫና ፈጥረው በማሸነፋቸው፣ ለአንድ አመት ያህል በዚህ መንፈስ እንድንቆይ አደረጉ። ከዚህም በተጨማሪ በአይዶሎጂ ደረጃ እንከተል የነበረው (ገዥ ሀሳብ) ኮሚኒዝም ሆነ። ማርክሲዝም፣ ሌኒንዝም መመሪያችን ነው እስከ ማለትም ተደረሰ።

በዚህ አይነት ሁኔታም በርካታ ህዝብ በየቀኑ እና በየሰዓቱ ከየአካባቢው እየጎረፈ የህወሓት አቅምን አፈረጠመው። ከደፈጣ አደጋ መጣል ወደ ሽምቅ ውጊያ፤ ከሽምቅ ውጊያ ወደ መደበኛ ጦርነት የሚረማመድ ሀይል ገነባን። ሠራዊታችንም ከሀይል ወደ ብርጌድ፣ ወደ ክፍለ ጦር እያለ በፈጣን ሁኔታ አደገ።

እኔ ህወሓትን ከመሰረትነው ሰዎች የምለይበት ምክንያት አለ። ይኸውም የአፄ ኃ/ሥላሴ የኮማንዶ ጦር አባል በመሆኔ፣ ከሌሎች የመስራች አባላት የበለጠ እና የላቀ ወታደራዊ ሳይንስ ግንዛቤ ነበረኝ። ስለዚህም ወደኤርትራ ከተላኩት ሰባቱ ታጋዮች ውጪ ሁሉንም የህወሓት ታጋይ አሰልጥኛለሁ። ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና ስዩም መስፍንን ጨምሮ ሁሉም በእኔ ነው የሰለጠኑት። ኋላም የታጋዩ ቁጥር እየበዛ ሲሄድ የእኔ ድርሻ አሰልጣኞችን ማሰልጠን እንዲሆን ተደረገና የህወሓትን የጦርም ሆነ የፖለቲካ መሪዎችን አሰልጥኛለሁ። ከትግሉ በፊት በኢትዮጵያ ሰራዊት ውስጥ የጤና መኮንን በመሆኔም ህወሓትን በሀኪምነት አገልግያለሁ።

ደስታ እና ሀዘን

እንደሚታወቀው ፋሽስታዊው ደርግን ለመጣል የአደረግነው ትግል መራራ እና ከባድ ከመሆኑም አኳያ ብዙ መስዋትነትንም ጠይቋል። ስለዚህም ነው፤ ደርግን መጣላችን አንዱ ትልቅ ታሪካችን ሊሆን የበቃው። ይህ ማለት ግን የመጨረሻ እቅዳችን ደርግን መጣል ብቻ ነበር ማለት አይደለም። ከደርቅ ውድቀት በኋላ ለመላው ኢትዮጵያውያን አዲስ ቀን ሊያመጣ የሚችል ተሻገሪ እቅዶችም ነበሩን። በነበር ቀሩ እንጂ። ሆኖም ደርግ ከወደቀ በኋላ ጥቂት የዴሞክራሲ መገለጫ የሚመስሉ ነገሮች መኖራቸው በራሱ አበረታች ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በመጨረሻ የተከሰተው ግን ሁላችንንም አንገት ያስደፋ ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ ለሰማዕታት ጓዶቻችን የህሊና ወቀሳ የሚዳርግ ነው። ምክንያቱም የብዙ ኢትዮጵያውያኖች ደም የፈሰሰበት፣ አጥንት የተከሰከሰበት ያ ታላቅ ትግል ሕወሓት ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ እንዲኮላሽ ተደርጓልና።

በእርግጥ ዛሬ እንደ ደርግ ዘመን ሰዎች በየጎዳናው አይረሸኑም፣ መንደሮችም አይቃጠሉም። ነገር ግን የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ እና አፈናው ከደርግ ዘመን ጋር ተመሳሳይ ነው። የሰው ልጅ በቁሙ ህሊናውን እንዲሸጥ ተደርጓል። ስለዚህም ያ ሁሉ መስዋዕትነት ከተከፈለ በኋላ በአለፉት 37 አመታት ውስጥ ህዝቡ ያተረፈው ይህንን ነው። ይሄ ለህወሓት-ኢህአዴግም ታላቅ ውድቀት ነው። እናም የህወሓት-ኢህአዴግ መንግስት ኢትዮጵያውያኖችን ለሌላ ትግል፣ ለሌላ መስዕዋትነት እንዲነሱ የገፋፋ እና እየገፋፋ ያለ ነው። የሞትንለት፣ የቆሰልንለት፣ የተራብንለት፣ የተጠማንለት፣ በዱር በገድል የተሠቃየንለት፣ በቤተሰብ ናፍቆት እየተቃጠልን ተራራን የወጣንበት፣ የወረድንበት ትግል እንዲህ የጥቂት ሰዎች የግል ሀብት እና እርስት ከመሆንም አልፎ የጣልነውን መንግስት ባህሪ መደገሙን ስመለከት ሀዘኔ ይበረታል።

በትግሉ ዘመን እና ዛሬ-የትግራይ ህዝብ

በትግራይ የነበረው የህወሓት አሰላለፍ በጣም የሚደንቅ ብቻ ሳይሆን ፍፁም ስህተት ነው። ምክንያቱም ህወሓት ገና ተመስርቶ ትግል እንደተጀመረ ህብረተሰቡን ከፍሎ ነበር የሚመለከተው። እናም ሀብታም ገበሬ፣ ሀብታም ነጋዴ እና ከፍተኛ ምሁራንን እንደ ጠላት፣ እንደኢምፔሪያሊስት፣ እንድአቆርቋዥ ተደርገው ሲወሰዱ፤ ደሀ ገበሬ፣ ዝቅተኛ ነጋዴ፣ የታችኛው ምሁር እና የግራ ዘመም ተከታዮች ደግሞ እንደ ወዳጅ የሚታይ በመሆኑ ትግሉ እስኪጠናቀቅ ድረስም ደጋፊ ሆኖ ከፍተኛ አስተዋፆ ያበረከተው ይህኛው መደብ ነው። ስለዚህም ህወሓት እንኳን ዛሬ ያኔ በትግሉ ዘመንም በትግራይ ደጋፊም ተቃዋሚ ነበረው ማለት ነው።

የሆነ ሆኖ ህወሓት ዛሬም ቢሆን በምሁራን ላይ ያለው ጥላቻ አልተቀየረም። ምሁራንና የሚያየው እንደ ጥገኛ እንጂ እንደ ሞያተኛ እና መሪ ሀሳብ እንዳለው አጋዥ አድርጎ አይደለም። ባለሀብቱም ቢሆን ታዛዥ እና የህወሓት ጥገኛ ካልሆነ በቀር እንደ ዜጋ የሚታይበት ሁኔታ የለም።

ያ ህወሓትን ከልጆቹ ጉሮሮ እየነጠቀ ሳይቀር ይቀልበው የነበረ፤ ልጆቹን መርቆ ይልክ የነበረ፤ የህወሓት ታጋዮች ሲዋጉ ከደረሰ አብሮ ይዋጋ የነበረው ደሀ ገበሬም ቢሆን ከህወሓት የጠበቀው ይህን ስላልነበረ በህወሓት እያዘነ ነው ያለው። የገበሬው ችግር ሰርቶ መብላት እና ጠግቦ ማደር አለመቻሉ ብቻ አይደለም፤ ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ ባለመጠበቃቸውም ከፍተኛ ቅሬታ አድሮበታል። እናም በአሁኑ ወቅት በትግራይ ያለውን ሁኔታ ስገመግመው በህወሓት ከሚደሰተው ይልቅ የተከፋው ህዝብ ቁጥር በእጅጉ እንደሚበልጥ ነው።

በትግሉ ዘመን የተደሰትኩበት ቀን ቢኖርም ያዘንኩበት ቀን ይበልጣል። እንደማስታውሰው የመጀመሪያው እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የህወሓት ሰዎችንም የሚያሳዝን ክስተት የተከሰተው፣ ህወሓት ለዴሞክራሲ ከሚታገሉ እንደኢህአፓ ካሉ ድርጅቶች ጋር ያደረገው አላስፈላጊ ጦርነት ነው። በዚህ ጦርነትም ብዙ አላስፈላጊ መስዕዋትነት ተከፍሎአል፤ ንብረት ወድሞአል። ሌላው በጣም አሳዛኝ ነው የምለው ህወሓት ግንባረ ገድሊ ሓርነት ትግራይ የተባለ ድርጅት ላይ የፈፀመው አስከፊ ወንጀል ነው። ነገሩም እንዲህ ነው።

የህወሓት አመራር፣ ይህንን ድርጅት አብረን እንታገል፤ አንድነት እንፍጠር ብሎ ለስብሰባ ይጠራዋል። ከዛም ስብሰባው ተካሄደ። ቀኑም መሸ። የሁለቱም ድርጅቶች አመራሮች አብረው አደሩ። ነገር ግን የህወሓት አመራር ሌሊት ላይ የግንባረ ገድለ ሓርነት አመራርን በጥይት ደብድቦ ፈጃቸው። ለወሬ ነጋሪ እንኳ ሳይተርፉ በሙሉ አለቁ። እንግዲህ ለዜጎች ነፃነት እታገላለሁ የሚል ድርጅት የዴሞክራሲ ድርጅቶች እንዳይኖሩ ማድረጉ በጣም አሳዛኝ ነገር ነው።

በእርግጥ አሁን ያለውም ልዩነትን አለመቀበል፣ አለመቻል፣ አለመሸከም ዛሬ የጀመረ አይደለም። ይልቁንም ከ1967 ጀምሮ እንደ ባህል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ተደስትኩ የምልበት እና እንደልዩ ቀኔ የማየው 604ኛ ኮርን ሽሬ ላይ ያሸነፍንበትን ቀን ነው። ምክንያቱም ከሽሬ ሽንፈት በኋላ ደርግ ሙሉ በሙሉ ከትግራይ ለቀቀ። እናም ደርግ በኢትዮጵያ ደረጃ ሙሉ በሙሉ እንደሚሸነፍ እርግጠኛ የሆንኩበት ቀን ስለሆነ ነው ከልብ የተደሰትኩበት ቀን የሆነው-ይህ ቀን።

የዘንድሮው በዓል

እኔ ከ1987ዓ.ም ጀምሮ የህወሓትን የልደት ቀን ከህወሓት ሰዎች ጋር አክብሬ አላውቅም። በቤቴ ግን ፍስክ ከሆነ የፍስክ ምግብ፣ ፆም ከሆነ የፆም ምግብ አሰናድቼ ቀኑን ሳላከብር ቀርቼ አላውቅም። ለምንድን ነው የማከብረው? የሚለውንም ማስረዳት አለብኝ። አዎን! የህወሓት አላማ ተኮላሽቷል። ዛሬ ያ ሁሉ ሰው የተዋደቀለት አላማ በመጠለፉ የሚያዝኑ ሰዎች የህወሓትን የምስረታ በዐል ማክበራቸው ግራ ያጋባ ይሆናል። ነገር ግን ብዙ ሺ ኢትዮጵያዊያን የስርዓት ለውጥ ለማምጣት የከፈሉት መስዕዋትነት ስላለ ነው እኔ በአሉን የማከብረው። ሳከብረውም ይህኛውን ህወሓት እያሰብኩ አይደለም። መጀመሪያ የመሰረትነውን ህወሓት ልደት ነው እንጂ። ለወደፊቱም አከብረዋል።

አሁን እያከበርን ነው የሚሉት የህወሓት ሰዎች በእውነቱ ያስቃሉ። አንደኛ ሲጀመርም አብዛኛው በአሉ የሚመለከታቸው አይደሉም። አርቴፊሻል ነው። ለነገሩ እነሱም ቢሆኑ ከልባቸው ሳይሆን፣ ለህዝብ ግንኙነት ስራ ሲሉ ነው እያከበሩ ያሉት።

ለምሳሌ የህወሓት ልደት በትግራይ ሲከበር፣ ልጆቻቸው ተሰውተውባቸው፣ ጧሪ ቀባሪ አጥተው ለልመና የወጡ አረጋውያንም ሆኑ በትግሉ የተጎዱ አካል ጉዳተኞች ተሳታፊ አይደሉም። ቢያንስ በዚህ ቀን እንኳ እነዚህን ሰዎች አስበው ሌላ አይደለም ጠግበው እንዲበሉ አይጋብዟቸውም። በግልባጩ ለራሳቸው ብቻ ብሎ ሌብል፣ ሬድ ሌብል፣ ቺቫዝ… አማርጠው እየጠጡ፣ ሰንጋ ጥለው ጮማ እየቆረጡ ነው የሚያከብሩት። ብላ ጠጣ፣ ፍሰስ ተፋስስ ነው።

ይህ ደግሞ የአጭበርባሪዎች፣ የሙሰኞች እና የአምባገነኖች የበዓል አከባበር ፈሊጥ ነው። ስለዚህም ነው እኔ በቤቴ ከልጆቼ እና የተወሰኑ ሰዎችን ጠርቼ የማከብረው።

የተሰዉ ታጋዮች ብዛት

ህወሓት ከ50-60 ሺህ ሰው ተሰውቶብኛል ይላል። እኔ በዚህ አሀዝ አልስማማም። ምክንያቱም በእኔ እምነት ከህወሓት ውስጥ ከዚህ ቁጥር በላይ ነው የተሰዋው። እንግዲህ በህወሓት የትግል ታሪክ በአጠቃላይ 386 ሺ ታጋዮች ታግለዋል። በሚሊሻ ደረጃ የነበሩት ደግሞ ከ300 ሺህ በላይ ናቸው። የገጠር ካድሬዎቻችንም በ10 ሺህ የሚቆጠሩ ነበሩ። እንግዲህ በእነዚህ ሶስት ሀይላት (በታጋይነት፣ በሚሊሻነት እና በገጠር ካድሬነት) ከተሰለፈው ውስጥ ቢያንስ ከ100 ሺህ በላይ ሰዎች እንደተሰዉ ነው እኔ የማውቀው።

ሌላው ከሰላማዊ ህዝብ የተጎዳው ምን ያህል ነው የሚል ነው? እነዚህን የምንቆጥረው ጦርነት በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች ያለቁ፣ በአየር ተደብድበው የሞቱ፣ ጦርነቱ በወለደው ረሀብ እና ስደት ያለቁ ብለን ነው። እንዲህ ከፍለን ስንደምራቸው ከግማሽ ሚሊዮን ህዝብ በላይ በትግራይ ብቻ አልቋል። ይሄ እንግዲህ የጎንደር፣ የወሎ፣ የሰሜን ሸዋን… እልቂት ሳንጨምር ነው።

ማሳረጊያ

ህወሓት በርካታ ታሪኮችን ክዶአል። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚፃፉ ታሪኮችን ካስተዋልን ህወሓት ለድል የበቃው አሁንም በስልጣን ላይ በሚገኙት ጥቂት ሰዎች ብቻ እንደሆነ ለማስመሰል እየተሞከረ ነው። ሌላው ቀርቶ እኔን ከአስራ አንዱ ሰዎች መካከል አይደለህም የሚሉ ታሪክ ፀሀፊዎች ተነስተዋል። በእርግጥ ከትላንት በስቲያ ስዩም መስፍን በቴሌቪዥር ሲናገር ስሰማው አስገደ መስራች ነው ብሏል። ነገር ግን በምስረታው ወቅት ያልነበሩትን ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊን እና አቦይ ስብሃት ነጋንም ከአስራአንዳችን ውስጥ ጨምሮአቸዋል። ይህ ስህተት ነው። ምክንያቱም መለስ ወደኤርትራ ከተላኩት ሰልጣኞች ጋር አብሮ አስመራ ድረስ የሄደ ቢሆንም፣ ወደበረሃ ግን ዛሬም ድረስ በማይታወቅ ምክንያት ሳይሄድ ቀርቶ ከሶስት ወር በኋላ ደደቢት መጥቶ የተቀላቀለን ሲሆን አቦይ ስብሃትንም፣ እኛ ደደቢት ከገባን ከሶስት ወር በኋላ ሽሬ ድረስ መጥቼ እኔነኝ የወሰድኩት። ከዚህ በቀር ታሪክ ባናበላሽ ለመጭው ትውልድ መልካም ነው። በቀደመው ዘመናችን ያበላሽነው ከበቂ በላይ ዋጋ እያስከፈለን ነውና።

# ህወሓት ከጋርዮሻዊ አመራር ወደአንድ ሰው ብቸኛ መሪነት



**አቶ ገብሩ አስራት**
**የአረና ሊቀመንበር**

## ህወሓት የተመሰረተበት ምክንያቶች

ህወሓት ከምስረታው ጀምሮ የነበረውን ሁኔታ ማወቅ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ በወቅቱ በኢትዮጵያ ፀረ-ዴሞክራሲ ባህሪ የነበረው አምባገነን የደርግ ስርዓት የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ስለዚህ ዋነኛው አላማ ይህንን አምባገነናዊ ስርዓት መታገል ነው፡፡ ትግሉ የተለያዩ ዝርዝር ፖለቲካዊ አላማዎች ነበሩት፡፡ የብሔር ብሔረሰብ መብቶችን የማስከበር ጉዳይን በሚመለከት ከዛ በፊት የነበሩ ስርዓቶች ይሁን ከዛ በኃላ የተነሳው የደርግ መንግስት የብሄሮችን እኩልነት እና መብት አላስጠበቁም የሚል እምነት ስለነበረው መታገልን እንደዋነኛ አላማ አድርጎ ይዞት ነበር፡፡ በተጨማሪም በጊዜው ያስቀመጣቸውን ሌሎች አላማዎች ስናይ በጊዜው የነበረውን ባላባታዊ ስርዓት መታገልና እሱን መጣል ሲሆን፣ከውጪ ሃይሎች ጋር በመቀናጀት አገሪቱን የሚመዘብረውን ሃይል የመታገል አጀንዳ ፓርቲው ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝም ይለዋል፡፡ ሌላው በጊዜው ያስቀመጠው አላማ ኢምፔሪያሊዝምን ከጣልቃ ገብነትም ያለፈውን የውጭ ሃይሎች /በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የነበረውን ተፅዕኖ/ መቋቋም የሚል ነበር፡፡ በጊዜው አንኳር የነበሩ እኔ የማስታውሳቸው ሌሎችም ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ አላማዎች ነበሩት፡፡

## መገንጠል /የትግራይ ሪፖብሊክ መመስረት/

ህወሓት አስቀድሞ አላማው ይህ አልነበረም፡፡ የመጀመሪያ አላማው እንዲያውም ቅይጥ አመለካከት ነበር፡፡ በአንድ በኩል የወዛደሩ አለማቀፋዊነት የሚል እና በሌላ በኩል ደግሞ ብሔሮች፣ሕዝቦች ከዛም አልፎ ላባደሮች መተባበር አለባቸው የሚል አቋም ሲኖረው የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል የሚለውን የመብት ጥያቄ በፕሮግራሙ ውስጥ እስከ መጨረሻው ድረስ የያዘው አቋም አልነበረም፡፡

የትግራይ ሕዝብ ለነፃነት መታገል አለበት የሚል ፕሮግራም የነበረው ግንባር ግድሊ ሓርነት ትግራይ የሚባለው ድርጅት ነበር፡፡ ትግራይ ሊብሬሽን ፍሮንት/ TLF/ የሚባልው ድርጅት በጊዜው የነበረው አቋም የትግራይ ህዝብ ጥያቄ የቀኝ ግዛት ጥያቄ ነውና ለነፃነት መታገል አለብን የሚል ነበር፡፡ እስከ 1968ዓ.ም ጥቅምት-ህዳር ድረስ ባለው ጊዜ ከዚህ ድርጅት ጋር ህወሓት ልዩነት ነበረው፡፡ የህወሓት አቋም የትግራይ ህዝቦች ጥያቄ የቀኝ ግዛት አይደለም፣ በነፃነትም መፈታትም የለበትም የሚል ነበር፡፡ ስለዚህ ህወሓት ይህንን ድርጅት አፍርሶ ከመታ በኂላ ከተረፉት ጋር ተዋህዷል፡፡ ህወሓት ከዚህ ድርጅት ጋር ከተዋህደ በኂላ በፕሮግራሙ ውስጥ የትግራይ ህዝብ ጥያቄ የነፃነት ጥያቄ ነው፤ ትግራይ ነፃነት ማግኘት አለባት በማለት ለ6 ወራት ፕሮግራሙን አራምዷል፡፡ ይሄ እንግዲህ በድርጅቱ ታሪክ ውስጥ እንደ አንድ ጥቁር ነጥብ ተብሎም የሚታወቅ ነው፡፡ በኂላ ግን ታጋዩ ባደረገው እንቅስቃሴ ታርሞ ለነፃነት የሚባለው ነገር ስህተት ስለሆነ የብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል የሚለውን ብቻ ተቀብለን መሄድ አለብን ስለዚህ አንድ ህዝብ ቢፈልግ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች እና ብሄረሰቦች ጋር አብሮ ይኖራል ሲያስፈልገውም የህዝቡ ምርጫም ከሆነ የራሱን መንግስት መስርቶ አንድ ነፃ ሀገር ማቋቋም ይችላል በማለት አሁን ያለውን የፌደራል መስተዳደርን በመርህ ደረጃ ፈቅዶ በህገ መንግስቱም፣ በፕሮግራም ውስጥም አካቷል፡፡ ይሄ ነገር አሻሚ ነው፡፡ እንዴት ነው በአንድ አገር በህብረት እየኖሩ ችግር፣ ጭቆናም ቢኖር አብሮ መጋፈጥ ነው እንጂ ሲመቸን በአንድነት ሲከፋኝ ደግሞ ተነጥዬ እኖራለሁ የሚለው አስተሳሰብ ስህተት እንደሆነ በፕሮግራሙ ላይ መጀመሪያ ያለው የነፃነት ጉዳይ ሳይሆን አሁን ያለውን ፕሮግራም የሚተች ነው፡፡

## ስለማሌሊት ያልተባሉ ጥቂት ነገሮች

ስለ ማሌሊት ያልተባለ ነገር አለ ብዬ ለመናገር ያስቸግረኛል፡፡ በተለያየ ወቅት እና አጋጣሚ ብዙ ነገር ተብሏል፡፡ ህወሓት በተለይ በ77 ዓ.ም አንድ ጉባኤ አካሂዶ ነበር፡፡ በጉባኤው ላይ ከእንግዲህ ግንባሩ ዲሞክራቲክ፤ ሆኖ የተለያዩ መደቦች፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚካፈሉበት፣ የሚሳተፉበት ነው ብሎ ያምን ነበር፡፡ ከዚያ በኂላ በ77ዓ.ም የግንባሩ እንቅስቃሴ በላባደሩ ፓርቲ እስካልተመራ ድረስ የዴሞክራሲ ግቡን አይመታም ተባለ፡፡ ስለዚህም ጉባኤው የላባደር ፓርቲ ማቋቋም አለብን የሚል አቋም ወሰደ፡፡ በዚህ የተነሳ ማሌሊት የሚባለው ድርጀት በጉባኤ ደረጃ በ77 ዓ.ም መጨረሻ ገደማ አቋቋመ፡፡ ይሄን አቋቁሞ ጥቂት እንደሄደ አለም አቀፍ ሁኔታዎች ተለዋወጡ፡፡ በዛን ጊዜ ህወሓት ግንኙነት የነበረው አልባኒያ ከምትባል አገር ጋር ነበር፡፡ 3 ሚሊዮን ህዝብ ካላት እና አክራሪ ኮሚኒስት ከሆነችው ከአልባኒያ እና ከአንዳንድ አውሮፓ ውስጥ ከነበሩ ማሌት የሚባሉ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቱን አጠናክሮ ነበር፡፡ በ1981ዓ.ም አካባቢ የአልባኒያ እና ሌሎች የምስራቅ አውሮፓ አገሮች መበታተን ተከትሎ ህወሓት አንዳችም ጉባኤ ሳያደርግ፣ የማንንም ውሳኔ ሀሳብ ሳይጠይቅ ማሌሊትን አፈረሰ፡፡ ድርጅቱን ካፈረሰ በኂላ በቀጣይ ከምዕራቡ አለም ጋር ተዋህጄ ለዲሞክራሲ እታገላለሁ በሚል በአዲስ መልክ መንቀሳቀስ ጀመረ፡፡

## ከጋርዮሻዊ አመራር ወደ አንድ ሰው ብቸኛ መሪነት

በአንድ ጥያቄ በአንድ ጋዜጣ ላይ ብቻ የሚመለስ አይደለም፡፡ በጣም ትልቅ ጥያቄ ነው፡፡ ሂደቱ በጣም ረጅም ነው፡፡ እስካሁን ድረስ እንደምናውቀው ህወሓት ወደ 37 አመታት ሆኖታል፡፡ እና አሁን ያለው አጠቃላይ የፓርቲው ሁኔታ ከድርጅቱ ባህሪም የሚነሳ ይመስለኛል፡፡ ድርጅቱ አወቃቀሩ እና አፈጣጠሩ ለዚህ ለማዕከላዊ ኮሚቴው የበለጠ ስልጣን የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ለስራ አስፈፃሚው የበለጠ ስልጣን የሚሰጥ ነበር፡፡ በጋራ የሚወስን ድርጅትም ነበር፡፡ ህወሓት ከሽምቅ ተዋጊነት ወደ መንግስት ሲሸጋገር ያ የለመደውን አሰራር፣ አመራር ይዞ ነው የተሻገረው እንጂ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታ እንዲሳካ ምን ምን መሰረታዊ ለውጦች መካሄድ አለባቸው ብሎ በደንብ አጢኖ አስቦበት የተነሳ አይመስለኝም፡፡ ችግሩ እዚህ ላይ ነው፡፡ ይሄ የአንድ ሰው አምባገነንነት አሁን እየተቀነቀነ ካለው የቡድን ዴሞክራሲ የሚባለው ወደፊት ዞሮ ዞሮ ወደ አንድ ሰው አገዛዝ መሰባሰቡ አይቀርም፡፡ መሰረታዊ የዴሞክራሲ ተቋማት፣ የብዙሃን ፓርቲዎች ስርዓት፣ የህግ የበላይነት፣ የመንግስት አካላት አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበት አወቃቀር ማለትም የህግ መወሰኛው፣ የህግ ፈፃሚውና ህግ ተርጓሚው የነዚህ እርስ በርስ ቁጥጥር (Check and balance) እስከ ሌለ ድረስ ዞሮ ዞሮ የአንድ ሰው አምባገነንነት እንደሚመጣ የታወቀ ነው፡፡ መታየት ካለበት ጉዳዩ ከመሰረቱ ነው መታየት ያለበት፡፡ አሁንም ቢሆን ለወደፊቱ ልምድ የሚሆን የሚመስለኝ በአንድ ፓርቲ አመራር ውስጥ የፈለገውን ያህል ዴሞክራሲ ቢኖርም ይህ ዴሞክራሲ ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ ህብረተሰቡ እስካልተቆጣጠረው፤ ዞሮ ዞሮ የቡድን ከዛም አልፎ የግለሰብ አምባገነንነት እንደሚኖር የታወቀ ነው፡፡ ስለዚህ የህወሓት ሂደትም ሳየው መጀመሪያ በአንድ ፓርቲ አምባገነንነት ያምን ነበር፡፡ በተለይ በድርጅቱ ይንፀባረቅ የነበረው የማሌሊት እምነትም ይሄ የላባደሩ አምባገነንነትን ነው፡፡ የላብአደር አምባነንነት ማለት ላባደሩ ሌሎቹን መደቦች ጨቁኖ መግዛት ትክክለኛ ህጋዊ ነው ብሎ የሚያምን ድርጅት ነው፡፡ ችግሩ የሚነሳው ከዚህ በተሳሳተ ርዕዮት ዓለም ነው፡፡ አሁንም የዚህ ርዕዮተ ዓለም ቅሪት አለ፡፡ የአንድ ፓርቲ የበላይነት በህዝቡ ውስጥ መኖር አለበት በሚለው አስተሳሰብ አሁንም ድረስ ያምናል፡፡ ሌሎች ፓርቲዎች እንዲሁ ለይስሙላ ወይም የውጪውን አለም እና ሌላውን የህብረተሰብ ክፍል ለማሳሳት ካልሆነ በስተቀር እንደ እምነት እስካሁንም ድረስ ህወሓት ከማሌሊት እምነት (በተለይ የአንድ ፓርቲ መሪነት /Vanguard ship) የአንድ ፓርቲ እና የአንድ መደብ የበላይነት ብሎ ስለሚያምን እዚህ ላይ ዴሞክራሲ ተንዷል ማለት ነው፡፡

ዴሞክራሲ ከተናደ ደግሞ የሚፈጠሩት ተቋማትም ይሄንን መሰረት ያደረጉ ነው የሚሆኑት፡፡ ተቋማቱ ለአንድ ፓርቲ አገዛዝ እንዲመች መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው የአንድ ፓርቲ አገዛዝ፣ የአንድ ግለሰብ አገዛዝ ይኖራል፡፡ መጨረሻውም ይኸው ነው፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር እዚህ ላይ የደረሰው ከሚከተለው ርዕዮት አለም ከሚከተለው ፖለቲካ አቅጣጫ ከሚከተለው እስትራቴጂ ተነስቶ ነው

## የወደፊቱ ህወሓት

ህወሓት እኔ ሳየው ወደፊትም ቢሆን የሚችለው አሁን ያለውን ነው፡፡ ህወሓት በአስተሳሰብ ደረጃ የአንድ ፓርቲ የበላይነት የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት የሚያምን ድርጅት ነው፡፡ ስለዚህ ህወሓት መጀመሪያ ሲነሳ ለዴሞክራሲ ለልማት ለፍትህ ለእኩልነት ቢነሳም አሁን ህወሓት ጭራሽ ከዚህ የተለየ አቋም ይዞ በማራመድ ላይ ነው፡፡ እነ ጋና ለዴሞክራሲ ታግለን ተሰውተናል አይሉም እነ ታንዛኒያ፣ ሞዛምቢክ፣ ቦትስዋና እንዲህ አይሉም፡፡ ነገር ግን ከኢትዮጵያ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመትከል ችለዋል፡፡ ዜጎችን መሸማቀቅ የዜጎችን ስቃይ የሚያመለክት ስርዓት ነው የሆነው ስለዚህ ዞሮ ዞሮ ህወሓት ከድሮዎቹ ስርዓቶች የሚለይበት ነገር ቢኖር በአዋጅ ደረጃ በስም ደረጃ ዴሞክራሲ ከመባሉ በስተቀር አሁን እያካሄደ ያለው የህዝብን መብት ረግጦ የህዝብን የመወሰንና መብት ህገ መንግስቱን ጭምር ረግጦ የኢትዮጵያን ህዝብ አፍኖ የሚገዛ ድርጅት ሆኗል ከእንግዲህ ህወሓትም እሱ የሚመራው መንግስት ከዚህ ውጪም ሊሆን አይችሉም ይሄንን ነው የሚሆኑት፡፡

በተለይ እኔ ዝም ብሎ እንዳጋጣሚ ሳይሆን ግዛቱን ለማጠናከር በስልጣን ላይ ረጅም ጊዜ ለመቆየት እየወሰዳቸው ያሉት እርምጃዎች ከህዝቡ እየነጠሉት ነው፡፡ ለምሳሌ የፀር ሽብር አዋጁ፣ ከዚያም ቀደም ብሎ የማህበራት ማደራጀት አዋጅ፣ የፕሬስ አዋጅ ይሄ ሁሉ ያወጻቸው ህዝቡን አፍኖ በስልጣን የሚቆይበት ሁኔታ ለመፍጠር እንጂ ዴሞክራሲ ለማጠናከር ወይ ቁጥጥር ለማድረግ አይደለም፡፡ አሁን ደግሞ ከዛ አልፎ የህዝቡን ፖለቲካዊ ህይወት ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ ህይወት ለመቆጣጠር አዋጅ አውጥቷል፡፡ በቅርቡ የሊዝ የሚባለው ከተማ ውስጥ ያለው መሬት በሙሉ የኔ ነው፡፡ እንደውም ቤቱም ጭምር የኔ ነው፡፡ እያለ ነው ምክንያቱም ከመሬቱ ውጪ ቤቱ ስለሌለ ቤቱ በሚሸጥበት ጊዜ የናንተ ብሎኬቱ እንጨቱ ቆርቆሮ ነው እንጂ ከዛ የተለየ የኔነው ከዛ ሲሸጥ ዋናውን መውሰድ ያለብኝ እኔ ነኝ ብሎ አውጇል ይሄ ህዝብን ለመቆጣጠር የህዝቡን የኢኮኖሚ አቅም አዳክሞ የመንግስትን ጡንቻ ለማጠናከር የወሰደው እርምጃ ነው፡፡ የህወሓት ኢህዴግ መጨረሻውም የኃይለ ሥላሴ እና የደርግ አይነት ከህዝብ መነጠል ነው የሚሆነው፡፡ አሁን የሚታይ ፍርሃት በህዝብ ውስጥ አለ ከፍተኛ ፍርሃት የማየው ስልጣኑ ለማርዘም እየፈለገ ያለው እነዚህ የፀጥታ መዋቅሮች የስለላ ተጠቅሞ ህዝቡ ፍርሃትን ሊሻገረው ይችላል የዛን የህወሓት ኢህዴግ የት እንደሚቆም ለመተንበይ ቀላል አይደለም፡፡ እንዲሁ ከውጪ እንደምናየው ጠንካራ የማይበገር ሆኖ ማየቱ ስህተት ነው አንድ ስርዓት ጥንካሬው ዴሞክራሲያዊ ካልሆነ ደካማ ነው ይፈረከረካል እርስ በርሱም ይብላላል የቡድን አምባገነንነት መኖሩ ውጪ ያለው ሳይሆን ፓርቲ ውስጥ ያሉ ሰዎች ጭምር መንግስት ውስጥ ያሉ ሰዎች ጭምር ይከፍላሉ፡፡ ስለዚህ ስርዓቱ በዚህ ጊዜ መቆሚያ አይኖረውም፡፡

## የህወሓት የተሳኩ እና ያልተሳኩ ግቦች

ህወሓት ሲቋቋም ካስቀመጣቸው አላማዎች ውስጥ አንዱ ተሳክቷል ለማለት እችላለሁ፡፡ እሱም የደርግ ውድቀት ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ፍፁም ኢ-ዲሞክራሲያዊ ፍፁም አምባነን የነበር ስርዓት ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ባደረጉት ትግል ወድቋል፡፡ ደርግ በዚች አገር ከፈፀመው ከፍተኛ ጥፋት አንፃር ስርዓቱ መውደቁ የተሳካ ነው፡፡ ሌላው ግን በተለይ አውጆ ያስቀመጣቸው አላማዎች አንዳንዱ የተሳካ ሊመስል ይችላል፡፡ በተለይ ብሔር ብሔረሰቦች የሚባሉት ትግራይ፣ ኦሮሞ፣ አማራ እና በደቡብ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች በደርግ ጊዜ በተሻለ መብታችን ተከብሯል የሚል ብዥታ አላቸው፡፡ በርግጥ እነዚህ ብሄር ብሄረሰቦች ያገኙት ቢኖር ያው በቋንቋቸው ቤት፣ ት/ቤትም ሆነ ሌላም አካባቢ ቋንቋቸውን መጠቀማቸው ከነበረው የተለወጠ ነገር ነው፡፡ በመሰረቱ ግን ባህሉ መከበሩ ብቻ አይደለም፡፡ ይሄ አንድ ገፅታ ነው፡፡ ዋናው ነገር መብት ተከብሯል ወይ? ነዋሪዎቹ በአካባቢያቸው ራሳቸው ይወስናሉ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ይሄ ነው መሰረቱ፡፡ አካባቢውን የማልማት መብት አለው ወይ? በአካባቢው የፖለቲካ ስልጣን ኖሮት መወሰን ይችላል ወይ? የሚለው ግን በመሰረታዊነት አልተመለሰም፡፡ እንግዲህ ቅድም ካነሳሁት የህወሓት /ኢህአዴግ/ አምባገነንነት ጋርም አብሮ የሚያያዝ ነው፡፡ እንኳን ብሄር ብሄረሰቦች እላይ ያሉት የፓርቲ አባላትም መወሰን አይችሉም፡፡ የፖለቲካ ነፃነት የላቸውም፡፡ ዜጎች በጠቅላላ የፖለቲካ ነጻነት በሌለበት የብሔር ብሔረሰብ መብት ተከብሯል ብሎ አፍ ሞልቶ መናገር አይቻልም፡፡ በቋንቋ የመናገር፣ ባህል የማክበር፣ ታሪኩና ወጉ የመነገሩ ብቻ ካልሆነ በስተቀር የተነሳበት መሰረት በአካባቢያቸው ልማትን ያለማሉ፣ በራሳቸው ተነሳሽነት የአካባቢ መሪያቸውን መምረጥ የሚችሉበት ሁኔታን እና በአገሪቷ ውስጥ ለዜጎች የሚፈቀደው መብትና ነፃነት በነዚህ ብሔረሰቦች ተግባራዊ ሲሆን የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተከብሯል ሊባል ይችላል፡፡ ስለዚህ ህወሓት ከተነሳበት አላማ አንፃር ስናየው ብሄር ብሄረሰቦችን በቋንቋቸው እንዲናገሩ በመፍቀድ ላይ ብቻ ተገድቧል፡፡ ይሄ ለኔ የመብቱ ትንሽ ክፍል እንጂ ዋናው ክፍል አለመመለሱን ነው የሚያሳየኝ፡፡ ስለዚህ ህወሓት ደርግን ከመጣል ባለፈ ብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋቸው እና በወጋቸው ከመኖር ያለፈ ለውጥ አላመጣላቸውም፡፡ በመሰረቱ ለእኔ የብሔሮች ጥያቄ አልተመለሰም፡፡ ያልተመለሰበት ምክንያትም ህወሓት የቆመለትን አላማ እርግፍ አድርጎ ትቶ ለስልጣን ብቻ በመቆሙ ነው፡፡ ህወሓት ሲነሳ እንደተራው ዜጋ እንደ አንድ ዜጋ ሆኖ እያንዳንዱ በህወሓት ውስጥ ያለው አባል እንደተራው ህዝብም መብቱ ይከበርለታል፣ የመናገር፣ የመጻፍ ሰብዓዊ መብቱ እና ፖለቲካዊ መብቱ ይከበርለታል ከሚል ነበር፡፡ ስልጣን ከተቆናጠጠ በኂላ ግን ስልጣን ማስጠበቁን እንጂ የህዝቡን መብት በጭራሽ ረስቶታል፡፡ ደግሞም ለራሱ ስልጣን ቅድሚያ ከሰጠ ህዝቡን መጨቆን፣ ማፈን፣ መርገጥ የግድ ይሆንበታል፡፡ እንደዚህ ካላደረገና ለህዝቡ መብት ከሰጠ በስልጣን አይቆይም፡፡ ህዝቡ የመረጠው ነው በስልጣን ሊቆይ የሚችለው፡፡ እናም እነዚህ ሁለት ነገሮች ተፃራሪ ናቸው፡፡ የህዝብ መብት ማክበር የአምባገነኖች በስልጣን ላይ መቆየት የሚፃረሩ ስለሆኑ ህወሓት/ ኢህአዴግ የመረጠው አምባገነን ሆኖ ይችን አገር ማስተዳደር እና መግዛት ነው፡፡

## ስለህወሓት የምስረታ በዓል አከባበር

ይሄ በአል አንድ ገፅታ ብቻ ያለው በዓል አይመስለኝም፡፡ ህወሓት ውስጥ እያለሁ በአሉን በሁለት መንገድ አከብረው ነበር፡፡ አንዱም ህልማቸው ባይሳካላቸውም መብት ረገጣ እንዲቆም፣ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ የህግ የበላይነት እንዲከበር፣ የብሔሮችና የዜጐች መብቶች እንዲከበሩ ብለው ወጥተው የቀሩ 54ሺ ሰዎችን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ሌላው ገፅታ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ቀን ዴሞክራሲ የተረጋገጠበት ነው፣ ሰብዓዊ መብት የተረጋገጠበት፣ ልማት የተካሄደበት፣ ፍትህና እኩልነት የተረጋገጠበት ነው የሚል ብዥታ ነበረኝ፡፡ ከፓርቲው ጋር በነበርኩበት ወቅት ከነዚህ ሁለት ነገሮች አንፃር በዓሉን አከብረው ነበር፡፡ አሁን ግን በሁለተኝነት የተጠቀሱት ጉዳይ በጭራሽ እንደሌለ አረጋግጬለሁ፡፡ ቅድም ያላነሳሁት ኢህአዴግ እንደ ህጋዊ ቅቡልነት አድርጎ እየወሰደው ያለው በኢትዮጵያ የልማት ኃይል ነኝ ብሎ የሚናገረው ነገር በፍፁም የለም፡፡ ምክንያቱም በኔ ግንዛቤ ልማት ማለት ፎቆችን መገንባት፣ መንገድ መስራት፣ ፋብሪካዎችች ማቋቋም አይደለም፡፡ ይሄ የልማት አንዱ ገፅታ ብቻ ነው፡፡ ልማት ሶስት ገፅታዎች አሉት፡፡ አንዱ ልማትን እድገት ነው የሚያሰኘው ፍትሃዊ የሆነ የኢኮኖሚ ክፍፍል በዜጎች ውስጥ ሲኖረው ነው፡፡ ሁለተኛ ልማት እንዲኖር የዜጐች ክብር መጠበቅ አለበት፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ሁለት ገፅታዎች አንፃር ኢህአዴግ ልማት እያመጣ አይደለም፡፡ ጥቂት ከስርዓቱ ጋር ቁርኝት ያላቸው በጣም ሀብታም ሆነው ብዙ ገንዘብ ያጠፋሉ፡፡ በሚሊዮን የሚቆጠረው ህዝብ ግን ከተማ ውስጥ ሳይቀር የሚበላ አጥተው በጣም በከፍተኛ ችግር ተውጠዋል፡፡ ይህ ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍልን ኢህአዴግ ማስተካከል ባለመቻሉ ልማትን አምጥቷል ብዬ አላምንም፡፡

እናም እኔ በዓሉን የማከብረው እነዛ የተሰዉ ጓዶችን ለማክበር ነው፡፡ ምክንያቱም አላማቸው ባይሳካም ለፍትህና ለእኩልነት ብለው የታገሉ ስለነበሩ ይሄን ገፅታ ብቻ ሁልጊዜ አከብረዋለሁ፡፡

# የፍትህ መልዕክት ለህወሓት

በኢትዮጵያ ከ1966 ዓ.ም. ወዲህ በርካታ ድርጅቶች ተፈጥረው የፖለቲካ ትግል ሲያካሄዱ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ህዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ /ህወሓት/ ነው፡፡ ይህ ድርጅት ከነገ በስቲያ የተመሰረተበትን ሰላሳ ሰባተኛ አመት ያከብራል፡፡

ህወሓት የደርግ ስርዓትን ለመጣል በተደረገው ትግል የግንባር ቀደሙን ሚና መጫወቱ የሚካድ አይደለም፡፡ እናም የደርግ ስርዓት ወድቆ የኢህአዴግ መንግስት ቢተካም አሁንም በኢህአዴግ ውስጥ የግንባር ቀደሙን ሚና እየተጫወተ ያለው ህወሓት መሆኑ የአደባባይ እውነት ነው፡፡

ከ1983ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ለተከሰቱ በጎም ሆነ መጥፎ ሁነቶችም በግንባር ቀደምነት ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ህወሓት ነው፡፡ ፍትህ በአጠቃላይ ሲገመገም በሀገሪቱ የፖለቲካ ስልጣን ላይ የአንበሳውን ድርሻ የያዘው ህወሓት ያበረከተው ጥቂት በጎ ነገር ቢኖርም እንደ ሀገር ሲታይ ግን ያጠፋው ይበዛል ብላ ታምናለች፡፡

በፍትህ እምነት ሀገሪቱ ወደብ አልባ ልትሆን የቻለችው በህወሓት አመራር ፍላጎት ወይም ድክመት ነው፡፡ በቋንቋ ላይ ከተመሰረተው ፌደራሊዝምም ምንጩ ህወሓት ነው፡፡ ምክንያቱም ህወሓት የብሔር ጭቆና አለ ብሎ ብረት፣ አንስቶ በሚታገልበት ዘመን፤ ሌላኛው አጋር ድርጅት በወቅቱ ኢህዴን ይባል የነበረው፣ ዛሬ ብአዴን የሚል የአንድ ብሄር መጠሪያ የያዘው የብሔር ድርጅት አልነበረም፡፡ ነፍጥ ያነሳውም አምባነንነትን በዴሞክራሲያዊ ስርዓት እቀይራለሁ ብሎ እንጂ ቀዳሚው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ጥያቄ የብሔር ጭቆና ነው በሚል እምነት አልነበረም፡፡

በደርግ ውድቀት ዋዜማ የተቋቋመው ኦህዴድ በትጥቅ ትግሉ ላይ የነበረው ተሳትፎ እዚህ ግባ የሚባል ስላልነበረ፣ ደርግ ከወደቀ በኋላም በግንባሩ ውስጥ የተሰጠው ቦታ በትክክል ድርጅቱ ከወከለው ብሔር ህዝብ ቁጥር ጋር የሚመጣጠን እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ደኢህዴን ጭራሽ በትግሉ ላይ ያልነበረ ከመሆኑ በተጨማሪ የተቋቋመውም በ1985ዓ.ም እንደሆነ አይዘነጋም፡፡ እናም በዚህ የተነሳ አራቱ ድርጅቶች በመሰረቱት ኢህአዴግ ውስጥ የህወሓት ሚና እና ተፅዕኖ ፍፁም የበዛ ሊሆን ችሎአል፡፡ ለዚህም ነው ፍትህ የህወሓት ስህተቶች የመንግስት ስህተቶች ተደርገው ሊወሰዱ ይገባል የምትለው፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ የ3000ሺ አመት ሳይሆን የ100 ነው የሚለው የታሪክ ብረዛም ምንጭ ህወሓት ነው፡፡ ህወሓት በተደጋጋሚ ጊዜ እንዳሳየው ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር ተቃርኖ ውስጥ በመግባት ‹‹ነፃ ላወጣው›› ተመሰረትኩለት ከሚለው ህዝብ አቋም እና ፍላጎት በእጅጉ ያፈነገጠ እና የራቀ የታሪክ አመለካከት አንፀባርቋል፡፡ ህወሓት ከምስረታው ጀምሮ በሩ የዘጋ ወይም እጅግ ምስጢራዊ ከመሆኑ የተነሳ ለታሪክ ተመራማሪዎችም ሆነ ለጋዜጠኞች ዝግ የሆነበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡

ከላይ እንዳልነው ሀገራዊ ተፅእኖው እጅግ የበዛ የሆነውን ፓርቲ ስለውስጣዊ አወቃቀሩ ተመራማሪዎች ማጥናታቸው ፋይዳው የላቀ ነውና ፓርቲው ይህንን ጉዳይም እንዲያስብበት ፍትህ ታሳስባለች፡፡

በቅርቡ የቀድሞ የህወሓት ሊቀመንበር አቦይ ስብሓት ነጋ በአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ በሚተላለፈው የትግርኛ ፕሮግራም ላይ ቀርበው የአክሱም ታሪክ የኢትዮጵያ አይደለም፤ የትግራይም አይደለም፤ ከትግራይም የአጋሜ አውራጃን እና ተንቤንን አይመለከትም በሚል ያቀረቡት ትንተና ህወሓት ከታሪክ ጋር ያለውን ታሪካዊ ፀብ ሊያመላክት የሚችል በመሆኑ በዚህ በምስረታ በአሉ ላይ ይህ አቋም የግለሰቡ ወይም የፓርቲው ለመሆኑ ይፋ ይሆን ዘንድ ፍትህ ትጠይቃለች፡፡

ከዚህ ባሻገርም ህወሓት በትግሉ ዘመን ያፈራሁት ነው በሚል በኤፈርት ስም ያቋቋመው የንግድ ድርጅት ገቢ እና ወጪው፣ እስከ ዛሬ ድረስ ከንግዱ ያተረፈው፣ እንዲሁም በሀገሪቱ የንግድ ስርዓት ላይ እያደረሰ ያለው በጎም ይሁን መጥፎ ገፅታ ይፋ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የኤፈርት ገቢ የት እንደገባ፣ ከኤፈርት በሚገኘው ትርፍ ምን እንደተሰራ፣ ማን እንደተጠቀመም የመጠየቂያው ጊዜ አሁን እንደሆነ ፍትህ ታስገነዝባለች፡፡

ከላይ እንደተገለፀው በትግሉ ዘመን ዋነኛው ባለድርሻ ህወሓት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በርካታ አካል ጉዳተኛ ታጋዮች እና ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው የተሰዉባቸው ዜጎች ከኤፈርት ገቢ መጠቀም ያለመጠቀማቸውም በግልፅ ሊነገር ይገባል እንላለን፡፡

ሌላው ጉዳይ ተደጋጋሚ ጊዜ እንደሚነገረው ህወሓትን ለመመስረት ወደ ደደቢት በረሃ የገቡት አስራ አንድ ሰዎች እንደሆኑ ነው፡፡ በፍትህ የምርመራ ዘገባ መሰረትም ከአስራ አንዱ አንዱ የአማራ ተወላጅ ሲሆን አብተው ታከለ ይባላል፡፡ ይህ ሰው ፎቶው በሰማዕታት ሀውልት ላይ አለመቀመጡ እና በህወሓት ታሪክ ውስጥም የሚገባውን ስፍራ አለማግኘቱ በፍትህ እምነት ተገቢ አይደለም፤ እናም ቢያንስ ህወሓት በሰላሳ ሰባተኛ በዓሉ ላይ ለታጋዩ የሚገባውን ክብር ይሰጥ ዘንድ ፍትህ አጥብቃ ትጠይቃለች፡፡

## አህቢንዲ

ahbindi@gmail.com

በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ ጊዜ ስለ አንድ አስተማሪዬ የማልረሳው ትዝታ አለኝ፡፡ ይህ አስተማሪ የሚያስተምረን ኮርስ ትንሽ ጠንከር ያለ ከመሆኑ ጋር ክብደቱን ተገን አድርጎ ብዙ ተማሪ እንደሚጥል ይዝት ነበር፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የኮርሱ መክበድ ሳያንስ የአስተማሪው ዛቻ ያስደነገጠው ቀለሜ ሌሎች ኮርሶችን እርግፍ አድርጎ ትቶ ይህንን ኮርስ ብቻ ማጥናቱን ቀጠለ፡፡ ነገር ግን ዛቻው ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጠናክሮ በመቀጠሉ ተማሪው ምንም ጠንክሮ ቢሰራም ለማለፍ ግን የአስተማሪው ይሁንታ ወሳኝ ሆኖ ስላገኘው ተስፋውን ቆርጦ ጭርሱን ማጥናቱን አቆረጠ፡፡ ካዲያ አንድ ቀን አጅሬ የተለመደውን የማስፈራሪያውን ቀረርቶ ሲጀምር ተስፋ የቆረጠው ተማሪ ግን ሊሰማው ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ ፍርሀታቸው ገደቡን አልፎ ወደ ተስፋ መቁረጥ የተሸጋገሩት ተማሪዎች ይባስ ብለው ጉዳዩን ለሚመለከተው ክፍል አቅርበው አስተማሪውን ከማስቀጣት ባለፈ ከተደጋጋሚ የዲሲፕሊን ጥፋቶቹ ሊታረም ያልቻለው አጅሬ ለመባረሩ ምክንያት ሆነዋል፡፡ የፍርሀትም መጨረሻ አለው!

በብዙ መስኮች መጠነኛ ፍርሀት (tension) ጥሩ ነው ያሰራል፡፡ መጠነኛ ፍርሀት በተፈጥሮው ፈሪዎቹን ፍርሀታቸውን ዋጥ አድርገው ፍርሀታቸው እስኪወገድ ድረስ በትጋት እንዲሰሩ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡ ተገቢ ፍርሀት ተማሪዎችን ለጥናት ያነሳሳል፤ ነጋዴዎችን በተወሰነ መልኩ እንዳያጭበረብሩ ያግዳቸዋል፤ ለአገልግሎት ሰጪ ሰራተኞች ለህብረተሰባቸው ጥሩ አገልግሎት እንዲሰጡ ያነሳሳቸዋል፡፡ መንግስትም ቢሆን የመረጠውን ህዝብ በቅንነት ለማገልገል መጠነኛ ፍርሀት ያስፈልገዋል፡፡ ነገር ግን ከመጠነኛ ፍርሀትም ጋር ማንም አካል በቆመለት አላማ ላይ ፍላጎት እና ዕምነት ካልታከለበት ፍርሀት ብቻውን ውጤታማ ያደርጋል ማለት ዘበት ነው፡፡ በተቃራኒው የመጨረሻው የፍርሀት ጫፍ ላይ የደረሱ አካላት ከመስራት ይልቅ ወደ ተስፋ መቁረጥ ደረጃ ይሸጋገራሉ፡፡ ተስፋ የቆረጠ ሰው ማለት ‘ያለኝን ሁሉ አጥቼአለሁ ወይም ወደፊት የማጣ ከሆነ ከዚህ የበለጠ ምን ሊመጣብኝ?’ የሚል ደረጃ ላይ የደረሰ ማለት ነው፡፡ እጅግ በጣም የፈራ ተማሪ ከማጥናት ውጭ ያሉ አማራጮችን ያፈላልጋል ልክ ከላይ እንደተጠቀሱት ተማሪዎች፡፡ በጣም የፈራ ነጋዴም ጠንክሮ ሰርቶ የተጣለበትን የዜግነት ግዴታ(ግብር) ከመወጣት ይልቅ አደገኛ የሆኑ ህገ-ወጥ አሰራሮች ውስጥ እጁን ያስገባል፡፡ ከልክ በላይ ቁጥጥሩ የከፋበት የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ሰራተኛ “ከመባረር በላይ ምን እንዳይመጣብኝ?” ሲል በተቃራኒው ምንም ተቆጣጣሪ ከሌለበት ደግሞ የሻይ እና የዕረፍት ጊዜው በዛለት ማለት ነው፡፡ የመጨረሻ ፍርሀት ላይ የደረሰ መንግስት ብዙም አይተን ባናውቅም እዛ ደረጃ ከደረሰ ግን ህዝቡ ፍሬን የሌለው መኪና ውስጥ ነው ያለው ማለት እንችላለን፡፡ በተቃራኒው ብዙ ጊዜ እንደታዘብነው መንግስት ቅንጣት ታክል የህዝብ ፍራቻ ካላደረበት ልክ እንደ ጋዳፊ ህዝቡን በረሮ እና አይጥ አድርጎ ማየት ይጀምራል፡፡

ሰዎች የፍርሀት ጣሪያ ላይ ሲደርሱ ከተስፋ ይልቅ ጨለማን አሻግረው መመልከት ይጀምራሉ፡፡ በድብቅ ሲንሾካሸኩበት የነበሩ ቅሬታዎቻቸውን በገሀድ መናገር ይጀምራሉ፡፡ በነገራችን ላይ ህዝባችን የመጨረሻ የፍርሀት ደረጃ ላይ ደርሷል ብዬ ባላምንም ወደዛው የሚያስኬደውን መንገድ እንደጀመረ ይሰማኛል፡፡ ልብ ብላችሁ ከሆነ ከሁለት እና ሶስት ዐመታት በፊት ሰዎች በህዝብ መገልገያ ስፍራዎች አካባቢ ሳንሱር ሳያደርጉ እንዳመጣላቸው የውስጣቸውን ስሜት አይገልፁም ነበር፡፡ ዛሬ ግን ግራ ቀኝ ሳያማትር፤ ማን ይሰማኛልም ማለት ቀርቶ የቤተ-መንግስት ሰዎቻችንን በአደባባይ መዝለፍ ጀምረዋል፡፡ አንድ የታክሲ ሾፌር ሁሉም ተሳፋሪ እየሰማው የተናገረውን ሳልረሳው ልንገራችሁማ፡፡ “አሁን አሁንስ መንግስት ከገዛ ልጁ የሚቀማ ክፉ አባትን እየመሰለኝ ነው፡፡”

በምሬት ላይ ያለ የሚመስለው ህዝባችን ከቀለዳቸው የምሬት ቀልዶች አንድ ሁለቱን ልጨምርላችሁ፡፡ አንድ ተስፋ የቆረጠ ነጋዴ ምን አለ መሰላችሁ “የቻልኩትን ያህል የግብር ዕዳዬን ከፍዬ ለተቀረው ዕዳዬ ቃሊቲ ማረሚያ እወርዳለሁ ብሎ የሚያስብ ነጋዴ የዋህ ነው፡፡ የኩላሊት ገበያ በውጭ ሀገሮች በጣም እየደራ ስለሆነ መንግስት ግብሩን መክፈል ከተሳነው ነጋዴ ላይ አንድ አንድ ኩላሊት እየወሰደ ለውጭ ሀገር ገበያ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ መቼም ህዝቡ ለአባይ ግድብ ማንኛውንም መስዋዕትነት ለመክፈል ቃል ገብቶ የለ?” እንደዚህ ነጋዴ አባባል ከሆነ እኮ መጀመሪያውኑ በተለያዩ ምክንያቶች አንድ ኩላሊታቸውን ያጡ ነጋዴዎች ከታወቁ መንግስታዊ ሆስፒታሎች ተፅፎ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ የጽሁፍ ማስረጃ ሁልጊዜ አብሯቸው ሊኖር ይገባል ማለት ነው፡፡ እህ! ማስረጃውን ያልያዘ ባለዕዳ የቀረችውን አንድ ኩላሊት ለዕዳ ማካካሻ ቢወሰድበት መሞቱ አይደለም እንዴ? ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ፡፡ ሌላኛው ቴሌን በተመለከተ ይሆናል፡፡ መቼም በቴሌ አገልግሎት መቆራረጥ እና በSMS ጋጋታዎቹ ያልተማረረ አለ ከተባለ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ህልም የሚመስለንን ደሞዝ የሚቆረጥላቸው የፈረንሳዮቹ ወዳጆቻችን የቴሌ አስተዳደሮች መሆን አለባቸው፡፡ በየጊዜው ቴሌ በየቦታው እየሰቀላቸው ያሉ የቻይና አንቴናዎች ምንም ቁጥራቸው ቢጨምርም በጥራት ላይ ያመጡት ለውጥ አለመኖሩን ተከትሎ ቁመተ-ረጅሙ ወዳጄ ምን አለ መሰላችሁ “አሁንማ ቴሌ እንደ እኔ አይነቱን ረጃጅም ሰው እየፈለገ ጭንቅላታችን ላይ የቻይና አንቴና እንዳይሰቅልብን ብቻ፡፡”

## አስተያየት

# የፍርሀት ጣራ

መንግስት በአሁኑ ሰዐት እየተገበራቸው ያሉ ተግባሮች አንዳንዱ በመሰረታዊ ሀሳብ የሚደገፉ ሆነው አፈጻጸማቸው ግን በስህተት የታጨቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የንግዱን ዘርፍ ብንመለከት ግብር ከፋዩ ማህበረሰባችን የሚጠበቅበትን ግዴታ በትክክል እየተወጣ ላለመሆኑ ማስረጃ ማፈላለግ አያሻንም፡፡ ባለፉት ዐመታት በዐመት ሁለት ሺህ(2,000) ብር ግብር ሲከፍል የነበረን አንድ ነጋዴ በአንዴ ሀምሳ ሺህ(50,000) ብር ክፈል ማለት ግን የጤነኝነት አይደለም ምንም እንኳ ይህ ሀምሳ(50,000) ሺህ ብር ትክክለኛው የግብር መጠን ቢሆንም፡፡ በአንድ ሌሊት ሁሉንም ግብር ከፋይ ታማኝ ማድረግ የማይቻል ነው፡፡ ሲጀምር ታማኝ ግብር ከፋይ ለመጥፋቱ ምክንያት የገቢዎች እና ጉሙሩክ ባለስልጣን የራሱን ሚና ተጫውተዋል፡፡ BPR ከመተግበሩ በፊት ድርጅቱ ከላይ እስከታች ድረስ ስር በሰደደ ሙስና የተጨማለቀ እንደነበር እራሱ አምኖ ከ BPR በኋላ ችግሩ እንደሚቀረፍ ቃል ገብቶ ነበር፡፡ ምን ያህል ተሳክቶለታል ለሚለው ጥያቄ በየግዚው በዚህ ነቀርሳ ምክንያት በገፍ የሚያባርራቸው ሰራተኞች ህያው ምስክሮች ስለሆኑ ብዙም ጭንቅላታችሁን አታስጨንቁ፡፡ የሚሰበሰበው ግብር በትክክለኛው መንገድ ለህዝብ አገልግሎት እንደሚውል በተጨባጭ ማሳየት የመንግስት ሀላፊነት ነው፡፡ አለበለዚያ የራሱን ደጅ ሳያጸዳ የሌላውን ደጅ ቆሻሻ ብሎ ከመውቀስ ጋር ይመሳሰላል፡፡ በተጨማሪ የግብር ከፋዩ አመለካከት ላይ ብዙ መሰራት አለበት፡፡ አብዝሃኛው ነጋዴ (በተለይ ደረጃ ሐ) የሂሳብ አያያዝ ዕውቀት ስሌለው ብዙ ነገሮችን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት እራሱን የተበደለ አድርጎ ይቆጥራል፡፡ ያላተረፈ ቢመስለውም ካለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ሱቁ መሙላቱን ቤቱን በቁንጠኛ ዕቃዎች ማስዋቡን እና ሌሎች የግል ወጪዎችን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ የተጠየቀውን ያህል የግብር መጠን በጥሬ ገንዘብ እጁ ላይ ባለመኖሩ (ነጋዴ ብሩን ዕቃ ላይ ማስቀመጡ ባህል መሆኑን ልብ በሉልኝ) ያለአግባብ ዕዳ እንደተጫነበት ያስባል፡፡ እነዚህንና መሰል ችግሮችን መንግስት በቅድሚያ መቅረፍ ይኖርበታል፡፡ አለበለዚያ በጉልበትም ቢሆን የመንግስት ካዝና መሙላት አለበት የሚባል ከሆነ የወርቅ ዕንቁላል የምትጥልን ዶሮ ተስገብግቦ ከማረድ አይተናነስም፡፡

ሌላው ህዝቡን ወደ ፍርሀቱ ጫፍ እየነዳው ያለው ጉዳይ ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በቂ ውይይት ሳይደረግባቸው የሚጸድቁ አዋጅ መመሪያእና ደንቦች ናቸው፡፡ ደንቦች እና መመሪያዎች አዋጅን በጠራራ ፀሀይ ሲቃረኑ እያየን እንገኛለን፡፡ በየመስሪያ ቤቱ ለቅሬታ አቅራቢዎች የምትመለስ ተደጋጋሚ መልስ አለች፡፡ “ቅሬታችሁ ተገቢ ሆኖ ብናገኘውም እኛ ምን እናድርግ? ህግ ነው፡፡” መቼ ይሁን እንደታደሉት ሀገሮች በእኛም ሀገር በአንድ ፓርቲ ውስጥ ያሉ ፖለቲከኞች በህጎች እና በአዋጆች ላይ እርስ በእርስ ሽንጣቸውን ገትረው በመከራከር ለህዝባቸው ትክክለኛውን አማራጭ የሚወስዱት፡፡ የውይይቱን ርዕስ እንኳን ሳያውቁ የፓርቲያቸው አለቃ ሀሳቡን ስላቀረቡት ብቻ በሙሉ ድምፅ ለማፅደቅ እና ለመሻር እጃቸውን ከማውጣት ውጭ ሌላ ሚና ከሌላቸው ፖለቲከኞች ይሰውረን፡፡ ቢያንስ ቢያንስ አስፈጻሚ አካላትንም እኮ ማሳመን አንድ ጉዳይ ነው፡፡

የውሀ ልማት ሰራተኛ የሆኑት አንድ የቧንቧ እና የቁፋሮ ባለሙያዎች በአንድ አካባቢ ላይ የውሀ መስመር ዝርጋታ ስራ ይታዘዛሉ፡፡ ቆፋሪው የተወሰነ ሜትሮችን ከቆፈረ በኋላ ሌላኛው ቧንቧውን ይቀብራል፡፡ ቆፋሪውም መልሶ አፈሩን ወደ ነበረበት ይመልስ የሚል ነበር ተዕዛዙ፡፡ ስራው በሚጀመርበት ቀን ግን የቁፋሮ ሰራተኛው በስተቀር የቧንቧ ሰራተኛው በቦታው ሊገኝ አልቻለም፡፡ የቧንቧ ሰራተኛው ባለመምጣቱ የቁፋሮ ሰራተኛው ምንም ሊሰራ አይችልም ብላችሁ እያሰባችሁ ያላችሁ ካላችሁ በትልቁ ተሳስታችኋል፡፡ የቁፋሮ ሰራተኛው ብቻውን ስራውን ጀመረ፡፡ የተወሰነ ሜትሮችን ይቆፍራል መልሶ አፈሩን ይመልሳል፤ ይቆፍራል መልሶ አፈሩን ይመልሳል፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ የታዘዘውን ያህል ርዝመት ያለ ምንም ጥቅም ቆፍሮ እየመለሰ ጨረሰ፡፡ ሁኔታውን ሲታዘቡ የነበሩ መንደርተኞች ለምን ዝም ብሎ እንደሚደክም ሲጠይቁት “የምሰራውን አውቃለሁ፡፡ ባልሰራ የሚጠብቀኝንም በደንብ አውቃለሁ” የሚል ነበር መልሱ፡፡

የፍርሀቱ ጫፍ የደረሰ ህዝብ በምንም ዐይነት መንገድ ለመንግስት ተገዢ አይሆንም፡፡ በሰሜን አፍሪካ እና በመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮች የተከሰተው ክስተት ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ከሙባረክ የደህንነት ግዝፈት የተነሳ እንኳን ግብፅ ላይ ሳዑዲ አረቢያ ላይም ተቀምጦ ሙባረክን መቃወም የሚታሰብ አልነበረም፡፡ ለቀባሪው አረዱት እንዳይሆንብኝና ደርግ የነበረው ጦር ለቅርብ ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ለሩቆችም አስፈሪ እንደነበር ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ እንደውም ግብፆች ለብዙ ዐመታት መንግስቱ ኃ/ማሪያም ተሸንፎ ከሀገር መውጣቱን ማመን አቅቷቸው እንደነበር ያነበብኩት ትዝ ይለኛል፡፡ ያ አስፈሪ ጦር እዚህ ግባ በማይባል ነገር ግን የመጨረሻ የፍርሀት ጣራ ላይ በደረሰ ጦር መሸነፉ እርግጥ ነበር፡፡ የበዛ ፍርሀት ብቻውን ተስፋ መቁራጥ ሲያስከትል ተስፋ ብቻውን ደግሞ ላም አለኝ በሰማይ … ሆኖ ይቀራል፡፡ እነዚህ ሁለቱም ጠርዘኝነት ባህሪ አላቸው፡፡ ጠርዘኝነት ደግሞ በማንኛውም ሁኔታ የሚደገፍ አይደለም፡፡ አንድዬ ህዝባችንንም መንግስታችንንም ከጠርዘኝነት ይጠብቅልን፡፡ ቸር እንሰንብት!

## ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራ ድርጅት በየሳምንቱ የሚታተም

**የአሳታሚው አድራሻ**
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

**ሥራ አስኪያጅ**
ማስተዋል ብርሃኑ

**ዋና አዘጋጅ**
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

**አዘጋጆች**
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

**ሪፖርተር**
ሰውዓለም ታዬ

**አምደኞች**
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቀጣው እጅጉ
ዮናስ በላይ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

**የሽያጭ ሰራተኞች**
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

**አታሚ**
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ:- አራዳ
ቀበሌ:- 17
የቤት:- 984

# አንድ በሉ

በዚህ አምድ ስር ሀገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ይዳሰሳሉ



ተመስገን ደሳለኝ

# አማራው የህወሓት ቼ ጉቬራ

## (ከህወሓት አስራ አንዱ መስራቾች አንዱ ጎንደሬ ነው)

ፋኖ ተሠማራ
ፋኖ ተሠማራ
እንደ ሆቺሚኒ
እንደ ቼ ጉቬራ
በዱር በገደሉ ታሪክ ልትሰራ

ዛሬ ፋኖ ወደ ዱርም፣ ወደ ገደልም አይሰማራም፡፡ ግራ የሚያጋባው ግን አለመሰማራቱ ብቻ አይደለም፡-

ፋኖ፣ ፋኖ፣… ኧረ ፋኖ…
ጥራኝ ጫካው፣ ጥራኝ ዱሩ
ለአንተም ይሻልሀል ብቻ ከማደሩ
ፋኖ፣ ፋኖ፣ ኧረ ፋኖ፣ ፋኖ…

የሚል ዘፈንም አይዘፍንም፡፡ የቱንም ያህል መብትህ ቢገፈፍ፣ ድምፅህም ቢጭበረበር አንተም አታንጎራጉረው፡፡ ሌላው ቀርቶ እነዚህ መብቶች ቅንጦት ናቸው ብለን ብናልፋቸው እንኳ ቢርብህ እና ቢጠማህም ‹‹ፋኖ፣ ፋኖ፣ አረ ፋኖ…›› ብለህ አትዘፍንም፡፡ ለዚህም ነው ከእስር ይልቅ በረሀብና በጥማት ለመሞት የሚመርጥ ህዝብ ከኢትዮጵያ በቀር የትም የለ የሚል አባባል እየሰማህ ያለህው፡፡ የትም…

መቼም በዛሬ ጊዜ ‹‹ነጋዴ ሙዚቀኞቻችን››ን ‹‹ፋኖ፣ ፋኖ፣ ኧረ ፋኖ…››ን ይዘፍኑልኛል ብለህ እንደማጠብቅ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እነሱ ባይሆን ልማታዊ ዘፈኖችን ይዝፈኑልህ፡፡ ያውም ‹‹የኮፒ ራይት መብት›› እያሉ እያላዘኑብህ፡፡ አየህ! ለእነሱ የመብቶች ሁሉ ቁንጮ መብት፣ የኮፒ ራይት መብት ነው፡፡ ለዚህም ነው ከኮፒ ራይታቸው ውጭ ወደብ መጣ፣ ወደብ ሄደ፤ ኑሮ ተወደደ፣ነዳጅ ጨመረ፤ ምርጫ ተጭበረበረ፣ ኮሮጆ ተሰረቀ፤ ፍትህ ተዛባ፣ሙስና ተስፋፋ፤ አምባገነንነት ነገሰ፣ ጨመንጃ የበላይ ሆነ…ጉዳያቸው ያልሆነው፡፡ ብቻ ያንቡሌ፣ ጨንበላላ፣ ከስከሲና፣ ወላይታ ጊዜ ነው፣ አለምዬ ሶራ ሶራ፣ ኪያዳ፣ ኢቦንጎ፣ወሃለ ባይ…. እያሉ የጎሳ ፖለቲካውን ከኢህአዴግ ንድፈ ሀሳብ መፀሀፍና መፅሄቶች ገልብጠው፤ ወደ ግጥም አስቀይረው፣ ዜማ ገዝተው (አንዳንዴም መንትፈው) ይዘፍኑልሀል፡፡ ዘፍነው ብቻ አያበቁም፤ በእጅም በእግር ብለው ከተዘፈነላቸው ክልሎች ልክ እንደ ቡሄ ሽልጠ መሬትን የሚያህል ነገር ተሸልመው ‹‹አመት አውደ አመት… ድገምና አመት›› ይሉልሀል፡፡ ያውም ለዚህ ከፋፋይ ስራቸው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህማ ብሶባቸዋል፡፡ ስለሀገር አንድነት፣ ስለአንድ ህዝብ፣ ስለኢትዮጵያዊነት…እንኳን ሊዘፍኑ፣ አያስቡትም፡፡ ድንገት አጀንዳው ቢነሳ እመነኝ ‹‹ጎመን በጤና›› ወይም ‹‹ፖለቲካና ኮረንቲ…›› ሲሉ ትሰማቸዋለህ፡፡ እስቲ እንደው ‹‹አንድ ሀገር፣ አንድ ህዝብና አንድ ባንዲራ›› ማለት በየት ሀገር ነው ገዥውን ፓርቲ እንደመቃወም ተቆጥሮ የሚያሸማቅቀው? ብቻ ይቅር፤ ሁሉን ቢያወሩት…

የሆነ ሆኖ የዛሬው አጀንዳችን ከነገ በስቲያ የተመሰረተበትን 37ኛ አመት የሚያከብረው ሕዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይን (ሕወሓትን) ከመሰረቱት አስራ አንድ ሰዎች ውስጥ አንዱ በእናቱም በአባቱም አማራ ስለመሆኑ መዘከር በመሆኑ ወደዛው እንለፍ፡፡

በመጀመሪያ ለመግባባት ይረዳን ዘንድ ቼ ጉቬራ ማነው? የሚለውን እናስቀድም፡፡ ደህና! ይህ ሰው እ.ኤ.አ በ1928ዓ.ም ሮዛሪዮ በምትባል አንዲት የአርጀንቲና ከተማ ተወለደ፡፡ ወላጆቹ ያወጡለት ሙሉ መጠሪያ ስሙ አርነስቶ ጉቬራ (Ernesto Guevara) ይሰኛል፡፡ ጉቬራም እድሜው ለትምህርት ደረሰ እናም ተማረ፤ ተመራመረ፡፡ በህክምናም ከቦነስ አይረስ ዩንቨርስቲ ዲግሪውን አገኘ፡፡

ዶ/ር አርነስቶ ጉቬራ በህክምናው አለም ለመሰማራት ወደጓቲሚላ ሄደ፡፡ በጓቲማላም በአንድ ሆስፒታል ተቀጥሮ እ.አ.አ እስከ 1954 አገለገለ፡፡ ሆኖም በ1954ዓ.ም ሶሻሊስቱ የጓቲማላው ፕሬዝዳንት ጃኮቦ አርቤንዝ (Jacobo Arbenz) በአሜሪካ አቀነባባሪነት በመፈንቅለ መንግስት ከስልጣኑ ሲባረር፣ ገና ከተማሪነቱ ጀምሮ የሶሻሊዝም አቀንቃኝ የሆነው ጉቬራ በቀጥታ ወደሜክሲኮ ተሰደደ፡፡ ነገር ግን በሜክሲኮ ከሚገኙ ሆስፒታሎች በአንዱም ስራ ይቀጠር ዘንድ አላመለከተም፡፡ ይልቁንም ከጥቂት ኩባውያን አብዮተኞች ጋር ጓደኝነት መሰረተ፡፡ ከእነዚህ ኩባውያን አብዮተኞች የአንደኛው ስም ፊደል ካስትሮ ይሰኛል፡፡

ጉቬራ እና ካስትሮ የነፍስ ትስስር ፈጠሩ፡፡ እናም ከሁለት አመት በኋላ (እ.አ.አ በ1956) ሁለቱ አብዮተኞች ሌሎች ስምንት ሴት እና ወንድ ወጣት አብዮተኞችን አስከትለው፣ ለታላቅ አብዮት፣ ለታላቅ ነውጥ ኩባ ገቡ፡፡

ኩባ ከገቡ ከጥቂት ቀናት በኋላ የጄነራል ፉሌንሶ ባቲስታ (Fulgencio Batista) መንግስት ላይ መፈንቅለ መንግስት አደረጉ፡፡ ሆኖም ሙከራቸው ከሸፈባቸው፡፡ ይህ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራም የሐምሌ ሃያ ስድስቱ ንቅናቄ (July 26 Movement) በመባል ይታወቃል፡፡

የፍንቀላውን መክሸፍ ተከትሎ እነካስትሮ አስራ ስድስት ሆነው፣ አስራ ሁለት አሮጌ ጠመንጃዎችን በማንገብ ወደበረሀ ገቡ-ሳይራ ማስትራ በረሀ፡፡

ምሽጋቸውንም ሳይራ ማአስትራ (Sierra Maestra) ተራራ ላይ አድርገው ከባቲስታ መንግስት ጋር መፋለማቸውን ቀጠሉ፡፡ በዚህ ወቅትም ኩባውያን አብዮተኞች ከባእድ ሀገር መጥቶ፣ በደምና ስጋ ለማይዛመደው ህዝብ ደሙን የሚያፈሰውንና አጥንቱን የሚከሰክሰውን አርጄንቲናዊ አብዮተኛ በራሳቸው ቋንቋ ‹‹ቼ›› ሲሉ የበረሀ ስም አወጡለት፡፡ ትርጓሜውም ‹‹የእኛ›› ማለት እንደሆነ ነገሩት፡፡

ትግላቸውም ጋመ፡፡ የመንግስት ወታደሮችም በደፈጣ ተዋጊዎቹ በእነቼ ከባድ ጉዳት ይደርስባቸው ጀመረ፡፡ ጥቂት የማይባሉ ከተሞችንም ነፃ ማውጣት ቻሉ፡፡ ነፃ በሚያወጧቸው ከተሞችም ለገበሬው መሬት እያከፋፈሉ ወደሀቫና ገሰገሱ፡፡ በድል ላይ ድል እያገኙም በጃንዋሪ 9 ቀን እ.አ.አ 1959ዓ.ም ሀቫና ከተማን ተቆጣጠሩ፡፡ አዲስ የሶሻሊስት መንግስትም መሰረቱ፡፡

ፊደል ካስትሮ የኩባ ፕሬዘዳንት ሲባል፤ አለም አቀፍ አብዮተኛው ቼ ጉቬራም የኢንዱስትሪ ሚንስትር ሆኖ ተሾመ፡፡ እ.አ.አ ከ1961-65 ድረስ ኩባን ካገለገለ በኋላ አፕሪል 15 ቀን 1965 በራሱ ፍላጎት ስልጣን ለቀቀ-ቼ፡፡ ስልጣን ከለቀቀ በኋላም በቀጥታ ወደቦሊቪያ ሄዶ የቦሊቪያ አብዮተኞችን ተቀላቀለ፡፡ ነገር ግን እ.አ.አ በ1967ዓ.ም በቦሊቪያ መንግስት ወታደሮች ተማርኮ በዛው አመት ኦክቶበር 9 ቀን ተገደለ፡፡ ቼ ጉቬራ ማለት ይሄ ነው፡፡ ፋኖ ተሰማራ

እንደ ቼጉቬራ
ታሪክ ልትሰራ

ማለትም ይህው ነው፤ ሌላ አይደለም፡፡ ቼ ጉቬራ፣ ቼ ጉቬራ፣ ቼ ጉቬራ፣ ቼ ጉቬራ…ቼ ጉቬራ፣ ሀገሩ ቬትናምን ከአሜሪካ ነፃ ካወጣው አጐት ሆ ቼሚኒ ጋር ስሙና ስራው ለኢትዮጵያውያን አብዮተኞችም አርአያ ሆነ፡፡ እናም በ1966ቱ ታለቁ የኢትዮጵያ አብዮት ዋዜማና ማግስት፣ ያ ትውልድ

ፋኖ ተሠማራ ፋኖ ተሠማራ
እንደ ሆ ቺሚኒ እንደ ቼ ጉቬራ

እያለ በመዘመርም ድፍን የሀበሻን ምድር አጥለቀለቀው፡፡ ተራሮች እና ኮረብቶችም ‹‹…እንደ ቼ ጉቬራ…›› በሚል ህብረ ዝማሬ ተንቀጠቀጡ፡፡ ተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ፡፡ የዚህ ትውልድ አካል የሆኑት የትግራይ ልጆችም ለትግራይ ነፃነት በረሀ ገቡ፡፡ እናም ህወሓት የሚባል ድርጅት መስርተው ተራራውን አንቀጠቀጡ፡፡ ከእነዚህ መስራቾች እና መሪ ተራራ አንቀጥቃጮች ወይም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ የትግራይ ተወላጅ አይደለም፡፡ የአማራ

ወደ ገፅ 6 ዞሯል


# ‹‹ምዕራባዊት›› እና ‹‹ያልታበሱ ዕንባዎች››



- በደራሲ አሰፋ በቀለ ገ/የሱስ ተፅፈዋል!
- ልዩ ታሪክ በልዩ አተራረክ ይዘው ቀርበዋል!
- በኢትዮጵያዊ ህይወትና አኗኗር ትክሳት ተሞልተዋል
- ሰው ሰው ይሸታሉ!
- አይረሴ ገፀ ባህሪያቱ የማይረሳ መልዕክት ለርሶ ያስተላልፋሉ!
- በሚያነቧቸው ጊዜ የተጣፉበትን ወረቀት ረስተው ለባለ ታሪኮቹ ብቻ ይጨነቃሉ!
- ከጀመሯቸው ሳይጨርሱ አይለቋቸውም!
- ልክ እንደጨረሷቸው በረጅሙ ይተነፍስና ታሪኩን እንደገና በአዕምሮዎት ለማመላለስ ይገደዳሉ፤ በታሪኮቹ ውስጥ እርስዎም ይገኙባቸዋልና!
- ከእነዚህ እውንታዎች በመነሳት እርስዎም ለመጽሐፍቱ ጊዜ አይሽሬነትና ዘመን ተሻጋሪነት ቋሚ ምስክር ይሆናሉ!!



‹‹ያልታበሱ ዕንባዎች›› ለ4ኛ ጊዜ፤ ‹‹ምዕራባዊት›› ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለ2ኛ ጊዜ ታትመው ሰሞኑን በመላ ሀገሪቱ እየተሰራጩ ነው፡፡ ይፈልጓቸው! አንዴ ከአነበቧቸው እድሜ ልክዎን ሲናፍቋቸው ይኖራሉ!!

# የአመክንዮ ስሜታዊነት ፍልስፍናዎች



## ውድ ዶ/ር አድለር

በምክንያታዊነት እራሳችንን እንድንገዛና በስሜታዊነት እንዳንነዳ ምክር ይቀርብልናል። የዚያኑ ያህል ደግሞ ስሜታችንን አፍነን እንዳንይዝ÷ እንደዚያ ካደረግን የአእምሮ መቃወስ እንደሚደርስብን ይነገረናል። የትኛውን እንቀበል? ስሜታችንን ነፃ እንልቀቀው ወይስ እናቅበው? ምክንያታዊነታችንንና ስሜታዊነታችንን አጎዳኝተን ለመቀጠል ምን ማድረግ ይኖርብን ይሆን?

ዲ.ኤስ

## ውድ ዲ.ኤስ

እስከ አስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ስሜታዊነት ስንል ቃሉ የሚያመለክተን ነገር አለ። ከፍተኛ የፍርሃት÷ የፍቅርና የደስታ ስሜት ሲያድርብን÷ እንዲሁም መቆጣጠር ተስኖን ይሄንኑ ለማንፀባረቅ ስንገደድ ያኔ ስሜታዊ ሆንን ማለት ነው። ቅጥ ባጣ ሁኔታ መደነቅና መፈንደቅ አመክንዮ (ምክንያታዊነት) ለመኖሩ ማረጋገጫ የሆኑትን ፅሞና÷ ሚዛናዊነትና መረጋጋት የሚቃረን ድርጊት ነው። ብዙ ታላላቅ ፀሐፍት ምክንያታዊነትን በማነፃፀር የተለያዩ ፅንሰ ሐሳቦችን አቅርበዋል። አመክንዮ እና ስሜታዊነት በህይወታችን ውስጥ ያላቸው ትክክለኛ ሚና ተተንትኖ የቀረበባቸው ፅንሰ ሐሳቦች ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶች ያንፀባርቃሉ። 1. አመክንዮ ስሜታዊነትን ሊገዛው ይገባል። 2. አመንክዮ ስሜታዊነትን ጨርሶ ሊያስወግደው ይገባል እና 3. ስሜታዊነት አመክንዮን ሊገዛው ይገባል የሚሉ ናቸው።

አርስቶትልና ኘሌቶ የመጀመሪያውን አመለካከት ያንፀባርቃሉ። ለእነሱ አመክንዮ ተገቢ ፍርድ ሰጪና ወደ ትክክለኛ የህይወት ግብ የሚመራ ለሰው ልጅ ብቻ የተቸረ ባህሪይ ነው። ለእነዚህ ታላላቅ ፈላስፎች ስሜታዊነትም ለሥነ-ምግባር እውን መሆን አስፈላጊ ሚና አለው። በዚህ አመለካከት ስሜታዊነት በአመክንዮ እስከተመራና መዳረሻ ግቡ መልካም ፍፃሜ እስካለው ድረስ ጥሩ ነው። ለአርስቶትል እንደ ውጤታማነትና ፅኑ ፍላጎትና ትጋት ያሉ ከስሜት የሚመደቡ ሰዋዊ ጠባያት ቢሆኑም በአመክንዮ ትዕዛዝ እስከተመሩ ድረስ ለሥነ-ምግባር ተፈፃሚት ተገቢና አስፈላጊዎች ናቸው።

ሁለተኛው አመለካከት እንደ ኢፒክተተስ እና ማርኮስ አውራሊየስ ባሉ የስቶይክ (Stoic) ፈላስፎች የሚቀነቀን ነው። ስሜታችንን ማስወገድ እስከቻልን ድረስ መጨቆን ተገቢ እንደሆነ በእነዚህ ፈላስፎች ይነገራል። በምንም አይነት ሁኔታና በእንዴትም አይነት ጉዳይ ቢሆን የደረሱብንን ነገሮች በስሜት ለመግለፅ ከመሞከር መታቀብ እንደሚኖርብን እነዚህ ፈላስፎች ያስረዳሉ። የምናፈቅረው ሰው ቢሞት ወይም እኛ ላይ ልንቋቋመው የማንችለው መከራ ሊወርድብን ይችላል። በዚህ ሁኔታ ስሜታዊነታችንን ልንቆጣጠረው እስካልቻልን ድረስ ሥነ-ምግባራዊነታችን በነበረበት ሁኔታ ቀጥሏል ማለት እንደማይቻል ለስቶይኮቹ ፈላስፎች ያስረዳሉ። ጥልቅ ስሜት ሆነ የስሜታዊነት ሙላት ካልተቆጣጠሩት በስተቀር ነፃ ሥነ-ምግባራዊ ህይወት አለን ማለት እንደማያስችለን ይናገራሉ።

በዘመናዊው ዓለም ጀርመናዊው ኢማኑኤል ካንትም ከሞላ ጎደል ይህንኑ የስቶይኮችን አመለካከት ያራምዳል። ትክክለኛና መልካም አላማ በስሜታዊነት ሊዋጥና ሊደናቀፍ አይገባም የሚል አቋም ነበረው። ሃላፊነት በራሱ በምክንያታዊነት የተመረመረ ሥነምግባራዊ ልቀት ነው። የስሜታዊነት ውጤት የሆኑት ያልተገራ ሐዘንና ቅጥ ያጣ ደስታ ሥነ-ምግባራዊው ንፍቀ ክበብ ውስጥ ስፍራ አይኖራቸውም።

ሦስተኛውና የመጨረሻው አመለካከት ስሜታዊነትን ከአመክንዮ አብልጦ የሚመለከተው በዋነኛነት የዘመናዊው ዓለም አቋም ነው ማለት ይቻላል። በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበሩት ጀርመናዊዎቹ የሮማንቲክ ሥነ-ፅሁፋዊ ዘውግ አራማጆቹ እንደ ስኪሊንግ፣ ሺለርማርሸር እና ኖቫሊስ ያሉት በዚህ አመለካከት አራማጅነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ ደራሲዎች ለህይወት ምልአት ሆነ ለዕውቀት መዳረሻ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ስሜታዊነትና ምናብ እንደሆነ አቋም ይዘው ተከራክረዋል። ለሰው ልጅ ህልውናዊ ጥያቄዎች የተገናዘበ አመክንዮአዊ ምላሽ ማቅረብ የተሳሳተ አቅጣጫ የመጠቆም አዝማሚያ እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንግሊዛዊው ባለቅኔ ዊልያም ብሌክ ተመሳሳይ አቋም ያራምዳል። በሳይንስና በቴክኖሎጂ ሳቢያ የሰው ልጅ የሚከተለው ቁጥር የተሞላ ህይወትና አመክንዮአዊ እሳቤ ላይ የከረረ ተቃውሞ አለው።

የሲግማን ፍሩድ አመለካከት ከሦስቱም አቋም ጋር የማይኳኳን ሆኖ ተገኝቷል። እንደ ግሪኮቹ ፈላስፎች ሁሉ የህይወትን ግብ ለማሳካት ስሜት በቁጥጥር ስር መዋል አለበት ይላል። ነገር ግን የእሱ እሳቤ ትኩረቱን የጣለው ከስነ ምግባር ይልቅ አካላዊ ጉዳዮች ላይ ነው። በዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ስሜታዊ ፍላጎቶችን አመጣጥኖ ለመኳዝ ህይወት ለሰው ልጅ ዋስትናና ውጤታማነት እንደ ቃል ኪዳን የሚቆጠር ነው ይላል። በሌላ በኩል ደግሞ ስሜትን አፍኖ መያዝ የአእምሮ መቃወስን ሊያስከትል እንደሚችል ያስተምራል። ስለዚህ ለገዛዳዊው ተፈጥሮአዊና ማህበራዊ ሁኔታ ስሜትን ልቅ ሳይተዉ÷ ጨቁነውም ሳይዙ አመጣጥኖ መጠቀም ተገቢ እንደሆነ ከፍሩድ አስተምህሮ እንረዳለን።

# አማራው የህወሓት... ከገፅ 5 የዞረ

ተወላጅ ነው። ሆኖም እስከዛሬ ድረስ አንዳቸውም የህወሓት አመራሮች ስለዚህ ጉዳይ ትንፍሽ ብለው አያውቁም። ህወሓትን ከመሰረቱት ውስጥ ሙሉ በሙሉ አማራ የሆነ አንድ ሰው አለበት መባሉ በፍፁም በታሪካቸው እንዲካተት አይፈልጉም። ዛሬ ግን ይህን ያልተሰማ ዜና ለመስማት በጥፍራችው ቁሙ።

በእርግጥም ከነገ በስቲያ በሚከበረው የህወሓት ምስረታ 37ኛ አመት ላይ ታሪኩ ስለማይነገርለት፤ እንዲሁም ያለፉት 36ት አመታዊ የድርጅቱ በአል ሲከበር ሽራፊ ታሪኩ ተነግሮለት ስለማይታወቀው አማራው ቼ ጉቬራ ልነግራችሁ ነው። መቼም ይህ ዜና የትግራይ ህዝብን ሲያስደስት፣ የታሪክ ‹‹ፎቢያ›› ላለባቸው የህወሓት ሰዎች ‹‹ኳክብት ይርገፉ፣ ፀሀይ ትጨልም፣ ጨረቃም አትድመቅ...›› ቢሆንም መነገር አለበትና እናገራለሁ።

በኦርቶዶክስ የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ አንድ ታላቅ በአለ ንግስ አለ። በየዓመቱ በህዳር 21ቀን የሚከበረው የአክሱም ማርያም። ታቦተ ጽዮን እንዳለ በሚነገርባት በአክሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን ከአራቱም አቅጣጫ፣ የመጡ የእምነቱ ተከታዮች ይሠባሠባሉ። ያን ጊዜም አክሱም ሞልታ ትፈሳለች፤ በሰው ጎርፍ ትጥለቀለቃለች።

...እለቱ ህዳር 21 ቀን ነው። አመቱ 1967 ዓ.ም። ‹‹በትግራይ ህዝብ ላይ እየደረሠ ያለው የአማራ ጭቆናን እና ቅኝ አገዛዝን ከዚህ በላይ መሸከም አንችልም›› ያሉ ወጣቶች ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ (ማገብት) በሚል መጠሪያ ስም የመሰረቱትን ድርጅት የፖለቲካ ፕሮግራም፣ በዚሁ እለት ታቦት ለማንገስ ለተሰባሰበው ምዕመናን በተኑት። ይህ ከሆነ ከሶስት ወር በኋላ ማገብቶች፣ የደርግ መንግስትን ለመፋለም አስራ አንድ ሆነው በረሀ ገቡ። ከሽሬ ከተማ በስተምዕራብ በ80 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘው ደደቢት በረሃ።

የተወለደው በ1929 ነው። ቼ ጉቬራ በተወለደ በአመቱ። ይህ ሰው ልክ እንደ ቼ ጉቬራ ከኢትዮጵያ ከተሞች በአንዱ የገጠር ከተማ ተወለደ። ከመሀል አዲስ አበባ 774 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ጎንደር ክፍለ ሀገር። በእርግጥ የትውልድ ከተማው ከጎንደር ከተማም 118 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች-ድብ በሐር።

በደባርቅ ወረዳ የምትገኘው ድብ በሐር ከተማ ከአምስት ሺ በላይ ሰዎች እንደሚኖሩባት ይነገራል። በፍራፍሬ፣ ጫት እና ዋንዛ እንጨት ምርቷም ትታወቃለች-ድብ በሐር። ለከተማው አንድ ለእናቱ ከሆነው ድብ በሐር አንደኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስተቀር ምንም አይነት ትምህርት ቤት የለም። ይህች የገጠር ከተማ በአመት ሁለቴ ትደምቃለች። በአብዛኛው ነዋሪዎቿ ዘንድ በሚከበረው የድብ በሐር ጊዮርጊስ ደብር ንግስ እለት።

የድብ በሐር ከተማ በርካታ ሰዎች በደርግ የግፍ አገዛዝ ከተወረወሩበት ሊማሊሞ ገደል ስር ትገኛለች። በህወሓት ታሪክ ውስጥም ጉልህ ስፍራ ሊይዝ የሚገባውን፤ ነገር ግን አመድ አፋሽ የሆነ አንድ ሰው አፍርታለች። ከላይ በተጠቀሰው ቀን የተወለደውን-አብተው ታከለን።

ስለአብተው የልጅነት ታሪክ የተፃፈ ነገር ባለመኖሩ ብዙ ማለት አይቻልም። ለነገሩ እንኳን የልጅነት ታሪኩ ቀርቶ የመሰረተው፣ የታገለለት፣ የሞተለት፣ የቆሰለለት፣ የወጣለት፣ የወረደለት... ድርጅትም ታሪኩን አልዘከረለትም።

የሆነ ሆኖ አብተው ከደብ በሐር በ100 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው የሽሬ ከተማ ሄደ። ኑሮውን በዛው አደረገ። የሽሬ ከተማ ግምጃ ቤት ሀላፊ የሆኑትን የባላባራስ አፅባሀ ልጅ ወ/ሮ አለም አፅበሀንም አግብቶ ሶስት ጉልቻ መሰረተ። ባለንባራስ አፅበሀ የሌላኛው የህወሓት መስራች ስሁል አየለ (ገሠሠ) አጎት ናቸው። ይሄ ሁኔታም አብተው እና ስሁል እንዲቀራረቡ መንገዱን ከፈተላቸው። እናም ከእለታት አንድ ቀን የትግራይ ህዝብን ከአማራ ጭቆና ለማላቀቅ እና ነፃይቱን ትግራይ ለመፍጠር ድርጅት መመስረቱ አስፈላጊ እንደሆነ ተወያዩ፤ አብተው ምንም እንኳ አማራ ቢሆንም፤ ‹‹የተጨቆነ ካለማ...›› ሲል ለመታገል ወሰነ። እናም ከሌሎች 10 የትግራይ ልጆች ጋር በመሆን ስድስት አሮጌ መሳሪያ ታጥቀው ወደ ደደቢት በረሃ አመሩ። ቼ ጉቬራም ከአሰራአምስት ኩባውያን እና ከአስራሁለት አሮጌ መሳሪያ ጋር አይደል እንዴ ሲይራ ማስተራ በረሀ የገባው። እናም በደደቢት በርሀ ህወሓትን መሰረተ። በእርግጥ አብተው ቼ ጉቬራ የሚሆነው ከህወሓት የምስረታ ታሪክ ስንነሳ ነው። ምክንያቱ ደግሞ በህወሓት ታሪክ አፃፃፍ ህግ መሰረት አብተውን አማራ የሚባል ‹‹የሌላ ሀገር ሰው›› ሆኖ ስለምናገኘው ነው። የውም በህወሓት የታሪክ አረዳድ ‹‹በቅኝ አገዛዝ›› ስር እያማቀቁን ነው ተብለው ከተከሰሱት የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የማህብረሰብ ክፍል መገኘቱ ቼ ጉቬራነቱን ያጎላዋል። ልክ ቼ ጉቬራ የአርጀንቲና ሰው ሆኖ ለኩባውያን ታግሎ፣ ለቦሊቭያውያን እንደሞተው ማለት ነው።

ከህወሓት የፈጠራ ታሪክ ከወጣን ግን የአብተው በደደቢት መገኘት አስገራሚ አይሆንም። ቼ ጉቬራም አያሰኘውም። ምክንያቱም አስራ አንዱም በደም የተሳሰሩ ኢትዮጵያውያን ናቸውና። አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ጉራጌ... ለአብተው ታከለም ሆነ፤ ለአስገደ ወ/ስላሴ አሊያም ለስዩም መስፍን የተለየ ትርጉም ሊኖረው አይችልም። የአብተው ቼ ጉቬራነት ለህወሓት ብቻ ነው። እንዴት ብሎ? የሚጠይቅ ካለ መልሱ ግልፅ ነው፤ የትግራይ ህዝብ ህወሓት በሚለው ታሪክ አይስማማም የሚል።

ህወሓት የኢትዮጵያ ታሪክ የ100 ዓመት ታሪክ ነው ይልሃል። ነገር ግን ከህወሓት ውጭ ያለ የትግራይ ተወላጅን ብትጠይቅ ፍርጥም ብሎ ‹‹ሀገሬ ኢትዮጵያ የሶስት ሺህ አመት ታሪክ አላት›› ይልሃል። ህወሓት በረሀ የገባው ‹‹ትግራይ ለብቻዋ ነፃ አገር ነች እንጂ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም›› በሚል ነው። አሁንም ከህወሓት አመራር ውጪ ያለውን የትግራይ ተወላጅ ስለዚህ ሁኔታ ብትጠይቀው ጤንነትህን ይጠራጠረዋል። ለኢትዮጵያ ዳር ድንበርም አጥንታቸውን የከሰከሱ፣ ደማቸውን ያፈሰሱ እልፍ አላፍት የትግራይ ሰዎችንም ታሪክ ይነግርሃል። ከዚህም አኳያ ነው አብተው ለትግራይ ህዝብ ወንድም፤ ለህወሓት ግን ‹‹ከባእድ ሀገር›› የመጣ ቼ ጉቬራ የሚሆነው።

እነዚህ አስራ አንድ የመጀመሪያው በረሃ የገቡ ታጋዮች በስም ስንዘረዝራቸው ስሁል አየለ (ገሰሰ)፣ አረጋዊ በርሀ፣ ስዩም መስፍን (አምባዬ)፣ ግደይ ዘርአፅዮን (ፋንታሁን)፣ አጋዚ ገሰሰ (ዘርኡ)፣ አስፋሐ ሐጎስ (ሙሉ)፣ ፀሀዬ ካሕሳይ (አረፈአይኔ)፣ ምስጋና ቡርሀ (ካሕሳይ)፣ ቀለበት ታዬ (ንጉሴ)፣ አስገደ ወ/ስላሴ ( ወ/ሚካኤል) እና አብተው ታከለ (ሚካኤል) ይባላሉ። እነዚህ ሰዎች የህዝባዊ ወያኔ አርነት ትግራይ መስራቾች ናቸው። ነገር ግን ከእነሡ አንዱ የትግራይ ተወላጅ እንዳልሆነ እየነገርኩ ነው። አማራ ነው። ስሙም ተጋዳላይ አብተው ታከለ ይባላል፤ ደደቢት በረሃ እብረውት የገቡ ጓደኞቹ ደግሞ ‹‹ሚካኤል›› ሲሉ ሰየሙት። አርንስቶ ጉቬራን ኩባውያን ‹‹ቼ-የእኛ›› ሲሉ እንደሰየሙት ሁሉ፣ የህወሓት መስራቾቹም አብተውን ከዋነኞቹ የመላዕክት አለቃ በአንዱ ስም ሰየሙት-ሚካኤል።

የሆነ ሆኖ ህወሓት የአብተውን መስዋትነት ብቻ አይደለም የካደው፤ በርካታ የኢትዮጵያን ታሪክም እንጂ። የአፄ ኃይለ ሥላሴን ታሪክም ከአፍሪካ ህብረት ድርጅት ዋነኛ መስራችነት ታሪክ መፋቅም አንዱ የኢህአዴግ የታሪክ ግጭት ነው። ለምሳሌ ህወሓት ታሪክን ለመካድ ችግር እንደሌለበት ለመረዳት ሩቅ ሳንሄድ ጥር 27 ቀን 2004ዓ.ም በአሜሪካ ሬዲዮ ጣቢያ ትግርኛ ፕሮግራም ላይ የቀድሞ ሁለቱ የህወሓት ሊቀመንበሮች ዶ/ር አረጋዊ በርሄ እና አቦይ ስብሓት ነጋ የተከራከሩትን ክርክር በጥቂቱ እንየው። የክርክሩ መነሻ በቀድሞ የህወሓት የስለላ ሀላፊ የተፃፈው ‹‹ፍኖተ ገድል›› መጽሐፍ ሲሆን፤ መጽሐፉ የአክሱም ታሪክ የትግራይ ህዝብ ብቻ ነው ማለቱ ነው ለውይይት እንዲቀርብ ያስቻለው። መጀመሪያ አረጋዊ በርሄ የአክሱም ታሪክ የትግራይ ብቻ ሳይሆን፣ ከላይ ከቀይ ባህር ጀምሮ ድፍን ኢትዮጵያን አካሎ እስከ ሱዳንም የሚደርስ እንደሆነ አብራራ። አቦይ ስብሓት ግን ይህንን ማብራሪያ አምርረው ተቃወሙ። ተቃውሞአቸውንም በትግርኛ እንዲህ ሲሉ ገለፁ

‹‹ነቲ ፅሁፍ ግን ከም ባግራውንድ ካብ ትግራይ ወፃኢ ካብ ኤርትራ ወፃኢ ንኻልእ ከምዘልአልካየ፤ ንጋምቤላ፣ ንኻልዕ ዝሐውስ አይኮንን አክሱም። ትግራይ እውን ሙሉእ ትግራይ ዝሐውስ አይመስለንን። ተምብየን አካል ናይ አክሱማይት ኢምፓየር ዶ ነይሩ ዝብል ሕቶ አለኒ። ኢሸን ዓጋመ ነይሩ ዶ? አብ ሓደ አጋጣሚ ፐርፐለስ ኦፎ ዘ ኤርትርያን ሲ ዘብል ናይ ዓጋመ ስይም ዝብል አብኡ ሪኤ፤ ስያሞ አበይ እዩ እንተበልኩ ዓጋመ እዩ ኢሎምዎ በቲ ናይ ቀደም አፀዋውዓ ንሱዋን ፓርት ኦፎ አክሱማይት ከምዘይነበረ እየ ተረዲአ።›› (ይህ ፅሁፍ እንደ መነሻ ሲወሰድ አንተም እንዳነሳከው ከትግራይና ከኤርትራ ውጭ ጋምቤላና ሌላውንም የሚያጠቃልል አይደለም አክሱም። ወደ ትግራይም ስንመጣ አሁን ያለውን ትግራይ በሙሉ የሚጨምር አይመስለኝም ተምቤን የአክሱማይት ኢምፓየር አካል ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ አለኝ። አጋሜስ ነበር ወይ? በአንድ አጋጣሚ ፐርፐለስ ኦፍ ኤርትራ መጽሐፍ ላይ የአጋሜ ስያሞ የሚል አየሁ። ስያሞ ማለት ደግሞ አጋሜ ነው ብለውታል። እናም አጋሜ የአክሱም አካል እንዳልሆነ ተገነዘብኩኝ)

መቼም ይህ የጤና አይመስለኝም። እንግዲህ የአክሱም ታሪክን ከመላው ኢትዮጵያ ከመንጠቅም አልፈው፤ መላው የትግራይ ህዝብንም አይወክልም ማለት ምን ማለት ይሆን?

በአቦይ ስብሃት የታሪክ ትርክት መሰረት አክሱም የኢትዮጵያ አይደለም። ከትግራይም ተንቤን እና አጋሜ አውራጃን የአክሱም ታሪክ አይመለከታቸውም። ግዙፉ የአክሱም ኢምፓየርም በህወሓት ዕውቀት ጠቦ፣ ጠቦ፣ ጠቦ...ከአንድ ቀበሌ የማይበልጥ ሆነ።

ይህን በመሰለው ትምክት ነው አብተው ታከለም ከህወሓት መስራቾች ታሪክ ዝርዝር ውስጥ የተደለዘው ወይም መስዕዋትነቱ የተነጠቀው። በእጅጉ የሚያስገርመው ትግራይ በቆመው የሰማዕታት ሀውልት ላይ የአስሩ መስራቾች ስም እና ፎቶ አለ። የአብተው ታከለ ግን ስሙ አለ፣ ፎቶው የለም። ይህ ሰው ፎቶ የለውም እንዳይባል ደርግ ከወደቀ በኋላም በህይወት ነበረ። እስከ 2000ዓ.ም በጎንደር ደባርቅ፣ ደብ በሐር ከተማ ከባለቤቱ ጋር ይኖር ነበር። የአራት ልጆችም አባት ነው። ህይወቱ ያለፈውም በአንጀት ድርቀት ተሰቃይቶ ነው። በ1999ዓ.ም መታከሚያ ገንዘብ አጥቶ ወደ መቀሌ ሄደ፣ በመቀሌም አቶ አስገደ ገ/ስላሴ እና ጉዳዩን የሰሙ የመቀሌ ነዋሪዎች ገንዘብ አዋጥተው ከመቀሌ ሆስፒታል ዶ/ር ኬዳኔ ጋር ተባብረው አሳከሙት። ለሁለት ወር ያህልም አቶ አስገደ ቤት ካረፈ በኋላ ወደ ትውልድ መንደሩ ጎንደር ድብ በሐር ተመለሰ። በትውልድ መንደሩም ከድህነት የተነሳ የሚንከባከበው አጥቶ ህይወቱ አለፈ። ያ የህወሓት ቼ ጉቬራ። የሰራው ታሪክ የሌላ ብሄር ተወላጅ በመሆኑ ብቻ ተቀበሮ እንዲቀር የተፈረደበት- ቼጉቬራ።

በእርግጥ ህወሓት የአብተው ታከለን ታሪክና አማራነት ስለምን መደበቅ አስፈለገው? የሚለው ጥያቄ ዛሬ ብቻ ሳይሆን በቀጣዩ ትውልድም የሚነሳ ይመስለኛል። ከህወሓት መስራቾች ውስጥ የተወሰኑት መጽሐፍ ፅፈዋል። ለምሳሌ አረጋዊ በርሄም ሆነ ግደይ ዘራፅዮን በመጽሐፋቸውም ሆነ ቃለ ምልልስ በሚሰጡበት ጊዜ ወይም የህወሓትን የትግል ታሪክ የፃፉ ልሂቃኖች ስለአብተው አማራነት ነግረውን አያውቁም። የብአዴን መስራቾችም ስለዚህ ጉዳይ ሲያነሱ አልተሰሙም። ስለማያውቁ ነው እንዳይባል ያውቃሉ። ምናልባት ህወሓት የጠላውን መጥላት፣ ህወሓት የወደደውን መውደድ የሚለው ያልተፃፈው የህወሓት ህግ አስሮአቸው ሊሆን ይችላል።

# በዕውቀት መሻታችን ላይ የተልኮሰኮሰው ፖለቲካችን እንዳያጠላበት ቁንጽልነትን እናስወግድ!

## የሃበሻ ጀብዱ ትርክት እንደማሣያ



በብርሀኑ ደቦጭ

ርዕስ ፦ የሃበሻ ጀብዱ
ጸሐፊ፦ አዶልፍ ፓርለሳክ
ተርጓሚ ፦ ተጫኔ ጆብሬ መኮንን
አሣታሚ፦ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ
የታተመበት ዓ/ም፦ 2010 እኤአ
ገጽ፦-349

ስትገመግም ጸሐፊው የጻፈውን መጽሐፍ እንጂ አንተ ጸሐፊው እንዲጽፈው የምትፈልገውን መጽሐፍ እንዳይሆን ተጠንቀቅ የሚለው የግምገማ ስነምግባር ሀሁ መጽሐፍ ሲገመ¬¬¬ገም በተጻፈበት አውድ መሆን እንዳለበት ለማስገንዘብ ነው፡፡

በእርግጥ ‹‹ትክክለኛው የመጽሐፍ ትችት አካሄድ ይሄ ብቻ ነው›› የሚል ነገር የለም፡፡ በተፈጥሮው የመጽሐፍ ትችት ግለሰባዊ አቀራረብ ያመዝንበታል፡፡ የትችቱ አካሄድ ከተለያየ ማዕዘን ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ ከይዘት፣ ከቅርጽ/አወቃቀር ወይም ከአቀራረብ አንጻር ሊሆን ይችላል፡፡ በየማዕዘኑም ቢሆን የሚሰጠው አስተያየት ሳይቀር እንደተቺው ዳራ ሊለያይ ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ብዙ የመጻሕፍት ትችት ሁሉንም እንዲያስማማ የማይጠበቀው፡፡ ይህ ማለት ግን ማንም ደራሲው ያላሰበውን/ያላለውን እንዳለ/እንዳሰበ አድርጎ በማቅረብ፣ አለቅጥ በማጋነን፣ ለጥጦ እየተረጎመ በማዛባት፣ አለምክንያት በማጣጣል ወይም ስለመጽሐፉ በቅጡ ሳይረዳ ራሱ ተደናግሮ ሲያደናግር ግን የመጽሐፍ ሒስ ጤናማ ተፈጥሮውን ያጣል፤ ከአልሚነቱ አጥፊነቱ ይጎላል፡፡ ለዚህ አስተያየት መነሻ የሆነኝ በይኩኖ አምላክ አዲስ ጉዳይ ቅጽ 5 ቁጥር 105፣ 2004ላይ በየሃበሻ ጀብዱ ላይ የቀረበው አስተያየት ሲሆን ፍትህ ስለሁኔታው ለማጥራት ዕድል ስለሰጠችኝ ላመሰግናት እወዳለሁ፡፡

በመጽሐፍ ግምገማ የሚሰጡ ትችቶች ስለመጽሐፉ በቀላሉ ልንረዳ የማንችላቸውን ነገሮች እያሳዩን ጉድለቶችን ነቅሰው የሚያወጡልን እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ የይኩኖ ትችትም ስለጉዳዩ አስተያየት ለመስጠት ብቁ ነኝ ብሎ ካመነ ከአንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር የመነጨ ስለሆነ በቂ መረጃ፣ ሚዛናዊ ትችትና ገንቢ ድምዳሜ ላይ ሊያደርስ እንደሚችል ቢጠበቅ ብዙ ፈላጊ አያሰኝም፡፡

ደራሲው እንደይኩኖ አምላክ አቀራረብ ‹‹…ሥራ የማግኘት ተስፋ የተሰጣቸው ምስኪን ፈረንጅ…››፣ የመጽሐፉ ዋና ዓላማም ‹‹… የሃገሩ ልጆች ያላዩትን፣ ሊገምቱት የማይችሉትን የኋላ ቀርነት፣ የድንቁርና፣ የገጠሬነት ትረካ እያስገነዘበ ማዝናናት…›› የሆነና ከዚኽ ዓይነቱ ጸሐፊ እውነት እንደማይጠበቅ የሚመሰክር አንድምታ ያለው ነው፡፡ ስለዚህም ‹‹አታሚዎቻችን(አሳታሚዎቻችን ለማለት ይመስላል) ጊዜና ገንዘባቸውን ከማባከናቸው በፊት ስለሚመርጡት መጽሐፍ እንዲያስቡ…›› በማለት የመጽሐፉ መታተም ከጅምሩ የማይገባ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ ምንም እንኳን ይኩኖ አገር ወዳድነቱ አገብሮት የኢትዮጵያን ስም በክፉ ያነሳ ሁሉ ሊታገሰው እንደማይችል ባንጸባረቀበት የአስተያየቱ ክፍል ለትችቱ አንኳር መነሻ የሆነው ኢትዮጵያውያን ተሰደብን በሚል መሆኑን ቢያመላክትም ይህ አስተያየቱ ዝንፈት ያለበት መሆኑን በሦስት አንጓ ሥር አመለክታለሁ፡፡

### የሃበሻ ጀብዱ ከደራሲው ማንነት አንጻር፦

በቅድሚያ የሃበሻ ጀብዱ መጽሐፍን መበየን ያስፈልጋል፡፡ ይህ መጽሐፍ ከላይ በጠቀስሁት መንገድ በወቅቱ በኢትዮጵያ በአካል ለመገኘት የታደለው የአዶልፍ ፓርለሳክ የዓይን ዕማኝ ምስክርነት ነው፡፡ ባለቀለት የታሪክ ጥናትና በዓይን ዕማኝ ምስክርነት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አያዳግትም ብዬ ላሳብና ስለዓይን ዕማኙ አዶልፍ ፓርለሳክ ልቀጥል፡፡ ፓርለሳክ በኢንጂኒሪንግ በዲግሪና በኢኮኖሚክስ በማስትሬት ደረጃ የተመረቁ፣ በርከት ያሉ(12) ቋንቋዎችን የሚናገሩ፣ በአውሮጳ፣ እስያና አፍሪካ ብዙ አገሮችን የጎበኙ፣ ወደኢትዮጵያም ሁለት ጊዜ የተመላለሱ ናቸው፡፡ መጽሐፋቸው የሚያትተው ቁምነገርም ለሁለተኛ ጊዜ ወደኢትዮጵያ ተመልሰው የኢትዮጵያ ጦር መኮንነትን ተሸመው በካፒቴን ማዕረግ ከሰባት ወራት ላላነሰ ጊዜ በሰሜኑ የጦር ግንባር አዛዥ በነበሩት የራስ ካሣ ጦር ሥር ላለው የሰላሌው ዘማች አማካሪ ሆነው ያገለገሉበትን ዘመን የሚሸፍን ነው፡፡ በዚህም ወደግንባር ለመዝመት ከተደረገው ከመጀመሪያው እንቅስቃሴ ጀምሮ በምድርና በሰማይ በተሰለፈው የጣሊያን ጦር መሣሪያና ሥልጠና የበላይነት የኢትዮጵያ ጦር ተረትቶ ወደአዲስ አበባ የተደረገውን መልስ ጸሐፊው ፓርለሳክ ራሳቸው ካደረጉት፣ ካዩት፣ ከሰሙትና ካመሳከሩት አንጻር ያቋደሱን ሲሆን እራሳቸውም ከኢትዮጵያ የወጡበትን ሁኔታና ንጉሡ ወደስደት ሲሄዱ በጂቡቲ የነበረውን ሁኔታ አክለውበታል፡፡

እንዲህ ዓይነት መጻሕፍትን ለመገምገም፣ ለማንበብና በትክክል ቀልባቸውን ለመረዳት ባህሪያቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ከይኩኖ አቀራረብ የምንማረውም ይህን ጉዳይ በቅጡ አለማጤን የሚያመጣውን የአስተሳሰብ ጉድለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት ከውጪው ማኅበረሰብ ጋር ረዥም ግንኙነት አላት፡፡ የአገራቸውን መንግሥት በመወከል በዲፕሎማትነት፣ ለንግድ፣ ለሣይንሳዊ ጥናትና ምርመራ፣ ድንቃድንቅ ነገሮችን ለመጎብኘት ጉዞ በማድርግ፣ ለስለላ፣ ለሥራ ፍለጋ፣ ለሰብአዊ እርዳታ፣ ለኃይማኖታዊ ተልእኮ፣ ለቅኝ ገዢነት፣ ለቅጥረኛ ወታደርነት፣ የተከማቸ ሐብት ፍለጋ መጥተው ከቀናት እስከህልፈተ ሕይወታቸው የኖሩባት የውጪ ዜጎችን አስተናግዳለች፡፡ ከነርሱም መሃከል ስለህዝቦቿ፣ መልክዓ ምድሯና ሌሎች ጉዳዮች ለመላው ዓለም መረጃዎችን አቀብለዋል፡፡ ከቆየው የፐሪፕለስ ኦፍ ኤሪቲሪያን ሲ ጸሐፊ፣ ከመካከለኛው ዘመን እነአልቫሬዝን ቀረብ ስንል እነጀምስ ብሩስን፣ ከ19ኛው መቶ/ክ/ዘ መጀመሪያ ጀምሮ ደግሞ የአገሪቱ ውጭ ግንኙነት በተለያዩ የጂኦፖለቲካ ኩነት መንስኤነት በመጠናከሩ በብዛትና በዓይነት ወደአገሪቱ መግባት የጀመሩት የውጭ ዜጎች መጠን እጅግ የጨመረ ብቻ ሳይሆን ቀደም በቀላሉ በማይደረስባቸው የአገሪቱ አካባቢዎች ሳይቀር ለመሰራጨት ችለዋል፡፡ በተለይ የባቡር ሀዲድ መዘርጋት፣ የአገሪቱ ባለሥልጣናት የውጭ ጉብኝት፣ አገሪቱ ነጻነቷን ለማስጠበቅ ያደረገቻቸው ጦርነቶች፣ ዓለም አቀፍ የኃያላን መንግሥታት ቅኝ ግዛትታቸውን ለማስፋት ያደረጓቸው ፉክክሮች፣ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነትና የጥቅምቱ አብዮት ሁሉ ወደአገሪቱ የሚመጡ የውጭ ዜጎችን ቁጥር አበራክቷል፡፡ እነአንቷኒ ዲ አባዲ፣ ሄነሪ ሳልት፣ ፔርኪን፣ ክራፍ፣ ጆን ቤል፣ ፖርታል፣ ሔዌት፣.. ወዘተ እያልን መዘርዘር እንችላለን፡፡ አንዳንዶቹ በከፍተኛ ሁኔታ የነገሥታቱን ባለሟልነት አግኝተው እስከሕይወት ፍጻሜያቸው የቅርብ አማካሪ ሆነው ነገሥታቱንም በቅርብ ለማወቅ፣ ሕዝቡንም ለመረዳት ተችሏቸዋል፡፡ ለአስተያየቴ መነሻ የሆነኝን መጽሐፍ የጻፉት አዶልፍ ፓርለሳክን ጨምሮ ለ1935ቱ ጦርነት ወደአገሪቱ ዘልቀው መግባታቸው በከፍተኛ ሁኔታ የኢትዮጵያ መንግሥትም የሚፈልገው ነበር፡፡ኢትዮጵያ ትከተለው በነበረው ፖሊሲ ምክንያት ለጦርነቱ ዝግጅት ባለማድረጓ አይቀሬው ጦርነት መጣሁ ሲል ቤልጂዬሞቹን አሰልጣኞች በመጠቀም ሁሉም ባለበት ሊሰለጥን ሲሞክር የጣሊኖቹን ሁኔታ ሊረዱ ይችላሉ በሚል ማንኛውንም እርዳታ ለማግኘት ከፍተኛ ፍላጎት ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ግብጽ በመሐመድ አሊና ወራሾቹ አስተዳደር ራሷን ባጠናከረችበትና ወደኢትዮጵያም ለመስፋፋት ጥረት ስታደርግ የአሜሪካ፣ የሰዊዘርላንድ፣ ዴንማርክና የመሳሰሉት አገሮችን እስከ ጀነራል መኮንኖች የሚደርሱ ወታደሮችን ቀጥራ ነበር፡፡ በአገራችንም በእነአፄ ዮሐንስ ጊዜ ኪርክ፣ በአፄ ምኒሊክ ጊዜ እነቡላቶቪች መምጣታቸው የሚታየው ከዚሁ አንጻር ነው፡፡

ከነዚህ ውስጥ በአራትና አምስት አሥሮች የሚቆጠሩት (ስማቸውን ለመዘርዘር ብዛቱ ለጋዜጣ ፎርማት አይመችም) ስለመጡበት ተልዕኮ፣ ስላዩት፣ ስለሰሙት፣ ስላነበቡት የአገሪቱ ሕዝቦች (ባህል፣ ታሪክ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ ሂደት፣ መስተጋብርና ልዩነት)፣ ስለመልክዓምድሯ (ተራሮቿ፣ ወንዞቿ፣ እንስሳዎቿ፣ ዕፀዋቷና የመሳሰሉት) በመጻሕፍትና በጋዜጦች ላይ ጽፈዋል፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም አገሪቱን እኩል ተረድተዋታል፣ ተመሣሣይ አመለካከትም አዳብረዋል ማለት አይቻልም፡፡ ዝርዝሩ ላይ በተቀሮች ባይጠፉም በደምሳሳው በግል የመጡት በመንግሥት ውክልና ተልከው ከመጡት፣ በኢትዮጵያ ቆይታቸው በየኤምባሲያቸው አካባቢ ተወስነው ከከረሙት ከህዝቡ ጋር ተቀላቅለው የኖሩት፣ በሰሜን የአገሪቱ አካባቢ ከከረሙት በደቡብ የአገሪቱ አከባቢ ብዙ ቆይታ ያላቸው፣ በሰላማዊ መንገድ ወደአገራቸው የተመለሱት በጸብ ከአገር ከተባረሩት፤ አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ከሌለው እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ይለያያሉ፡፡ ይህም ልዩነት የመረጃዎቻውን ጥልቀት፣ ተጨባጭነት፣ ሚዛናዊነት፣ ሐቀኝነት እና አቀራረብ ጠገግ ሊወስንባቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ የእኛ የአንባቢያን፣ ገምጋሚያን እና አስተያየት ሰጪ ኃላፊነት በተጨባጭ ማስረጃና አመክንዮ የእነዚህን ሰዎች ሥራ ምርቱን ከግርዱ መለየት እንጂ በስመ ፈረንጅ የዜኖፎቢያ ስሜት ዕውቀትን ማቀጨጭ መሆን የለበትም፡፡ ነጮቹ ካላቸው የባህል ልዩነት ምክንያት አገሪቱ በአውሮፓ አንጻር የነበረችበት ደረጃ ያስደምማቸው የነበሩ እነዚህ ሰዎች በነገሮች ቢደነቁ፣ ያንንም ቢያጋንኑ ለመረዳት አይከብደንም፡፡ምክንያቱም የግነቱን ደረጃ መለካትም ማብረድም በእኛው እጅ ስለሆነ፡፡ እንዲያም ሆኖ የሓበሻ ጀብዱ ትረካ ከእንደእነዚህ ዓይነቱ ሊያስመድበው የሚችል ልክ ያለፈ ማዳነቅ አሳይቷል ሊሰኝ ስለማይችል፣ ዛሬም ትክክለኛውን የመኪና መንገድ ጠርዝ ይዞ የሚጓዝ ሰው ምን ያህል እንደሆነ ልንረዳ እንችላለን፡፡

እስከአሁን በዘረዘርነው መሠረት የአዶልፍ ፓርለሳክ ወደኢትዮጵያ አገባብ፣ አኗኗርና ከኢትዮጵያውያኑ ጋር የነበራቸው ቁርኝት በአስተያየታቸው ላይ መንጸባረቁን መረዳት አያዳግተንም፡፡ ለምሣሌ ጠላት የሚሉትን ጣሊያንን በወራሪነት እንደሚከሱት ሁሉ ራሳቸውን ፍፁም የኢትዮጵያ ወታደር አድርገው ከመውሰዳቸው በተጨማሪ ሳይታክቱ የኢትዮጵያ ጦር ድንበሩን ለማስከበር ፍትሐዊ ውጊያ እንደሚዋጋና ስለጀግንነቱ ማስረገጣቸው ተገቢም ሆነ የማይገባ ስለኢትዮጵያ ያላቸው ፍቅር ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ ስለዚህ የሃበሻ ጀብዱ ከመሰል የነጮች ሥራ በተለየ ስለኢትዮጵያውያን ክብር የሚሟገት በመሆኑ በዘረኝነት የሚጻፉ አስተሳሰቦችን በተቃራኒው ለማንጸር የሚያስችል ሦስተኛ ዕይታ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡ ጸሐፊው በጦርነቱ ለኢትዮጵያ ግዛት መከበር እክል ሆኑ የሚሏቸውን ሁሉ ያለምህረት የሚወቅሱ ሲሆን፤ በዚህም ጣሊያኖቹንም ሆነ ሌሎች የውጭ ዜጎቹን ብቻ ሳይሆን ጦሩ ላይ የተለየ አደጋ ያደረሱትን ኢትዮጵያውያን ወገኖችንም አልማሩም፡፡ የዚያኑ ያህልም በጀግንታቸውና በውጊያ አስተዋጽኦ ያደረጉትን ሁሉ ለማመስገንና ለማሞካሸት አልሰሰቱም፡፡ አምርረው በሚወቅሷቸው የራያና አዘቦ ኢትዮጵያውኖች፣ ጥቂት ጦሩ የሚያልፍባቸው አካባቢ ያሉ የትግራይ መንደሮች፣ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ያደረጉትን ለምን እንዳደረጉ በጥያቄ፣ በትንተናና በመላ ያስቀመጡት አስተያየትም ሚዛናዊ ለመሆን መሞከራቸውን ያሳያል፡፡ ያም ሆኖ ግን የትኛውም ምክንያት ያደረጉትን እንዲያደርጉ ማስተባበያ አይሆንም ብለው ስላመኑ፤ ከወቀሳቸው አላለዘባቸውም፡፡ የውጭ ዜጋ መሆናቸውም የፈጠረላቸው ‹‹ነጻነት›› የተሰማቸውን እንደወረደ እንዲገልጹ ያስቻላቸው ስለሆነ የወቀሳውን ጉልበት ሰያጎላው አልቀረም፡፡ይሄንንም እንደ አንድ ድምጽ አድርጎ ወስዶ ከሌላው ጋር እያነጻሩ እውነታውን ለማውጣት ይረዳል፡፡

ስለዚህ ይህ ሥራ የአገራችንን የታሪክ ዕውቀት እንዲያጎለብትልን አይደለም አንድ የሃበሻ ጀብዱ የሱን ዓይነት ሌሎች በርካቶችን፣ ከእርሱ ተቃራኒ የሆኑትንም ሆነ ሊያማክሉት የሚሞክሩትን በበለጠ ብዛትና ዓይነት እንዲታተሙ የሚያነቃቃ እንጂ ጭራሽ አታሳዩኝ የሚያስብል አይደለም፡፡

እንደታዘብሁት ችግሩ የመጽሐፉ/የመጻሕፍቱ ሳይሆን እንዳለመታደል ሆኖ ያለፈ ዘመን ክስተቶችን ከዘመኑ ፖለቲካ ጋር እያጣመርን በማየት ለቁርቁስ ለማዋል ጥድፊያችን ለከት የሌለው መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ዙሪያ ከተነሱ ትርክቶች እኔን ያንገፈገፈኝ ይሄ ‹‹ማን ተወደሰ ማን ተወቀሰ›› በሚል ተነስቶ ድሮም እኮ ሲባባሉ መስማት ነው፡፡ ፕ/ር መስፍን በደቂቀ እስጢፋኖስ በተነሳ ሃቲት ላይ ከአበሻ ጀብዱ ወስደው የጠቀሱት አንቀጽ የዚህ ደካማ አስተሳሰብ መገለጪያ ሲሆን፤ እርሱን ተከትሎም ፕ/ር ገብሩ ታረቀ፣ ወዳጄ አሥራት እና አንዳንድ ሰዎች የሰጡት አስተያየት (በነገራችን ላይ ወዳጄ ይኩኖ አምላክ የአበሻ ጀብዱ መታተሙ በራሱ የሚገባ አይደለም ዓይነት አስተያየቱ ከዚህ ጋር እንደሚያያዝ የሚያስቡ አሉ) የዚህ አዙሪት ውጤት ነው ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ ክርክሩ ዕውቀትን/እውነትን የማጥራት ሳይሆን እከሌን ነካብኝ ወይም እሰይ እከሌን ሰደበልኝ በሚል መሆኑ ደረጃውን ዝቅ እንዳያደርገው ስጋት አለኝ፡፡ እንዲህ ዓይነት ቁንጽልነት ዕውቀትን ለመሻት ጋሬጣ ከመሆን ባለፈ ከቁንጽልነት መሻገርን፣ የዘመንን ልዩነት ከዚያም ጋር ተያይዞ የሚመጣ የአስተሳሰብ መለወጥን አስፈላጊነት እንዳንገነዘብ የሚያግድ በመሆኑ ዳፋው ነገሮችን በየዘመኑ እንደፈርጁ እንዳንመለከት ገትሮ ሽክርክሪት ውስጥ የሚያስምጠን ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ነገር ፖለቲከኞቹ ሲያደርጉት ብዙም አልደነቅም፤ ለእኔ እነርሱ ሁልጊዜ አንሰው ማሳነስ ስለሚወዱ ይመስለኛል፡፡ በሙያቸው ጥያቄ ላነሳባቸው የማልችላቸው ምሁራን አስተማሪዎቼ ሲያደርጉት ግን ያሳምማል፡፡ እንዲህ ዓይነት አቀራረብ የመጻሐፍቶችን ምሉዕ ዋጋ እንዳናስተውል የሚጋርድ ብቻ ሳይሆን ዛሬ ላይ ባለው በራሳችን የአስተሳሰብ ዕድገት ደረጃ፤ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወታችን አብሮነት ላይ የሚሰነዝር ፍላጻ ይሆንብኛል፡፡

### መጽሐፉ ከያዘው ፍሬ ነገር አንጻር፦

የመጽሐፉ ቀልብ ያለው ኢትዮጵያ በጣሊያን ወረራ መንስኤነት የገባችበትን ጦርነት አዶልፍ ፓርለሳክ አማካሪ የሆኑለት የራስ ካሣ ጦር የተሰለፈበት የሰሜኑ ግንባር ሁነት ነው፡፡ ከዋና ዋናዎቹ ጉዳዮች መሃል ለጦርነቱ የነበረው ዝግጅት ደረጃ፣ የኃይል አሰላለፍ፣ የመሳሪያ ብዛትና ዓይነት፣ የውጊያ ስልት፣ የስነልቦና ደረጃ፣ የቅስቀሳ ሥራዎች፣ የወኔና ጀብዱ ደረጃ ይገኙበታል፡፡ መጽሐፉ ስለ አምባአራዶምና ማይጨው ከሌሎች በተገኘ መረጃ፤ ስለተምቤን በዓይን ዕማኝነት ያቀርብልናል፡፡ የራስ ካሣን ጦር አስመልክቶ የዕለት ተዕለት ክስተት በአንዳንድ ጉዳዮችም ጥቃቅኑ ሁኔታ ሳይቀር ለማወቅ ለሚሻ የሃበሻ ጀብዱ ፍቱን ነው፡፡ ከማይጨው ጦርነት ወዲህ የጦሩ መልስ ምን እንደሚመስልም ማሣየቱም የመጽሐፉ ተጨማሪ ፋይዳው ነው፡፡ ባጠቃላይ የጦርነቱን ዋዜማ፣ የጦርነቱን ሂደት፣ የሽንፈቱንና የምልሰቱን ሁሉ ያካትታል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ጦርነቱን አስመልክቶ በኢትዮጵያውያኑ ወገን የተከተበው ማስታወሻ ብዙም አይደለም፡፡ ስለጦርነቱ በዓለም ላይ ለለው ዕውቀት በዋናነት ምንጭ/መሰረት የሆነው ጣሊያኖቹ ያዘጋጇቸው ሰነዶች/ዘገባዎችና ሕትመቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ እንደ የሃበሻ ጀብዱ ዓይነቱ ሦስተኛ ዕይታ በመስጠት ለማንጻሪያነት ይጠቅማል፡፡

የአዶልፍ ፓርለሳክን መጽሐፍ ከዘመነኞቹ ከነኮ/ል አለሀንድሮ ዴል ባዬም የሚለየው ጉዳይ አለው፡፡ እርሱም ስለሕዝባዊው ጦር ትረካው ነው፡፡ የዚህ ሕዝባዊ ጦር መሪም በፓርለሳክ አገላለጽ ወጣቱ አብቹ ነው፡፡ በደቡብና በምዕራብ ሸዋ አካባቢ ከሰላሌና ከአካባቢው የተነሱ ወጣቶች በአርበኝነቱ ጊዜ የነበራቸው ዝና ከድል በኋላ በነጃገማ ኬሎ ታሪክ ምልክትነት ቢዘከርም እንደ አብቹ ያልተነገረለት ስንት ይኖር ይሆን ያስብላል፡፡ እስከአሁን ለምን ስለአብቹ ሳንሰማ ቀረን? የአብቹ ዘፈን እና በዚያ ዙሪያ የሚነገሩ ሌሎች አፈታሪክ መሰል ጉዳዮች ከአዶልፍ ፓርለሳክ አብቹ ጋር ምን ያህል ግንኙነት አላቸው? ፓርለሳክስ ምን ያህሉ የአብቹ ትረካቸው ዕውነት ነው? ምን ያህልስ ግነት አለው/ወይም ቅናሽ? ለሚሉ ጥያቄዎች የኢትዮጵያ ታሪክ ተማሪዎችም ሆኑ የሚመለከታቸው ተቋማት የአብቹን ገድልና ተያያዥ ጉዳዮችን ለማጥናት፣ ለማጥራትና ለማሳወቅ ሲሞክሩ የምንረዳው ይሆናል፡፡

### ትርጉምና አርትኦት፦

በትርጉም ደረጃ የተርጓሚው ስራ የተዋጣለት ነው አይደለም ለማለት ዋንኛውን ቅጂ ማየት ያስፈልጋል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የቀረበልን የሃበሻ ጀብዱ ጥንቅቅ ባለ ቋንቋ የቀረበ በመሆኑ ብቻ ግን የተርጓሚውን አስተዋጽኦ እንድንገምት ይረዳናል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የቼክ ቋንቋን የሚያውቅ ሰው በወጡና በትርጉሙ መሃል ያለውን ሥምረት እንዲያጠናና እንዲያሳውቀን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ይህ ቢደረግ ወዳጄ ይኩኖ አምላክ ጸሐፊው የውጭ አገር ሰው ስለሆኑ አጤ ምኒሊክን የጠሩበት አጠራር በአማርኛው ሕትመት ላይ እንዳለው አይመስለኝም ብሎ ስላላየውና ቋንቋውን ስለማያውቀው መጽሐፍ እንደሰጠው አስተያት ዓይነት ላሉትም ስለሚጠቅም፡፡ በመሠረቱ አዶልፍ ፓርለሳክ ራሱን ሙሉ ለሙሉ ከኢትዮጵያውያኑ ጋር በመወገን እኛ እያለ ትረካውን ማቅረቡ ምልክት ቢሆንም ባለኝ መረጃ በመጽሐፉ ላይ የቀረበው አገላለጽ የጸሐፊው የራሱ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ የመጽሐፉ ታሪክንም ለማወቅ ከእርሱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማጥናት ቋንቋውን የሚያውቁ ፍላጎት ቢያሳድሩ አንባቢን ይጠቅማል እላለሁ፡፡ መጽሐፉ በቼክ ቋንቋ የተጻፈ የ1948 እና 1989 እኤአ እትም አለው፡፡ ያጋጣሚ ነገር ሁለቱም ዓመታት በቼክ ታሪክ ከፍተኛ ክስተት የተከወነባቸው ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ኮሚኒስቶች በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን የያዙበት ሲሆን ሁለተኛው በአብዮት ከሥልጣን የተባረሩበት ነው፡፡ የ1989ኙ እትም አጥሮ የተጻፈ ከመሆኑ አንጻር ሙሉ ለሙሉ አዶልፍ ፓርለሳክ የጻፈውን አያጠቃልልም፡፡ የተሟላው እትም በተርጓሚው እጅ ሳይገባ በፊትም የ1989ኙን እትም በቅጽ እየተረጎሙ በድጎረ ገጽ ያወጡት ቢሆንም፤ ታሪኩ ቁንጽል ነበር፡፡ ስለዚህ አሁን በእጃችን የገባው የሃበሻ ጀብዱ ትርጉም አሁን ባለበት የተሟላ መልክ የተተረጎመው ከ1948ቱ ነው፡፡ ስለዚህ በትርጉሙ መጽሐፍ በርዕስ ገጹ የተቀመጠው 1989 ዓ.ም የሚለው በአርትኦት ስህተት ነው፡፡ መጽሐፉን ለመጻፍ ስለፈጀው ጊዜ ጸሐፊው ለመረጃነት ከተጠቀሙበቸው መጽሐፎችና ደብዳቤዎች (60) የቃል መረጃዎች እና አንዳንድ አገላለጾች ለምሳሌ ‹‹አሁን››(69)፣ ‹‹ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት››(68) የሚጠቁሙት ነገር ቢኖርም ብዙ ማለት አይቻልም፡፡ የአርትኦት ነገር ካነሳን ትንሽ ስለመጽሐፉ በሚል ርዕስ ተርጓሚው ወደትርጉም የገቡበትን ሁኔታ የገለጹበት ዝርዝር የመጽሐፉ ጸሐፊ ለመጽሐፉ መጀመሪያ ካደረጉት ‹‹የአርሲዋ ትንቢተኛ አሮጊት›› በሚል ርዕስ የቀረበ ጽሑፍ ጋር መቀላቀሉ ተገቢነት የለውም፡፡

### የአስተያየቱ ፍሬነገር

የሃበሻ ጀብዱን ሙሉ ለሙሉ ያነበበ ኢትዮጵያውያንን ለመስደብ የተጻፈ ነው ብሎ ለመውሰድ በእጅጉ እንደሚቸገር ሳስብ፤ የወዳጄ ይኩኖ አስተያየት ስለመጽሐፉ በአጠቃላይ አስተያየት ሰጠ ለማለት ተቸግሬያለሁ፡፡ አቀራረቡም መጽሐፉን ያለአውዱ ያስቀመጠው ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ስለዚህ ምን ተጻፈ እንጂ ማን ጻፈ የሚለውን ከምር መውሰድ አቁመን፣ በመረጃ እጥረት የሚፈጠር ቁንጽልነትን አስወግደን፤ ትርክታችን ከሞቲቭ/መግፍኤ ሃሳብ/ ወደ ሰብስታንቲቭ/ፍሬነገር/ ለውጠን፤ ታሪክንና ትዝታን ለመለየት እንጣር፡፡ በመጨረሻም በማንኛውም መልኩ ስለመጽሐፉ በፍትህ ጋዜጣ፣ በአዲስ ጉዳይ መጽሔትና በሚዩዚክ ሜይዴይ የመጽሀፍ ውይይት ላይ አስተያየት የሰጡትን ሁሉ እያመሰገንሁ፤ ስለዚህም ሆነ ሌሎች መጻሕፍት ጤናማ ውይይት ለማድረግ እንዲያስችለን የፖለቲካው ልኩስኩስነት ስለዕውቀት በምናደርገው ውይይት ላይ እንዳያጠላ በመመኘት እሰናበታለሁ፡፡

# የአብዮቱ ደወል

በሙሉነህ አያሌውና በኃ/መስቀል በሸዋምየለህ

ህዝቦች ሆይ ተነሱ
ስለመብቶቻችሁም ቁሙ
ጠመንጃችሁን አንሱ
ጨቋኞቻችሁንም ታገሉ!
/የህወሓት የመጀመሪያው መዝሙር/

መጀመሪያ በያኔው አፄ ኃ/ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ስብስብ በኩል ስለትግራይ ጭቆና መወያየት የጀመሩት የትግራይ ወጣቶች ማህበር ገስገስቲ ብሔረ-ትግራይ/ማግባት/ የሚል ማህበር መሰረቱ፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላም በነውጠኛው የቀድሞ የአፄው የፓርላማ አባል ገሰሰ አየለ መሪነት ወደ ደደቢት ወረዱ፡፡ የህወሓት የሰላሳ ሰባት ዓመታት አስቸጋሪ ጉዞ ከዚህ ሁነት ይጀምራል፡፡ ፓርቲው ከዚህ ወቅት ጀምሮ የሄደባቸውን መንገዶች መመርመር አሁን ፓርቲውን እየመሩ ያሉት ልሂቃን ከሚያሰሙት ትርክት የዘለለ ፋይዳ ያለው ጭብጥ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ፕ/ር ኬጅ ቴል ትሮኖቮል “War and the politics of identity in Ethiopia” በሚለው መፅሐፉ ላይ በየሀገራቱ የሚነሱ የዘውግ እና የብሔርተኝነት ጥያቄዎች ዋነኛው ማጠንጠኛቸው ከሌሎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተነፃፃሪነት ተቀምጠው ከሚያገኙት የራሳቸው ምስል የሚነሳ ነው ይላል፡፡ እንደ ትሮንቮል አገላለፅ የዚህ አይነት እንቅስቃሴ አቀንቃኞች የትግላቸው መስመር መግቢያው ‹‹እኛ ማን ነን?›› የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ይጀምራል፡፡ ንፅፅሩም ደርዝ መያዝ የሚጀምረው የዚህ ፖለቲካ አቀንቃኝ ተጋሪ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በገዢው መደብ በሚደርስባቸው የ‹‹መገፋት እና የመገለል›› ተፅዕኖ ዋነኛው ምክንያታቸው ነው፡፡ በባህል፣ በማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መስፈርቶች ራሳቸውን ‹‹ከሌሎቹ›› በትይዩ አስቀምጠው የሚያዩዋቸው እውነታዎች ለልዩነት የድንበር ከለላ የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ይህንን ከሌሎቹ የህብረተሰብ ክፍሎች (በተለይ ከገዢው መደብ) ጋር በንፅፅር ያገኙትን የልዩነት መስመር በመጠቀም የውስጥ አንድነታቸውን ለማጠናከር የልዩነት መንፈሳቸውን በር ከፋች አካሄድ ያደርጉታል፡፡ በተለይ የውጭ ኃይሎች ጫና እና ግፊት ፣ለውስጥ ኃይሎች ህብረትና ጥንካሬ መተማመኛ ነው፡፡ መገፋት፣ ግጭት እና የመሳሰሉት ማህበራዊ ጫናዎች ለዘውግ እና ብሔርተኛ ቡድኖች መፈልፈል በምክንያትነት ይጠቀሳሉ፡፡

የመገፋት ጣጣ

የህወሓት መስራች እና የአመራር አባል የነበሩት ዶ/ር አረጋዊ በረሄ “The origin of the Tigray people’s liberation front” በሚለው ፅሁፋቸው ላይ የትግራይ ህዝብ በወቅቱ በተደጋጋሚ ይደርስበት የነበረው ‹‹ጫና›› እና ‹‹የባይተዋርነት›› ስሜት ለትግል ምስረታው ገፊ ምክንያት ነበር ይላሉ፡፡ በተለይ የትግራይ ምሁራን እና የማህበረሰቡ አባላት እራሳቸውን ከሌሎች የአገሪቱ ማህበረሰብ ክፍል አንፃር ሲመለከቱት፣ እራሳቸውን ያገኙበት ቦታ ‹‹እኛ›› እና ‹‹እነርሱ›› ወደ ሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ ገፍቷቸዋል፡፡

‹‹የትግራይ ህዝቦች እየደረሰባቸው የነበረውን ጭቆና ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር ሲያነፃፅሩት የእነርሱ ከሁሉ የከፋ ሆነው አገኙት፡፡ ይህ መገፋት ድሮ ትግራይ ከነበራት የታላቅነት ታሪክ ጋር በታሪክ መነፅር በመመልከት ቁጭት ውስጥ ለመግባታቸው የመጀመሪያው ልዩነትን መፍጠሪያ ቢሆንም በኢትዮጵያ ውስጥ ለወደቀው የትግራዊያን ማንነት እንነሳ የሚለውን የቁጭት ስሜት መፍጠርም የቻለም ነበር›› ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

የትግራይ ማህበረሰብ ከሌሎች የተቀሩት ‹‹የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በንፅፅር ራሳቸውን እየተመለከቱ›› የሚለው የአረጋዊ በርሄ ትንታኔ፤ በክልሉ የተነሳውን የህዝብ አመፅ፤ ትግራይን በኢትዮጵያ ውስጥ አድርጐ የመቀበል ማስረጃ ነበር፡፡ ይህም አቶ አረጋዊ በፅሁፋቸው መግቢያ ላይ እንደጠቀሱት

‹‹የህወሓት የደፈጣ ውጊያ በመጀመሪያዎች የትግሉ የታሪክ ምዕራፍ ላይ የዘውግ-ብሔርተኝነት ጥያቄ ሲሆን አላማውም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለች የራሷን እድል መወሰን የምትችል ነጻ ትግራይን እውን ማድረግ›› የሚል እንደነበር ገልፀዋል፡፡ የመጀመሪያውም የወያኔ የገበሬ አመፅም አምባገነናዊው የአፄውን ስርዓት በማለዘብ እንጂ በትግራይ የመገንጠል ጥያቄ ላይ ያተኮረ አልነበረም፡፡

ዘላለም ቁምላቸው ‹‹የኢትዮጵያዊነት እና የአማራነት መለያዎች ህብር›› በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ለሁለተኛው የወያኔ (የኋለኛው የህወሓትን) እንቅስቃሴ የአመሰራረት ምክንያቶች ከአጠቃላይ ታሪካዊ ዳራ አንፃር በጥቅሉ መታየት እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ፡፡ እርሳቸው የተለያዩ ምክንያቶችን በዚህ ረገድ ቢያቀርቡም በዋናት ግን ለትግራይ ልሂቃን እና ህብረተሰብ ክፍሎች በሌሎች የ‹‹መነጠል›› እና ‹‹የመገፋት›› ሂደት ውስጣዊ ትግል ባህሪን እንዲቀይሩ ያደረጓቸውን ታሪካዊ እውነቶች በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡

ነባሩ የትግራይ ‹‹መሳፍንታዊ›› አፄ ዮሐንስ ‹‹ንጉሠ ነገሥቱ›› ከትግራይ እንዳይወጣ ማድረግ ይችሉ ስለነበሩበት ሁኔታ ወደኋላው ተመልሶ መመልከት፣ በሸዋ እየተመሰረተ ይታይ በነበረው ስርወ መንግስት ላይ ያደረበት ታላቅ ቅናት በሂደት የሰፊውን የትግራይ ልሂቃንን ሁሉ አስተሳሰብ ውስጥ ሊሰርፅ በቅቷል የሚለው የመጀመሪያው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን የነበረው የአሀዳዊ መንግስት አስተዳደር እና የማዕከላዊ መንግስት ምስረታ አንድን ቋንቋ (አማርኛ) ነጥሎ በሀገሪቱ ውስጥ በሞላ እና በስፋት መጠቀሚያ እንዲሆን መወሰኑ ተፅእኖ አሳድሯል የሚለው ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች በዋነኝነት የብሔሩ ተወላጅ ለነበሩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የመሰባሰብ ምክንያት ነበር፡፡ በብሔሩ ላይ የደረሰው የጭቆና ታሪክ በተበጣጠሰ መልኩ ሲካሄዱ የነበሩ የተቃውሞ ድምፆች በአንድ ላይ ተቀናጅተው ለለውጥ ይሰሩ ዘንድ መተባበር ግድ ሆነ፡፡ እዚህ ጋር የሚጠቀሰው ጉዳይ የብሔሩ ልሂቃን በዩኒቨርስቲ ውስጥም ቢሆን ያነሳሳ የተቋውሞ ድምፅ እንደ ሌሎች የተቀሩት የሀገሪቷ ነዋሪዎች የደረሰባቸውን የጥላቻ እና የመገፋት ፖለቲካን በመቃወም እንጂ የመገንጠልን ሀሳብ በማቀንቀን አልነበረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለህብረቱ ጥንካሬ መሰረት የሆናቸው የ‹‹ተወላጅነት›› ስሜት እና በተወላጅነት ይገባናል የሚሉት የ‹‹ጥቅም ተጋሪነት›› ጥያቄ ለሌላ ተወላጅ ላልሆነ ግለሰብ ተላልፎ መስጠት ጉዳይ ነበር፡፡ ለእነዚህ ምክንያቶች አንድ ሁለት አስረጂ ሀሳቦችን ማቅረብ እንችላለን፡፡

የአፄ ዮሐንስ መተማ ላይ እረፍት ዜና ሁለት አበይት ውጤቶችን ይዞ መጥቷል፡፡ የመጀመሪያው ንጉሱ በጦርነቱ ህይወት ማጣት የፈጠረው የሐዘን ድባብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በመሳፍንታዊ አስተዳደር ከንጉሱ እረፍት በኋላ ስልጣን ለማን ይገባዋል? የሚለው ጥያቄ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ንጉሱ በልጃቸው አልያም በቅርብ ዘመዳቸው፣ዘውዳዊ ሥርዓቱን ጠብቆ ይተላለፋል የሚለው ሳይሆን ቀርቶ በጊዜው የሸዋ ንጉሥ የነበሩት አፄ ሚኒልክን በቦታው ይዞ ብቅ የማለቱ ሁነት ንጉሱን ህጋዊ የሥልጣን ባለቤት ሳይሆን የሥልጣን ነጣቂ (power usurper) እንደሆኑ አስመስሎባቸዋል፡፡ ይህም የብሔሩ ተወላጆች ለሸዋዎች እና ለሸዋ ገዢዎች ስልጣን እውቅና እንዲነፍጉ አድርጓቸዋል፡፡ የስልጣን ይገባናል ጥያቄም አንዱ መሰረት ይሄው ነበር፡፡

በአፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን የነበረው የሸዋ መሳፍንቶች በትግራይ ምድር ላይ በአስተዳዳሪነት እንዲመደቡ መደረጋቸው ሌላው የውክልና ይገባናል ጥያቄ መሰረት ነበር፡፡ በንጉሱ የተመደቡ የሸዋ ሹማምንቶች የብሔሩን ተወላጆች ባህል፣ ቋንቋና ማህበራዊ ስርዓት ከማክበር ይልቅ የመካከለኛውን ሀገር አኗኗር ለመጫን ያደረጉት ጥረት በብሔሩ ተወላጆች ዘንድ ቅሬታን ከመፍጠሩ በተጨማሪም አይወክሉንም የሚለው የቅራኔ ድምፅ ጉልቶ እንዲሰማ የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡

እነዚህ ሁለቱ ምክንያቶች የብሔሩ ልሂቃንን በ‹‹ተወላጅነት›› እና በ‹‹ይገባኛል›› ስሜት የጋራ ታሪክ ተጋሪ የመሆናቸውን ያህል የጋራ መፍትሄ ፈላጊም እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

‹‹የትግራይ ሪፖብሊክ››

በወቅቱ የነበረውን ‹‹ጨቋኝ›› አገዛዝ በመቃወም በተማሪዎች፣ ምሁራን፣ ሰራተኞች ወዘተ የተጀመረው እንቅስቃሴ በ1967ዓ.ም ህወሓትን ወለደ፡፡ ይህ ለውጥ ፈለግ እንቅስቃሴ መሰረቱ የአንድ ክልል ብሔር ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በጊዜው የነበሩ የተለያዩ የህብረተሰብ ልዑካንን ይወክሉ የነበሩ የብሄር ድርጅቶች ሀሳብም ጭምር እንደነበሩ የተለያዩ ድርሳናት ያመላክታሉ፡፡

ለዚህም ማስረጃው ከህወሓት በፊት የዚህን አገዛዝ በመቃወም ወደ ትጥቅ ትግል የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች መግባታቸው እውነት ነው፡፡ ግ.ገ.ሓ.ት (ግንባር ገድሊ ሓርነት ትግራይ)፣ ኢህአፓ፣ ኦነግ እና የሶማሊያ ድርጅቶች ለዚህ ተጠቃሽ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ህወሓት የእነዚህን ለውጥ ፈላጊ ቡድኖች ፈለግ ተከትሎ ወደ ትጥቅ ትግሉ ሲቀላቀል በጊዜው ሲቀነቀን ከነበረው ኮሙኒስታዊ ርዕዮተ ዓለም ውጭ የራሱ የሆነ አንዳችም ንድፈ ሀሳባዊ አካሄድ አልነበረውም፡፡ ትግሉም የወከለውን ‹‹የትግራይን ህዝብ ከጨቋኝ አገዛዝ ነፃ እናወጣለን›› ከማለት ውጭ እንዴት፣ ማን፣ በምን አይነት መልኩ የሚሉትን ስትራቴጂካዊ ማሳመኛ ሰነድ አልነበረውም፡፡ ለዚህም ነው ትግሉ በጥቂት ደፋር ግለሰቦች ደመነፍሳዊ አካሄድ ከጅማሮው ይመራ ነበር ሲሊ አቶ ዘላለም ቁምላቸው ከላይ በተጠቀሰው መፅሐፋቸው የሚከራከሩት፡፡

‹‹1968 ዓ.ም. ህወሓት የመጀመሪያው ጉባዔ ካካሄደ በኋላ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት (ከሁለት እና ሶስት የማይበልጡ) ያረቀቁትን በትግረኛ፣ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተፅፎ በአቶ ስዩም መስፍን አማካኝነት ሱዳን ውስጥ ታትሞ የመጀመሪያው ማኒፌስቶ ተሰራጨ፡፡›› ይላሉ የቀድሞ የህወሓት መስራች እና ታጋይ አቶ አስገደ ገ/ሥላሴ የማኒፌስቶው ዋናው ጭብጥ ‹‹በትግላችን ዋነኛው ጥያቄ ትግራይን ከአማራ ቅኝ ገዢዎች ነፃ በማውጣት የትግራይ ሪፖብሊክን ማቋቋም ነው›› የሚል ነበር፡፡

ትግራይ ልሂቃን የብሔር ጭቆናውን ‹‹እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን›› የሚለውን የጋራ መተያያ ወደ ጎን በመተው ‹‹ነፃ ትግራይን መመስረት›› ወደሚለው ተሸጋግረዋል፡፡

የክልሉን ታሪክ ወደ ኋላ ዞሮ በመጠምዘዝ ትግራይ ድሮም ቢሆን በመሃል አካባቢ በነበሩ ነገስታት አገዛዝ የኢትዮጵያ ክፍል ተደርጋ አትወሰድም የሚሉ የታሪክ ማስረጃዎችን በመፈለግ መተንተኑን ተያያዙት፡፡ ከነዚህም መካከል ከአፄ ቴዎድሮስ በኋላ በአፄ ዮሐንስ እና በሚኒልክ መሀከል የነበረው የስልጣን ሽኩቻ፣ ትግራይ ከቀሪው ኢትዮጵያ ነፃ ሁኖ የኖረ አካባቢ መሆኑን እንደሚያረጋግጥ ተደርጎ ቀረበ፡፡ አፄ ዮሐንስ ከውጭ ኃይሎች ጋር ሲዋጉ አፄ ሚኒልክ እርሳቸውን ከመረዳት ይልቅ፣ በሚጎዳቸው ተግባራት ውስጥ ተሳትፈው መገኘታቸው ለዚህ ልዩነት መታወቂያ ታላቅ ጭብጥ መረጃ ሆኖ የቀረበው አንዱ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪም በጊዜው በጣሊያን እና በሚኒልክ መካከል የተካሄዱ የጋራ ውሎች ሌላኛው ማሳያ ነበር፡፡በክልሉ ልሂቃን እይታ አፄ ዮሐንስ ጣሊያንን ከአካባቢው ነቅሎ ማባረር የዘወትር ሃሳባቸው የነበረ ሲሆን፣ አፄ ሚኒልክ ግን ለጣሊያኖች በውል የተወሰነውን የኢትዮጵያ ግዛት ክልል ቆርሰው ለመስጠት የተስማሙ ናቸው ይሏቸዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት የትግራይ ብሔር ልሂቃን የመገንጠል ሀሳባቸውን በአስረጅነት ሲያቀርብ፤ አፄ ሚኒልክ ያንን አካባቢ እንደ ሌሎቹ የአገሪቱ ህዝቦች እና መሬት ክልል አይቆጥሩት ነበር ማለት ነው ሲሉ ይደመድማሉ፡፡ ይህም ‹‹በትግራይ›› ህዝብ እና በተቀረው ‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ›› መካከል ላለው ልዩነት አንዱ ማሳያ እንደሆነ ማመናቸው ለትግራይ ሪፖብሊክ ሀሳብ አንዱ መሰረት መጣያቸው ነበር፡፡

የህወሓት እንቅስቃሴ በወቅቱ ነፃ ሪፖብሊክ ትግራይን ለመመስረት ስለነበር በጊዜው በትግራይ ክልል ውስጥ ይንቀሳቀሱ የነበሩትን ሌሎች ታጣቂ ቡድኖችን ‹‹ከትግራይ ክልል ውጡልን፣ ለትግራይ ራሳችን አለን፤ ወደ ሌላ የኢትዮጵያ ክልል ሂዱልን፤ የትግላችን ጥያቄ ነፃ ሀገር የሆነች ትግራይን መመስረት ነው፡፡ከዚህም የተነሳ ‹‹ከእኛ ውጪ ሌላ ፓርቲ በትግራይ ምድር ›› በሚል ማን አህሎኝነት በወታደራዊ እርምጃ ኢህአፓን ከትግራይ ማባረር እንዳለባቸው ማመናቸው ለፅሁፉ አርቃቂዎች አንዱ ሙግፋሴ ይመስላል፡፡ ›› የሚል እንደነበር መስራች ታጋዮች ይመሰክራሉ፡፡

ምንም እንኳን በታሪካዊው ትንታኔ ህወሓት የትግራይን መገንጠል በእጅጉ ቢያቀነቅንም የፖለቲካ ተንታኞች ግን ይህንን አካሄድ የጥቂት የህወሓት አመራር አባላት እንጂ ብዙሃኑን አይወክልም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ ለዚህም የሚያቀርቡት መከራከሪያ የማኒፌስቶውን ከአመት ያነሰ የቆይታ እድሜ ነው፡፡ ታዲያ የማኒፌስቶው መዘጋጀት ለምን አስፈለገ? ማን አዘጋጀው? የሚለውን ጥያቄም በሌላ መልኩ መመልከት ተገቢ ነው፡፡

ማኒፌስቶውን የፃፈው ማን ነው?

በህወሓት የፖለቲካ ታሪክ ላይ የታተሙ ፅሁፎች ከማይስማሙባቸው ጉዳዮች ዋነኛው ማኒፌስቶ በተመለከተ የሚያቀርቡት ጥቆማ ነው፡፡ ትግራይን በመገንጠል ‹‹የትግራይ ሪፖብሊክን›› ስለመመስረት የሚአወራውን ይህን ማኔፌስቶ ማን እንደፃፈው ከእርስ በርስ ውንጀላ ውጪ የጠራ ነገር ብዙም አይሰማም፡፡ ከማኒፌስቶው መበተን በፊት ቀደም ብሎ የነበረውን የፓርቲው ፕሮግራም ዝርዝር በሆነ መንገድ መዘጋጀት እንዳለበት ውሳኔ ተላልፎ ነበር፡፡ ይህንን ለመፈፀም በሚልም የፓርቲው የጊዜው አመራሮች በወቅቱ በትግራይ ክልል በአንፃራዊነት የተሻለ መሰረት ስለነበረው ኢህአፓ መወያየት ነበረባቸው፡፡ የወቅቱ አመራሮች ኢህአፓን በተመለከተ የደረሰበት ድምዳሜ ለማኒፌስቶው አርቃቂዎች አንዱ ማስመሰያ ምክንያት /Pre-text/ የነበረ ይመስላል፡፡ የበላይነት የሠረፀበት፣ በትምክህተኝነት የተሞላ አልፎም ‹‹የብሄር ጥያቄን›› መፍታት የማይችል አምባገነናዊ ቡድን ሲሉ ከሰየሙት ኢህአፓ ጋር ምንም ዓይነት ፓርቲ-ተኮር ግንኙነት ሊኖራቸው እንደማይገባ ወሰኑ፡፡

ዶ/ር አረጋዊ በኩላቸው “A political history of TPLF: Revolt, Ideology and mobilization in Ethiopia” በሚለው መጽሐፋቸው የማኔፌስቶው ባለቤቶች አባይ ፀሐዬ፣ መለስ ዜናዊ እና ስብሃት ነጋ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ለዚህም እንደማሳያነት የሚጠቅሱት በ1967 ዓ.ም. ከአቶ ስብሃት ነጋ ጋር ያደርጓቸው በነበሩ ወዳጃዊ ውይይቶች ላይ አቶ ስብሃት የትግራይ ጥያቄ እንደ ኤርትራው ሁሉ ‹‹የፀረ-ቅኝ አገዛዝ›› እንደሆነ እንደሚያምኑ ሲያነሱላቸው ‹‹ጉዳዩን በጥርጣሬ በመመልከቴ ከዛ ወቅት ጀምሮ እኔ እና ስብሃት ግንኙነታችን ሻከረ፡፡›› ሲሉ ዶ/ር አረጋዊ ስለጉዳዩ ያላቸውን አቋም ፅፈዋል፡፡ ፅሁፉን በማርቀቅ አስተዋጽኦ ባያደርጉም ‹‹እንገነጥላታለን›› ያሏትን ‹‹የትግራይ ሪፖብሊክ›› ካርታ በመቅረፅ ቀዳሚ ኃላፊነት የሚወስዱት አቶ ስዩም መስፍን ስለመሆናቸው ነባር የፓርቲው ታጋዮች ይናገራሉ፡፡ በ1968 ዓ.ም. የተበተነውን ይሄን ፅሁፍ በተመለከተ በአርቃቂነት ስማቸው የተነሳው እነ አቶ መለስ ለ‹‹መገንጠሉ›› ሀሳብ በምክንያትነት ስላቀረቡት ጉዳይ አቶ ካህሳይ በርሄ እና ተስፋዬ አጽበሃ ፓርቲው በወቅቱ ከነበሩ ኢህአፓን መሰል

ግራ-ዘመም ፓርቲዎች ጋር በጋራ ሊሰራ የሚያስችል ሁኔታ ያለመኖሩ ነው የሚል ሙግት ማቅረባቸውን ይናገራሉ፡፡ ነገሩ በዚህ መልክ ቢሆንም ከሻዕቢያ፣ ከኢህአፓ እና ከአንዳንድ የፓርቲው አመራር አባላት የተነሱ ተቃውሞዎች እና ትችቶች ህወሓት ማኒፌስቶውን ለጊዜውም ቢሆን ወደ ጎን እንዲል ተገድዷል፡፡ ከዚህም በዘለለ አመራሩ ትግራይን በመገንጠል ሃሳብ ላይ ያለውን አቋም እንደሳበ ለማሳየት በሚመስል በአንድ ጎኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በትግራይ ውስጥ ራሱን ብቸኛ የትግራይ ተወካይ አድርጎ ለማቅረብ ከመፈለግ በመነጨ እንደ ህወሓት ሁሉ ተመሳሳይ ጥያቄ የነበረውን የትግራይ ነፃ አውጪ ግንባርን ከወቅቱ አጋሩ ሻዕቢያ ጋር በመሆን በወታደራዊ ሀይል ከክልሉ አስወጥቷል፡፡ ይህንን ማኒፌስቶ በተመለከተ የሶሻሊስት ቡድኑ ማሌሊት በ1977 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ ምስረታውን በማስመልከት ባወጣው ባለአምስት ገፅ መግለጫ ስለጉዳዩ ሲናገር፣‹‹የማኒፌስቶ አርቃቂዎች ወደዚህ ውሳኔ የመራቸው በወቅቱ የነበሩት ግራ-ዘመም ፓርቲዎች ብሄርን በተመለከተ ያሳዩት የትምክህተኝነት ባህሪ ሲሆን፣ ይህ ሁነት ቢገፋቸውም ቅሉ በጊዜው የተወሰደው አቋም ህወሓት የብሄር ጥያቄን በተመለከተ የነበረውን የተንሸዋረረ ዕይታ ያሳያል ሲል ሞግቷል፡፡ አቶ ዘሪሁን ተሾመ በበኩላቸው‹‹ኮርኮራ›› በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ለዚህ ጥያቄ መልስ አላቸው፡፡ አቶ ዘሪሁን ለማኒፌስቶው መውጣት ዋናው ምክንያት ብለው የሚያነሱት በወቅቱ አመራሩ ውስጥ እንደተፈጠረ የሚነገረውን የአውራጃነት ስሜት ሲሆን ህወሓት በጊዜው ከአስመራና ከአዲስ አበባ በሚኖሩ ኃይሎች ትምክህታዊ ንቀት ተገፍቶ ሳንድዊች የመሆን ስሜት አጥለቅልቆት እንደነበር ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ መገፋት በተጨማሪም የድርጅቱ አመራር በኢትዮጵያ የፖለቲካ ትግል ስላለው ቦታና ሚና የጋራ የሆነ ሰፊ ግንዛቤ አለማጐልበቱ ሌላው ምክንያት ነበር፡፡ በመሆኑም እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ምክንያች ‹‹ከመገፋት ጋር ተደምሮ በንዴት የተሞላ ስሜታዊ እምቢተኝነት የበላይ ሆኖ እንዲወጣ አገዘ፡፡

ከዚህ የመገንጠል ሀሳብ ጀርባ ያሉትን የህወሓት አመራሮች ስነ-ልቦና ከሌሎች አቻ የአፍሪካ የጉሬላ ተዋጊ ንቅናቄ መሪዎች ጋር ማስተያየት ምናልባትም ሌላ ዕይታ ሊጨምር ይችላል፡፡ በዚህ ዓይነት እንቅስቃሴ ስሙ በገዘፉ የሚነሳው የምዛምቢኩ ፍሪሊሞ መሪ ኤድዋርድ ሞንዴል፣ የደቡብ ሱዳን ነፃ አውጪ ግንባሩ ጆን ጋራንግ፣ ኢሳያስ አፈወርቂ እና ሙሴቬኒ ከህወሓት አመራሮች ጋር በንፅፅር ለተመለከታቸው ሰፋ ያለ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ እኒህ የየንቅናቄዎቹ መሪዎች በተሻለ የት/ት ደረጃ ላይ የነበሩ፣ የተሻለ ፖለቲካዊ ተሞክሮ እና ከሌሎች ሀገራትም ጋር ጠበቅ ያለ ግንኙነት የነበሯቸው አብዮተኞች ናቸው፡፡ በግልባጩ የህወሓት ፖለቲከኞች በሃያዎቹ መጀመሪያ ላይ የነበሩ፣ ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን እንኳን መጨረስ ያልቻሉ ወጣቶች ነበሩ፡፡ ይህ ነው የሚባል የፖለቲካ ተሞክሮም ሆነ ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር (ከሻዕቢያ በስተቀር)

# እየተደወለ ነው

ጠንካራ የልምድ ልውውጥ ያደረጉ አልነበሩም፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ያነበቧቸውን የስታሊንን እና የማኦኢስት ድርሳናት እንደወረደ በተግባር ለማዋል እንዲጣደፉ የገፉቸው ይመስላል፡፡ ከልምድ እና ከትምህርት እጦት በተጨማሪ የወጣትነት ስሜታቸው ‹‹መገንጠልን›› ለመሰለ ከትግራይ የማህበረ-ፖለቲካ እና የታሪክ አውድ ውጪ ለሄደ ጠርዘኛ አቋም ሳይዳርጋቸው እንዳልቀረ ብዙ ፀሐፊዎች ይናገራሉ፡፡

ማኒፌስቶውም የነዚህ ድምር ውጤት ነው፡፡ከማኒፌስቶው አጭር ቆይታ በኋላ ህወሓት ስትራቴጂውን በመቀየር ‹‹በትግራይ ስኬታማ አብዮት አቀጣጥሎ በሌሎች ጭቁን ብሔሮች የትግል አጋርነት በመላው ኢትዮጵያ በብሔሮች የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል መብት ላይ የምትገነባ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መመስረት›› በሚል ተቀመጠ፡፡

ህንፍሽፍሽ

በ1969 ዓ.ም ሁለተኛ አጋማሽ እና በ1970 ዓ.ም መጀመሪያ ግድም ህወሓት ከውስጥ እና ከውጭ በተፈጠሩበት ተግዳሮቶች ገደል አፋፍ ላይ ለመቆም ተገዶ ነበር፡፡ በአንድ በኩል ከደርግ ጋር ያደርገው የነበረው ጦርነት፣ በሌላ በኩል በጊዜው ከህወሓት አንፃር የተሻለ ወታደራዊ ጥንካሬ ከነበረው ኢዲዮ ጋር እየተዋጋ መክረሙ ፓርቲውን የፈተኑት ውጪያዊ ጫናዎች ነበሩ፡፡ በወቅቱ ከነበረው የኤርትራው ጀብሃ ጋር ከህወሓት ይልቅ የተሻለ ግንኙነት የነበረው ኢዲዮ በተሻለ ወታደራዊ አቅም ላይ መገኘቱ ውጊያውን ለህወሓት አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ ከነዚህ ውጪያዊ ተግዳሮቶች በተጨማሪ የወቅቱ የህወሓት ፈተና የፓርቲው አካላት እጅግ ኢ-ህጋዊ በሆነ እና ከአመራሮቹ እይታ ውጪ በሆነ መንገድ እየተገናኙ መምከር ያዙ፡፡

ይህ ‹‹ህንፍሽፍሽ›› ተብሎ የሚጠራው አደገኛ ውስጣዊ እንቅስቃሴን ከመሩት መሀከል እንደ ሃይሉ መንገሻ ያሉ ቀዳሚ የፓርቲው መስራቾች ይገኙበታል፡፡ አመራሩ ከምዕራብ ትግራይ አውራጃዎች በመጡ ሰዎች ተይዟል ብለው ያመኑት አባላት ለጊዜው አመራር ‹‹አሽአ›› (አድዋ፣ ሽሬ እና አክሱም) የሚል ቅፅል በመስጠት አመራሩን በአውራጃዊነት ከሰሱ፡፡ በምስራቅ እና በደቡብ የትግራይ አካባቢዎች ፓርቲው ወታደራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ አያደርግም፣ በአባላት መሀከል አግባብ ያልሆነ አውራጃዊነትን የተንተራሰ አድሎአዊ ይካሄዳል ፣አልፎም አባላቱ ለአመራሩ በሚያሳዩት ታማኝነት እንደ ቀዳሚ መስፈርት እየታየ ነው የሚሉት የተቃውሟቸው ጭብጦች ነበሩ፡፡ ለማሳያነትም አቶ መለስ በአድዋ ፖሊስ ጣቢያ ላይ እና በአዲ-ዳይሮ በተሰጣቸው ወታደራዊ ተልዕኮ ላይ ያሳዩትን ዝንፈት እና ቅጣት አልባ አካሄድ በመጥቀስ በአመራሩ በኩል አድልኦ ይፈፀማል ማለታቸው በከፊልም ቢሆን ትክክል ነበረ ይላሉ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ፡፡ በጊዜው ህወሓት ሊያዳብረው ከቻገረው ዴሞክራሲያዊ ባህል አንፃር ጉዳዩን ወደ አደባባይ (ለምሳሌ ወደ ኮንግረሱ) ለማምጣት ተቃዋሚዎቹ አለመድፈራቸው ፓርቲው ቀስ በቀስ ከስሩ እንዲገዘገዝ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ሌላው ከስብስቡ መሪዎች መሀከል የፓርቲው መስራች አባላት የነበሩ ታጋዮች መካተታቸው ለ‹‹አሽአ›› አመራሮች ጉዳዩን የሀይል ትግል አድርገው እንዲመለከቱ ዳርጓቸዋል፡፡

በ1970 ዓ.ም ጉዳዩን የሚመረምር ወታደራዊ ካውንስል /ወታደራዊ ባይቶ/ እንዲቋቋም በመወሰኑ በህወሓት የፖለቲካ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አባይ ፀሐዬ መሪነት ምርመራ ተጀመረ፡፡ ምርመራውን የመሩት እና ውሳኔውን በማሳለፍ ቀዳሚ ባለድርሻ የነበሩት አቶ ስብሃት ነጋ አንዳንዶቹ ወደ እስር፣ በሌሎቹ ደግሞ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው አስወሰኑ፡፡ ከመረሸን እና ከእስር የተረፉት የተቃውሞው አባላት ወደ ሱዳን ተሰደዱ፡፡ ጥቂቶችም ‹‹ታሪካዊ ጠላታችን›› ወዳሉት ደርግ ተቀላቀሉ፡፡ አቶ ወልደሥላሴ አስፋው The TPLF: From guerilla to government በሚለው ፅሁፋቸው እንደሚሉት ከስታሊኒስታዊ ዘዬ የተቃኘው የአመራር ቡድን፣ አማራጭ የትችት ሀሳቦችን መታገስ ባለመቻሉ፤ ጥቂት የአመራር አባላቱ ብቻ በሚያውቁበት መንገድ በእንቅስቃሴው አባላት ላይ አሰቃቂ እርምጃ በመውሰድ ተቃውሞውን ለማፈን ሞክሯል፡፡ፕ/ር ገብሩ ታረቀም በበኩላቸው ይህ የግድያ እርምጃ የድርጅቱን ህልውና ለማሰንበት ቢጠቅምም ለዲሞክራሲያዊ ተላምዶት ግን አደገኛ አካሄድ እንደነበረ ይገልፃሉ፡፡

ሴረኛው መለስ?

ወደ ደደቢት ጉዞ ከማድረጉ ጀምሮ ህወሓት ራሱን በማርክሳዊ መነፅር ለመመልከት የደፈረ ግራ-ዘመም ፓርቲ ነበር፡፡ ከምስረታው በተከተሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ብዙ የትግራይ ወጣቶች እና አርሶ አደሮች ወደ ፓርቲው መቀላቀላቸው አንዳንዶቹን የህወሓት መስራቾች ለፓርቲው ግራ-ዘመማዊ ዕይታ ለመስጠት መንቀሳቀስ እንዲጀምሩ አደፋፍሯቸዋል፡፡ በ1970ዓ.ም መጀመሪያ ግድም ራሳቸውን ‹‹ፊተኞቹ›› /መሪሕ ባይታ/ ብለው የሰየሙ የፓርቲው ወጣቶች ስለማርክሲዝም-ሌኒኒዝም መወያየት ጀመሩ፡፡ ወቅቱ ታጋዮች እንደሚናገሩት ይህ ስብስብ ብዙውን ተራማጅ የፓርቲውን ወጣቶች ማቀፍ ችሏል፡፡ ዶ/ር አረጋዊ እንደሚሉት ይህ ስብስብ ራሱን ብሔራዊ፣ አብዮታዊና ዴሞክራሲያዊ ፕሮግራሞች (ብአዲፕ) ተብሎ ለሚጠራው የማኦ ፅንስ-ሀሳብ የተገዛ ነበር፡፡ ሊቀመንበር ማኦ ለደሀ ሀገራት ይሆናል ብለው የሚመክሩት ይህ ሙግት ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ወደ ሶሻሊስት አብዮት እንደሚያመራ ይከራከራል፡፡ የፓርቲው የፖለቲካ ታሪክ እንደሚያሳየው ይህ ስብስብ ቀስ እያለ ወደ ማሌሊት አደገ፡፡

ስለማሌሊት የሚናገሩ ፅሁፎች ለቡድኑ መመስረት የመጀመሪያውን ሀላፊነት የሚሰጡት ለአቶ መለስ ነው፡፡ በእርሳቸው ዙሪያ ስብሃት ነጋ እና አባይ ፀሐዬ መኖራቸውን በማይዘነጋ መልኩ የሰውዬውን አሻራ የበዛ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ህወሓት ሲመሰረት መስራች ከነበሩት መሀከል የመጀመሪያው ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት አባይ ፀሐዬ፣ ስብሓት ነጋ፣ አረጋዊ በርሔ፣ ግደይ ዘርዕፅዮን እና ስዩም መስፍን ሲሆኑ የኮሚቴው ተለዋጭ አባላት ደግሞ መለስ ዜናዊ፣ ስዬ አብርሃ እና አታክልቲ ቀፅላ ነበሩ፡፡ በ1971 የፓርቲው የመጀመሪያ ኮንግረንስ ሶሻሊስታዊ ፓርቲ እንዲመሰረት ተወሰነ፡፡ ኮንግረንሱ ይህን ፓርቲ የማዘጋጀቱን ስራ ለአቶ መለስ ሰጣቸው፡፡ ይህ የኮንግረንሱ ውሳኔ አቶ መለስን ከጦርነት አውድማው አርቆ በሚመሩት የካድሬ ት/ቤት ስራ ላይ እንዲጠመዱ አስቻላቸው፡፡ ካህሳይ በርሔ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው እንደሚሉት ይህ ውሳኔ አቶ መለስን ‹‹የሌት ቅዥታቸው›› ከሆነው የህወሓት እና የደርግ ጦርነት ርቀው እንዲቀመጡ ማስቻሉ ሰውየውን እጅግ ‹‹ደስተኛ›› አደረጋቸው፡፡ ይህን የካድሬ ት/ቤት መቆጣጠራቸውም የፓርቲው ብቸኛ የርዕዮተ-ዓለም ተንታኝ እየሆኑ የሚመጡበትን እድል ከማመቻቸቱ በተጨማሪ በሚቀጥሉት ጊዜያት ሊኖራቸው ለሚችለው ትንቅንቅ በቂ የሀይል መሰረት በታማኝ ካድሬዎቻቸው በኩል እንዲያደላድሉ ሁኔታዎችን አመቻችቶላቸዋል፡፡ የትምህርት ቤቱን የትምህርት ካሪኩለም የሚቀርፁት እሳቸው መሆናቸው ቁጥራቸው የበዛ የግራ-ዘመም አስተምህሮቶችን እንዲመራመሩ አስችሏቸዋል፡፡ ከዚህ በዘለለ ብዙዎቹን ወደ ትግሪኛ ቋንቋ የተተረጎሙ ስታሊኒስታዊ ፅሁፎችን አዘጋጅተዋል፤ አልያም በበላይነት መርተዋል፡፡ ሌሎች አቻዎቻቸው ከደርግ ጋር ሲዋደቁ በኮንግረንሱ ውሳኔ የተነሳ የፓርቲውን ካድሬዎች ለማሌሊት ምስረታ በሚያመቻቹ የማኦኢስት ሀሳቦች አጠመቋቸው፡፡ ‹‹እግረ መንገዳቸውንም›› ይላሉ ካህሳይ እና ተስፋዬ “Two groups of TPLF and Two Issues of Ethiopia” በሚለው ፅሁፋቸው ‹‹ለማሌሊት ምስረታ የሚያግዙአቸውን ካድሬዎችን በብዛት መለመሉ፡፡›› የህወሓት የፖለቲካ ኃላፊ የነበሩት አቶ አባይ ፀሐዬ በማዕከላዊው ኮሚቴ በኩል የአቶ መለስን ሁኔታ በጥንቃቄ እንዲመለከቱ ቢታዘዙም ሀላፊነታቸውን ብዙም እንዳልተወጡ በግልባጩ ሊመለስ የተመቻቹ ውሳኔዎችን ማዕከላዊው ኮሚቴ እንዲወስን ለማድረግ ይታትሩ እንደነበረ እነካህሳይ ይከራከራሉ፡፡ ከሌሎቹ የህወሓት አመራሮች በተሻለ የንባብ ጊዜ ከማግኘታቸው የተነሳ በፓርቲው ውስጥ የሚንሸራሸሩ ፖለቲካዊ ሀሳቦችን በብቸኝነት ለማርቀቅ እንዲያመቻቸው በሚል ማንም የድርጅቱ አባል ማዕከላዊ ኮሚቴውን ሳያስፈቅድ የተለየ ሀሳቡን በፓርቲው ውስጥ ማንሸራሸር አይፈቀድለትም የሚል ህግ በአቶ አባይ ፀሐዬ ትከሻ በኩል በኮሚቴው አስወሰኑ፡፡ ይህ ውሳኔም የሰውየውን ተፅዕኖ አሰፋው፡፡ የቀድሞ የትግል ጓዶቻቸው የመለስን የተፅእኖ ልክ ለማሳየት ህወሓት ፊቱን ወደ አልባኒያ ያዞሩበትን ሁኔታ ይጠቅሳሉ፡፡ እስከ 1970ዎቹ አጋማሽ ድረስ የቻይናው ‹‹የአዲሱ ዴሞክራሲያዊ አብዮት›› አድናቂ የነበረው ህወሓት በቻይናው ኮሚኒስት ፓርቲ ከብሄራዊ ብርሃ እንቅስቃሴ ጋር ህብረት ለማድረግ ስምምነት ላይ ይደርሳል፡፡ የሰሜን አሜሪካ የትግራውያን ማህበር ይህን ጉዳይ የሚያትት አንዲት ጆርናል ለፓርቲው የፕሮፓጋንዳ እና የፖለቲካ ክፍል ይልካል፡፡ ይህንን ያነበቡት አቶ መለስ ቻይናን ከላሽ፣ የኤንቨር ሆጃን አልባኒያ ብቸኛ ሶሻሊስት ሀገር መሆናቸውን አምነው ለማሳመን ብዙ ጊዜ አልጠየቃቸውም፡፡ ይህንን ተፅእኖአቸውንም በሚገባ የሚገልፀው የማሌሊትን ምስረታ አስመልክቶ የተበተነው መግለጫም በዚህ እነ አረጋዊ እና ካህሳይ በሚጠቅሱት ሙግት መሰረት መሞላቱ ነው፡፡

ከ1971ዓ.ም የመጀመሪያው የህወሓት ኮንግረስ ጀምሮ ማሌሊት እስከተመሰረተበት 1977ዓ.ም ድረስ በፓርቲው ወታደራዊ እና ፖለቲካዊ ክንፎች በኩል ምንም ዓይነት ዝምድና እንዳይኖ ሲታትር የነበረው የነመለስ ቡድን ለማሌሊት ምስረታ የሰጣቸው ምክንያቶች ፓርቲው አቅጣጫ የለሽ ሆኗል የሚል ነበር፡፡ በ1983 አጋማሽ ላይ ሃገረ ሰላም ላይ ላገኟት ጄኒ ሃሞንድ ‹‹በ1970ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ህወሓት ከአቅጣጫ አልባነቱ የተነሳ ተገትሮ የቆመ ሰው ይመስል ነበር›› ማለታቸውን ፀሐፊዋ “Fire from ashes: A chronicle of the revolution it Tigray” በሚለው ፅሁፏ ታስነብባለች፡፡ ይህን ሙግታቸውንም ለማስረገጥ በምክንያትነት ያቀረቡት የአንዳንድ የአመራር አባላትን ‹‹ፕራግማቲክነት›› ነበር፡፡ እንደ መለስ ክርክር ህወሓት ከሌሎች አለም አቀፍ የማርክሲስት ሀይሎች ጋር ግንኙነት አለማዳበሩ የአመራሩ ‹‹ወላዋይነት›› እና ‹‹ኦፖርቹኒስትነት›› ሲሆን መፍትሄውም በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ፓርቲውን መግራት ነው፡፡ አቶ መለስ በዚህ ክርክራቸው በመግፋት ህወሓትን ከ‹‹ተገተረበት›› ለማነቃነቅ የሚያስችለው ማሌሊት መሆኑን ለማስረዳት ሞክረዋል፡፡

በ1977ዓ.ም ከሐምሌ 5-18 ለአስራ አራት ቀናት የተካሄደው የማሌሊት ስብሰባ ማሌሊትን የሚመሩ አረጋዊ በርሄንና ግደይ ዘርዐፅዮንን ጨምሮ ሃያ አንድ .አባላትን በመምረጥ ተጠናቀቀ፡፡ አቶ መለስ የማኦን ቃል በመዋስ ‹‹ታላቁ እርምጃ››/Great leap forward/ ሲሉ በሰየሙት በዚህ ስብሰባ አረጋዊ እና ግደይ ከመለስ የተሻለ ድምፅ ማግኘታቸው በአባላቱ ዘንድ በማሌሊት እና በህወሓት መሀከል የጠራ ልዩነት እንደነበረ ለማየት እንደተቸገሩ የሚያሳይ እንደሆነ እነ ካህሳይ ይጠቅሳሉ፡፡ ከቀናት በኋላ የማሌሊት ፖሊት ቢሮ አባላትን እና ዋና ፀሐፊውን ለመምረጥ ውሳኔ ላይ ይደርሳል፡፡ ከስብሰባው በፊት አቶ መለስ ግደይን እና አረጋዊን የተመለከተ አጀንዳ እንዳላቸው ለስብስቡ ያሳውቃሉ፡፡ ከተባረሩት አንዱ የሆኑት ዶ/ር አረጋዊ እንደሚሉት እነ ስብሃት እና መለስ ‹‹የማሌሊትን ምስረታ ለማደናቀፍ ሞክረዋል›› እና ‹‹መለስን ቀድመው ለመምታት አሲረዋል›› የሚል ክስ ለማዕከላዊ ኮሚቴው አቀረቡ፡፡ አቶ ካህሳይ በርሄ በበኩላቸው አቶ መለስ የማዕከላዊ ኮሚቴውን ስብሰባ የመረጡት ሌላኛው አማራጫቸው የነበረው አጠቃላይ ስብሰባ እርሳቸው የሚጠብቁትን ውሳኔ ላያስገኝላቸው ይችል የነበረበትን እድል ከግንዛቤ በማስገባት ነበር፡፡ እንደ ዶ/ር ጆን ያንግ ዘገባ በአቶ

መለስ እና ግደይ መሀከል የ‹‹ርዕዮተ-ዓለም›› ነው የተባለው አስራ ስድስት ሰዓታት የፈጀ ክርክር ተደረገ፡፡ መለስም የቀድሞ ጓዳቸውን ‹‹ፖለቲካ ያልገባው የድርጅቱ ጋንግሪን›› ሲሉ አብጠለጠሏቸው፡፡ ጋንግሪን ደግሞ ተቆርጦ ካልተጣለ በቀር ሰውነትን እንደሚበክለው ሁሉ ግደይም በድርጅቱ ውስጥ ከቆዩ ፓርቲውን እንደሚበክሉ ተነተኑ፡፡ በአቶ አባይ ፀሐዬ መሪነት በተካሄደው በዚህ ስብሰባ አቶ መለስ በካድሬው ት/ቤት በኩል የገሯቸው ካድሬዎች ለክርክራቸው የአሸናፊነትን ግርማ በጭብጨባዎቻቸው ለገሷቸው፡፡ ከዚህ ክርክር በኋላም ግደይ እና አረጋዊ ከድርጅቱ ተሰናበቱ፡፡ አንዳንድ የቀድሞ ታጋዮች እንደሚሉት ሁለቱ አመራሮች ላይ በስብሃት ነጋ በኩል ወታደራዊ እርምጃ እንዲወሰድ ሀሳብ ቢቀርብም አቶ መለስ ‹‹እያበበ ያለውን የማሌሊት ስም ያጎድፋል›› በሚል ሀሳባቸውን እንዳስቀየሯቸው ይናገራሉ፡፡ ካህሳይ በርሄ በበኩላቸው አቶ መለስ የአረጋዊ እና የግደይን እንቅስቃሴ የሚከታተል ቡድን በስራቸው ማቀፋቸውን ይገልጻሉ፡፡ ይህ ቡድንም የሁለቱን ታጋዮች የግል ማስታወሻዎችን ከመዘርዘር ጀምሮ ከነርሱ ጋር የተገናኙትን የፓርቲ አባላት እስከማስፈራራት የደረሰ ስልጣን ነበረው፡፡ እንደ ፓርቲው ታሪክ ተንታኞች አረዳድ ማሌሊትን ተንተርሰው ተገዳዳሪዎቻቸውን ከፓርቲው ማራቅ የጀመሩት አቶ መለስ የህወሓትንም ዋና ፀሐፊነት በ1980ዎቹ መጀመሪያ ማሌሊትን በመጠቀም መያዛቸውን ይገልፃሉ፡፡

ችጋሩ እንዴት ታለፈ?

በቀዳሚው ዓመት ህወሓት በትጥቅ ትግል ወቅት ስለተከሰተው ችጋር እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ አሁን በስልጣን ላይ ባሉት እና ከፓርቲው በተለያየ ጊዜ የተሰናበቱት አመራሮች መሀከል ከፍተኛ ውዝግብ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ዶ/ር ጆን ያንግ “Peasant revolution in Ethiopia” በሚለው ድርሳኑ እንደሚያትተው ቁጥራቸው ሁለት መቶ ሺህ የሚጠጋ የትግራይ ነዋሪዎች እርዳታ ፍለጋ ወደ ሱዳን ሸሹ፡፡ ከሁለት ሳምንታት በላይ በሚፈጀው ጉዞ ዋታቾቹ ነዋሪዎች ከደርግ የአየር ጥቃት ለመሸሽ ቢሞክሩም በሽታ፣ ችጋር እና የዱር አውሬ በመንገዳቸው ያጋጠሟቸው መከራዎች ነበሩ፡፡ አቶ ስዩም መስፍን ለወቅቱ ኮንግረስ አስራ ሶስት ሺህ ነዋሪዎች በመንገድ ላይ መርገፋቸውን አስረድተዋል፡፡ ማሌሊት አጠቃላይ ኮንግረሱን ለማካሄድ ደፋ ቀና በሚልበት ወቅት የተከሰተ መሆኑ እና ቡድኑ የተሻለ ትኩረቱን ለኮንግረሱ መስጠቱ በችጋር የሞቱትን ነዋሪዎች ቁጥር እንደጨመረው ብዙዎቹ የድርጅቱ ታሪክ ፀሐፊዎች ይስማማሉ፡፡ እንደ እነ ዶ/ር አረጋዊ ያሉት በበኩላቸው ማሌሊት በኢምፔርያሊስትነት የሚያማቸው ምዕራባውያን እንዲሸሹ የወሰነው ማሌሊት መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ፅሁፎቹ እንደሚሉት የትግራይ መልሶ ማቋቋም ማህበር ወደ መቶ ሚሊዮን ዶላር አካባቢ ከምዕራባውያን በእርዳታ መልክ ተቀብሏል፡፡ የእርዳታውን አከፋፈል በተመለከተ አቶ መለስ ለማዕከላዊው ኮሚቴ ባቀረቡት ሀሳብ መሰረት ሀምሳ በመቶው ለማሌሊት ማጠናከሪያ፣ አርባ አምስት በመቶው ለህወሓት እንቅስቃሴ፤ የቀረው አምስት በመቶ በችጋር ለተጠቁት ነዋሪዎች እንዲውል ተወሰነ፡፡ የነስብሃት- መለስ ቡድን የአስተያየት ሰጪዎቹን ክርክር ከተሸናፊነት ስነ ልቦና ጋር ቢያያይዘውም የእነ አቶ መለስ ተቺዎች በበኩላቸው ለህወሓት ማጠናከሪያ የተባለው ገንዘብ የጦር መሳሪያዎችን ለመግዛት ውሏል ሲሉ አመራሩን ይወነጅላሉ፡፡ ብዙው የእርዳታ ገንዘብ ስለምን ለማሌሊት ማጎልበቻ ይውላል? ለሚለው ጥያቄ ‹‹ማሌሊትን ካጠናከርን ችግርን ጨምሮ ሁሉም ችግሮች በሳይንሳዊ መንገድ ይፈታሉ›› የሚል መልስ ከነመለስ ቡድን መሰጠቱን ተቺዎቹ ያስታውሳሉ፡፡

ለጋራ ጠላት ሲባል?

ህወሓት በተመሰረተበት ዓመት በኤርትራ በርሃዎች ጠንከር ያለ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ የነበሩ ሁለት ፓርቲዎች ነበሩ፡፡ ህወሓት ከሁለቱም ፓርቲዎች ጋር እየፈረሰ-የሚበጅ ግንኙነት አድርጓል፡፡ አንዳንድ ፀሐፊዎች ህወሓት በተለይም ከሻዕቢያ ጋር የነበረውን የግንኙነት ጅማሮ ወደ ኋላ ይወስዱታል፡፡ ዶ/ር ያንግ እንደሚሉት ከ1967ዓ.ም በፊት ማግበት ከሻዕቢያ ሀይሎች ጋር ግንኙነቱን ጀምሯል፡፡ ፓርቲውም ሲመሰረት በስዩም መስፍን የተመራ ቡድን ለወታደራዊ ስልጠና መረብን ተሻግሮ በሻዕቢያ አማካኝነት መሰረታዊ ወታደራዊ ክህሎትን እና የጦር መሳሪያ እርዳታዎችን አግኝቷል፡፡ ነገር ግን የሁለቱ ፓርቲዎች ግንኙነት እንደ አጀማመሩ አልቀጠልም፡፡ በጊዜው ከህወሓት ይልቅ የተሻለ ድርጅታዊ አቅም የነበረው ኢህአፓ በትግራይ መንቀሳቀስ መጀመሩን ያስተዋለው ሻዕቢያ አይኑን ወደ ኢህአፓ ጣለ፡፡ ጥቂት የአህአፓ ወታደራዊ ክንፍ አባላት /ኢህአህ/ በሳህል በረሃ በሻዕቢያ አመራሮች ስልጠና ተሰጣቸው፡፡ ኢህአፓን በ‹‹ትምክህተኛነት›› የሚፈርጀው ህወሓትም በዚህ ግንኙነት ደስተኛ ባለመሆኑ እርዳታ ፍለጋ ወደ ጀብሃ ተሻገረ፡፡ በህወሓት እና በጀብሃ በኩል የነበረው ግንኙነት እንዲጠናከር ያደረገው ሻዕቢያ ወደ ኢህአፓ ከመዞሩ በተጨማሪ ጀብሃ በአሁኑ የባድመ አካባቢ ያደርግ የነበረው ወታደራዊ እንቅስቃሴ እንደነበር ዶ/ር ጆን ያንግ ይጠቅሳሉ፡፡ ይህንን የጀብሃን እንቅስቃሴ በመንተራስ የራሱን ፍላጎት ሊያሟላ እንደሚችል ያሰበው ህወሓት ከፓርቲው ጋር ግንኙነቱን ለማጠናከር ሞክሯል፡፡ ምፀታዊ በሆነ መንገድ ይህ የሁለቱ ታጣቂ ፓርቲዎች መልካም ዝምድና ሌላ ተግዳሮት ገጠመው፡፡ ጀብሃ ሌላኛውን የትግራይ ነፃ አውጪ ፓርቲ /ቲሌሌ/ መደገፍ መጀመሩ ለፓርቲው ግንኙነት መፍረስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ኢህአፓ ሻዕቢያ ያቀረበለትን የኤርትራን የቅኝ ግዛትነት ጥያቄ አልቀበልም ማለቱ ኢህአፓን ከጀብሃ ጋር ሲያወዳጀው፣ ህወሓትን ደግሞ ወደ ቀደመው አገሩ ሻዕቢያ እንዲመለስ አደረገው፡፡ ከዚህ ወታደራዊ ትብብርም ከተገኘ ድርጅታዊ ጥንካሬ በመነሳት ህወሓት ኢህአፓን ከትግራይ ሲያባርር፣ አቶ ስብሓት እንደሚሉት ጀብሃን ከሻዕብያ ጋር በመተባበር ከኤርትራ በርሃ አራቁት፡፡

የሻዕቢያ እና የህወሓት ግንኙነት በመበጠስ እና በመቀጠል የተቃኘ ነው፡፡ ህወሓት የኤርትራን ጥያቄ በ‹‹ቅኝ-ግዛትነት›› መቀበሉ እና በውስጣዊ እና ውጪያዊ ግፊት ትግራይን የመገንጠሉን አላማ መቀልበሱ ለሻዕቢያ የድጋፍ መነሾ ሲሆን፣ ከወታደራዊ ስልጠና እና ድጋፍ በተጨማሪ የሻዕቢያ ትግል የደርግን አቅም ከማመናመን አንፃር በውጤቱም የጋራ ጠላትን ከማድከም በሚል በህወሓት በኩል የተወሰደው አቋም አንዳንዶች ‹‹በታላቅ እና በታናሽ›› የሚመስሉት ግንኙነት መሰንበት ምክንያቶቹ ናቸው፡፡ ነገር ግን ህወሓት ኤርትራ ውስጥ ስለሚገኙት ብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጉዳይ ላይ ያሳየው ርዕዮተ-ዓለማዊ ድርቀት እና ሻዕቢያ ከመገንጠል በመለስ በኦቶኖሚ መፍትሔ ዙሪያ እስከመደራደር መሄዱ ለግንኙነታቸው መበጣጠስ በምክንያትነት ይነሳሉ፡፡

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

# ሃያ ነጥብ ሶስት

‹‹20.3›› ይህ ቁጥር የኤፍ ኤም /FM/ ሬዲዮ ጣቢያ ቁጥር አይደለም፡፡ ወይም እድገትን ለማሳያ የተቀመጠ ባለሁለት ዲጂት /digit/ መከራከሪያ አይደለም፡፡ ቁጥሩ በገዛ ሀገራችን ነፃነት አጣን፣ ያልሆነውን ናችሁ ተባልን፣ ፍትሕ ተዛባብን የሚሉ ኢትዮጵያውያን በታጐሩበት እስር ቤቶች ሆነው የሚያስላስሉት፤ ሰሚ ባያገኙም በየፍርድ ቤቱ የሚጮኹበት የሀገሪቱ ሕገ-መንግስት አንቀፅ ነው፡፡ ባለፈው ሳምንት ረቡዕ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሀገሪቱ ፓርላማ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ ከተቃዋሚዎች ወገን ብቸኛው ተወካይ አቶ ግርማ ሰይፉ ይህ አንቀፅ በመንግስት በኩል እየተጣሰ ነው በማለት ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በፌዝ በታጀበ ምላሻቸው ሕገ-መንግስቱን እንደ አስፈላጊነቱ እየተረጐማችሁት እንጂ በመንግስት በኩል ምንም የሕግ ጥሰት አልተደረገም ብለው ነበር፡፡ ለመሆኑ የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ ምን ይላል? አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 3. የተከሰሱ ሰዎች መብት በሚል ርዕስ ስር የተቀመጠ ሲሆን እንዲህ ይላል ‹‹በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው፡፡››

እንግዲህ ይህ አንቀጽ ነው በአቶ ግርማ ሰይፉ በመንግስት እየተጣሰ ነው የሚል ክስ የቀረበበት፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲመልሱ ህገ-መንግስቱን እንደ አስፈላጊነቱ እየተረጐሙ ጥፋትን ለመከላከል መሞከር እንደማይችል ከገለፁ በኋላ በመጀመሪያ በእስር ላይ ያሉት እና የተከሰሱት ግለሰቦች ጥፋተኛ አይደሉም እያላችሁ መግለጫ ስትሰጡ የነበራችሁት ራሳችሁ ናችሁ፡፡ መንግስት የምታደርጉትን ነገር ከታገሰ በኋላ ራሱን ለመከላከል በሚል ከሰዎቹ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ጉዳዮችን ይፋ አድርጓል ብለዋል፡፡ ተቃዋሚዎች በተለያዩ ጊዜያት የታሰሩባቸውን አባሎቻቸውን እንዲሁም ሌሎች ጋዜጠኞችን አስመልክተው መግለጫ ሰጥተው ይሆናል፡፡ ይህ አካሄድ ክሱ በሂደት እስካለ ድረስ ምንም እንኳ በፍርድ ቤቶቹ ነፃ የዳኝነት ችግር እንዳለባቸው ቢገመትም በፍርድ ሂደት ባለ ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት ሕገ-መንግስቱን የተከተለ አካሄድ አይደለም፡፡ በተወሰነ መልኩም የዳኝነትን ሂደት ሊያዛባ የሚችልበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ከመንግስት ወገን ግን እንዳየነው በተለያዩ ዶክመንተሪ ፊልሞች በክስ ላይ ያሉ እና ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ያሉ ግለሰቦችን እያቀረቡ በተከሰሱበት የሽብርተኝነት ወንጀል ወንጀለኛ እንደሆኑ ሊያሳዩ የሚችል እና ከተለያዩ በዚህ መንግስት ሽብርተኛ ተብለው በተመደቡ ቡድኖች ጋር በማገናኘት ተከሳሾቹ የሰጡትን ምላሽ በቴሌቪዥን መስኮት በተደጋጋሚ በማቅረብ በተከሰሱበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውን መንግስት ሲወተውት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለ ማስረጃ የታሰረ አንድ ሰው የለም ይህንንም በቅርብ ቀናት ውስጥ ለህዝቡ ይፋ እናደርጋለን ብለው እንደነበር የቅርቡ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ባሉት መሰረትም ጉዳዩ በፍርድ ቤት እየታየ በመሀል በተለያዩ ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዙ ፊልሞች ተያያዥነት በክስ ላይ ያሉ ግለሰቦችን በማቅረብ ጥፋተኛ አድርገው ማቅረባቸውን አይተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክስ ተመስርቶባቸው የነበሩ ግለሰቦች በራሳቸው ላይ እና በሌሎች ተከሳሾች ላይ የምስክርነት ቃል ሲሰጡ አስተውለናል፡፡ ሌላው ጉዳይ ክሱን እስከ መጨረሻ ድረስ ተከራክረው የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጣቸው ግለሰቦች ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ሳይቀሩ በራሳቸው ላይ የምስክርነት ቃል እንዲሰጡ ሊያግባቡን ሞክረዋል ማግባባቱ አልሳካ ሲል በተለያዩ መንገዶች ጫና ፈጥረውብናል በማለት ፍርድ ቤት በቀረቡ ቁጥር ህጐችን እየጠቀሱ አቤት ብለዋል፡፡

ዋናው ጉዳይ ይህ በተቃዋሚዎች ተፈፅሟል የተባለው እና መንግስት በቴሌቪዥን መስኮት በተከሳሾች ላይ ያቀረበው የጥፋተኝነት መንፈስ ይዞ የመጣው ሀተታ ሕጋዊ ነው? ወይም ሕገ-መንግስቱን የተከተለ ነው? ወይስ አይደለም የሚለው ጥያቄ ነው? የጠቅላይ ሚኒስትሩም ምላሽ ሊሆን ይገባው የነበረው መንግስታቸውም ፈፀመው ተቃዋሚዎች ጉዳዩ ሕገ-መንግስቱን መሰረት ያደረገ ነው አይደለም የሚለውን ጥያቄ መመለስ ላይ ነው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሰጡት ምላሽ ግን ተቃዋሚዎች የተከሰሱት ግለሰቦች ጥፋተኛ አይደሉም የሚል ፕሮፓጋንዳ መንዛት ሲጀምሩ መንግስት ራሱን ለመከላከል ያደረገው ነው በማለት ነው፡፡ ይህ ምላሽ መንግስት በክስ ላይ ባሉ ግለሰቦች ላይ የወሰደውን የጥፋተኝነት መግለጫ ሕጋዊ ማድረግ አይችልም፡፡ ሕገ-መንግስቱንም እንደ አስፈላጊነቱ መተርጐም ማለት ይሄ ነው፡፡ በእርግጥ ተቃዋሚዎች በተመቻቸው መልኩ ሕገ-መንግስቱን ተርጉመው መጠቀሚያ አድርገውት ሊሆን ይችላል ግን መንግስት ተቃዋሚዎች እንደ አስፈላጊነቱ ስለተረጐሙት እኔም እንደ አስፈላጊነቱ ተርጉሜ ራሴን እከላከልበታለሁ የሚለው መከራከሪያ የፓርላማ አባላትን ፈገግ ሊያሰኝ፣ አልያም እንደ አንድ የፖለቲካ ማጣፊያ ሊወስድ ይችላል ነገር ግን በየትኛውም መመዘኛ ህገ-መንግስቱን መሰረት ያደረገ ሕጋዊ አካሄድ አይደለም፡፡ ስለዚህ በ20.3 የተቀመጠውን ተከሳሾች በፍርድ ሂደት ወቅት እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር ሕገ-መንግስታዊ መብታቸው ተጥሷል፡፡ በሕግ የተቀመጠው በተለይ ሕገ-መንግስት የሚደነገገው ሀገሪቷ ህግን መሰረት ባደረገ ማዕቀፍ ውስጥ ሆና እንድትንቀሳቀስ ለማድረግ ሲሆን ማንኛውም መንግስት፣ ባለስልጣን ወይንም ሌላ ግለሰብ ከሕግ በላይ ሆኖ በሀገሪቷ ውስጥ እንዳይንቀሳቀስ ለማገድ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በደንብ አስምረውበት ሲናገሩ እንደነበረው የአንድን መብት ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ እየደፈሩ ስራን መስራት እንደማይቻል የሲውዲናውያን ጋዜጠኞቹ ሀገር ደፍረዋል ሀገርን እየደፈሩ ስራ መስራት አይቻልም በማለት ምሳሌ እየጠቀሱ ተከራክረዋል፡፡ የፀረ-ሽብርተኝነቱ ህግ በአንድ ወገን አንድ የህግ አውድ ሲሆን በሌላ ወገን ደግሞ ከሕገ-መንግስቱ የበላይ ሆኖ ተቀምጧል፡፡ አንድ መንግስት በፀረ-ሽብርተኝነት የከሰሳቸውን ግለሰቦች ሕጋዊ በሆነ መልኩ ሽብርተኛ ናቸው ብሎ የሚያምን ከሆነ ሕጉን ተከትሎ በፍርድ ቤት ስራ ጣልቃ ሳይገባ፣ ተከሳሾቹ ሳይፈረድባቸው እንደጥፋተኝነት ሳይቆጠሩ የሚከራከሩበትን መንገድ በማመቻቸት ከሌሎች የህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር በማደጋገፍ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉን /ምንም እንኳ ህጉ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ በሀገራችን በነፃ የመንቀሳቀስ መብታችንን ይገድባል በሚል ተቀባይነቱ ዝቅተኛ ቢሆንም/ ዋቢ በማድረግ፣ ማስረጃዎችን በመዘርዘር ሊያስቀጣቸው የሚችልበትን የሕግ መስመር መከተል ይገባዋል፡፡ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕጉን ተከትሎ ሽብርተኞችን ለማስቀጣት ነው እያለ ሕጋዊነቱን የሚደሰኩር መንግስት ሕገ-መንግስቱን ካልጣሰ የሀገርን ሉዓላዊነት ደፈሩ ከተባሉት ጋዜጠኞች በምን ይለያል?አንድ ሕግ እየጣሱ /በተለይ ደግሞ የሀገሪቷን የበላይ ሕግ ሕገ-መንግስቱን/ ሳይከተሉ ሌላውን ላስፈፅም ነው ይሄን ያደረኩት ብሎ መከራከር ሚዛን አይደፋም፡፡

አንቀፅ 20.3 ከዚህ ሌላ በውስጧ የያዘችው አበይት ነጥብ ተከሳሾች በምስክርነት እንዳይቀርቡ ያለመገደድ መብት ነው፡፡ ተከሳሾች በዚህ አንቀፅ መሰረት በራሳቸው ላይ ተገደው በምስክርነት መቅረብ /ክሱን በግዳጅ ማመን/ ወይም ለሌላ ክስ በግዳጅ ምስክር ሆነው ያለመቅረብ መብት አላቸው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ተከሳሾች በመጀመሪያው የክሱ ሂደት ወቅት ጥፋተኛ አይደለንም ብለው ሲከራከሩ ከቆዩ በኋላ በሂደት በራሳቸው ላይ እና በአንዳንድ ተከሳሾች ላይ ምስክርነት የሰጡበት ሁኔታ ነበር፡፡ ከዚህ ሌላ በእስር ላይ እያሉ በራሳችሁ ላይ መስክሩና /ክሱን እመኑና/ ትለቀቃላችሁ እየተባልን ነው ይህንን እንድናደርግ በከፍተኛ ባለስልጣናት ሳይቀር ጫና ይደረግብናል ብለው እየወተወቱ ይህ ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ሳይጣራ ፍርድ የተሰጣቸው ህገ-መንግስቱን መሰረት አድርጐ ነው ወይ እንድንል ያደርገናል፡፡ ይህን የተከሳሾች መብት በበቂ ሁኔታ ስናከብር በየፍርድ ቤቱ እያመላለሱ መጨረሻ ውሳኔ መስጠት በፍትሕ ስርዓቱ ላይ የአምባገነንነት ስርዓት መጫን ስለሚሆን የፍርድ ቤቶች ዋጋ እንዲቀንስ ስለሚያደርገው የሕጉን መኖር አላስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ዋናው ጉዳይ ተቃዋሚዎች እንዳስፈላጊነቱ ተርጉመው እየተጠቀሙበት ስለሆነ መንግስትም ይህን ለማጣፋት ሰፋ ያለ የመከላከያ ፕሮፓጋንዳ ከሕገ-መንግስቱ ውጭ ማድረግ ይችላል የሚለው መከራከሪያ እንዳስፈላጊነቱ ተተረጐመ የተባለውን አንቀፅ ለመተርጐም እንዳስፈላጊነቱ ሕጋዊ አለመሆን ነው፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡

---

## የአብዮቱ ደወል... ከገፅ 9 የዞረ

የሁለቱን ዝምድና ያጠኑት ፕ/ር ገብሩ ታረቀ ሻዕቢያ ባይኖር ህወሓት ህልውናው ሊያከትም ይችል የነበረ ቢሆንም፤ ካለህወሓት ግን ሻዕቢያ ቢገፋ ኤርትራን የመገንጠል ህልውና በጥቂት ዓመታት ሊራዘምበት ይችላል ሲሉ ይደመድማሉ፡፡

ከትግራይ ወደ ኢትዮጵያ

የህወሓት ትጥቅ ትግል አስቀድሞ የተነሳለትን አላማ እውን ለማድረግ 1980ዎቹ መግቢያን መጠበቅ ነበረበት፡፡ ከረጅም እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ ሁሉንም የትግራይ መንደሮች ከደርግ አገዛዝ ቀንበር ነፃ ማውጣት የቻሉ ቢሆንም በቀጣይነት ምን መደረግ አለበት በሚለው ስትራቴጂካዊ ግብ ላይ በመንታ መንገድ ቆሙ፡፡

የመጀመሪያው አማራጭ ቀዳማይ ወያኔ የሞከረው እና ያልተሳካው የትግራይ አብዮት በዳግማዊ ወያኔ መሳካቱ በራሱ በቂ ስለሆነ ወታደራዊውን ዘመቻ እዚሁ ጋር በመግታት ትግራይን ብቻ ከልሎ እየጠበቁ መቀመጥ (ነፃ ትግራይ ክልል መመስረት) የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ አዲስ አበባ ላይ የከተመውን ደርግ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የማያዳግም እርምጃ ካልተወሰደበት በስተቀር በመልሶ ማጥፋት ተደራጅቶ ለህወሓት ታጋዮች (የትግራይን ህልውና ጨምሮ) በቀጣይነት አደጋ መፍጠሩ አይቀርም የሚል ነበር፡፡

በመጨረሻም የፓርቲው ከፍተኛ የአመራር አባላት የደርግ ስርዓትን ለማስወገድ ከተፈለገ ጉዳዩ የትግራዊያን ብቻ ሳይሆን ጭቆናው የመላው ሀገሪቷ ብሔሮችን ስለሚወክል በአጠቃላይ ከሌሎች ብሔር ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን መቀጠል አለበት በሚለው ላይ መግባባት ላይ እንዲደርሱ አስችሏቸዋል፡፡

የአመራሩ ውሳኔ ሁለት ውጤቶች ነበሩት፡፡ የመጀመሪያው ፓርቲው ለረጅም አመት ‹‹የትግራይ ህልውና›› ላይ ብቻ ያጠነጠነው ርዕዮተ አለማዊ አቋም ወደ ተቀረው ኢትዮጵያ ክፍል ማዘመትን ጨምሮ ከሌሎች ታጋይ ቡድኖች ጋር በጋራ ለመስራት የመዘጋጀት ለውጥ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትግሉን ጨርሰናል ብለው ለተቀመጡት የተቀሩት አባላት እና ደጋፊዎች ቀጣይ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዳለ ማስረዳት ናቸው፡፡

እነዚህን ሁለት ውጤቶች ሌላ ምዕከታም ነበራቸው፡፡ የህወሓት ቀጣይ እርምጃ ‹‹በባዕዳን መሬት ላይ›› የሚደረግ አላስፈላጊ ትግል አድርገው ይወስዱ የነበሩ ግለሰቦች መኖራቸው፣ የህወሓት ትግል ከመሰረታዊ ትግራይን በብቸኝነት አጥሮ የመቆየት ህልም ጋር እንደሚቃረን መረዳት እንችላለን፡፡ ይህንን ርዕዮተ አለማዊ ሽግግር ምሁራኑ ‹‹ከትግራይ ወደ ኢትዮጵያ›› ሲሉ ይጠሩታል፡፡

የአመራሩ አባላት ይህንን ቢያምኑም ከዚህ በተቃራኒ አብዛኛው በትግሉ ታሳታፊ የነበሩ ግለሰቦች የዚህን ስትራቴጂ ለውጥ በበጐ ጐኑ አልተቀበሉትም፡፡ ‹‹አላማችን የትግራይን መሬት ነፃ ማውጣት ነበር ይህንንም አሳክተናል፡፡ ከዚህ በኋላ አንዳችም መስመር ለማለፍ አንፈልግም፡፡ አማራ፣ ኦሮሞ እና ሌሎችም ተጨቁነናል ብለው የሚያምኑ ድርጅቶች ለራሳቸው ችግር እራሳቸው መፍትሄ ሊያበጁለት ይገባል›› የሚል አቋም ነበራቸው፡፡

ለረጅም አመት አብረው በትግል ያሳለፉ የባልደረቦች፣ ለቀጣይ ትግል ሂደት ላይ ያሰሙት የተቃውሞ ድምፅ ለህወሓት ታጋዮች ከፍተኛ ችግር እንደፈጠረባቸው እሙን ነው፡፡ የህብረተሰቡ ይሁኝታ ለማግኘት ይችል ዘንድ አመራሩ በሁሉም አቅጣጫ ያካሄዳቸው የለውጥ እርምጃዎች፣ የጥንካሬ ምስክሮች ናቸው፡፡

የህወሓት መሰረታዊ ‹‹ትግራይን የመገንጠል›› አባዜ በከፍተኛ አመራሮች ዘንድ ከጥንት ጀምሮ በዋናነት ይቀነቀን ነበር የሚሉት ተንታኞች የአንቀፅ 39 (የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል) የሚለውን እና በቅድመ ስልጣን ወቅት የኤርትራን መገንጠል የደገፉበትን አካሄድ በመንተራስ፣ ህወሓት አሁንም ቢሆን ትግራይን ለችግር ጊዜ ማምለጫ አድርጐ ይወስዳታል ብለው ያምናሉ፡፡

ወደ ሳልሳዊ ወያኔ?

በ1970ዎቹ መጨረሻ ህብረ-ብሔራዊ የነበረውን ኢህዴንን በማበጠር ፓርቲውን ለአማራ ህዝብ የሚታገል ለማስመሰል ብአዴን በሚል ስያሜ አስጠርቶ ህብረት ከመሰረተ ጀምሮ የቀድሞ የደርግ ወታደሮች የነበሩ የሻዕቢያ ምርኮኞችን በኦህዴድ አማካኝነት አዋቅሮ ኢህአዴግ የሚል ፓርቲ የፈጠረው ህወሓት ከ1983ዓ.ም ወዲህ ያለው ታሪኩ ከትግል አላማው እጅግ የራቀ እንደሆነ የቀድሞው የፓርቲው ታጋዮች ይናገራሉ፡፡ ለብሔር፣ ብሔረሰብ የእኩልነት መብቶች ታግያለሁ የሚለው ህወሓት ወደ ስልጣን ከመጣበት ወቅት ጀምሮ ይህን አፈ-ሀሳቡን /rhetoric/ የሚንድ ተግባር ውስጥ ተዘፍቋል፡፡ አራቱን የወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ እና ዳውሮ ብሔሮችን በመጨፍለቅ ‹‹ወጋጎዳ›› የሚል ስያሜ በአንድ የብሔር ከረጢት ውስጥ ሊከታቸው ሞክሯል፡፡ መሰረታዊ የአገሪቱ የፖለቲካ ጥያቄ ነው ብሎ ለሚያምነው ‹‹የብሔር ቅራኔ›› ችግር መፍትሔ ያለውን ቋንቋ-ተኮ ፌዴራሊዝም ለማስተዋወቅ በመሞከሩ ሀገሪቱ የገጠማት ተግዳሮትም የህወሓትን የክስረት ታሪክ የሚያሳብቅ ይመስላል፡፡ የህወሓቱ ፌዴራሊዝም ጎሳዊነትን ከማፋፋት /re-tribalization/ ውጪ አንዳች ጠቀሜታ የለውም ከሚሉት ፕ/ር አሊ ማዙር በዘለለ ኢትዮጵያን በአንድ ፓርቲ አምባገነንነት ከመግዛት ውጪ የተሻለ አማራጭ የላችሁም የሚል ምክር ለአቶ መለስ በመምከሩ የምናስታውሰው ሳሙኤል ሀቲንግተን በዚህ ጉዳይ ላይ በህወሓት መሪዎች ላይ ከፍተኛ ትችት ይሰነዝራል፡፡ ዜጎችን በብሔራቸው ለመለየት መሞከር የቀድሞዎቹ የሶቭየት ህብረት እና የደቡብ አፍሪካ ግርሻ ነው የሚለው ፕ/ር ሀቲንግተን ብዙዎቹ የሀገሪቱ ዜጎች ከአንድ በላይ ከሆኑ ብሔሮች ጋር ከመዋረሳቸው አንፃር ቋንቋን ማዕከል አድርጎ ስርዓቱን ማዋቀር እጅግ ታላቅ ስህተት ነው ሲል ይወቅሳል፡፡

የህወሓት ልሂቃን የብሔሮችን ግጭት በተመለከተ የፌዴራሊዝሙ ሙከራችን መፍትሔ ሰጪ ነው ሲሉ ቢከራከሩም በጉዳዩ ላይ የሚፅፉ ምሁራን በበኩላቸው በግልባጩ ይሟገታሉ፡፡ የፌዴራሊዝሙ መንገድ የሀገሪቱን የብሄር ቅራኔ ከማባባስ ውጪ ሌላ ጥቅም እንዳለው የማይታያቸው ፕ/ር ኤድሞንድ ኬለር በበኩላቸው ቋንቋ-ተኮሩን ፌዴራሊዝምን በተመለከተ የተሳካ ሊባል የሚችል ሀገራዊ ሙከራ በማንም ሀገር አለመከሰቱን በመጥቀስ ባለፉት ሃያ ዓመታት በፓርቲው የአመራር ዝንፈት የተነሳ የተከሰቱ እጅግ ብዙ ቁጥር ያላቸው የብሄር ግጭቶችን በምክንያት በማቅረብ ፓርቲው ስርዓቱን ወደ አሃዳዊነት ለማንሸራተት እንደጠቀመው ይከራከራሉ፡፡

በፌደራሊዝም ስርዓት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ብሔር-ተኮር ግጭቶችን በተመለከተ ምሁራን በመፍትሔነት የሚያቀርቡት ሁለት አማራጮችን ነው፡፡ እነርሱም የዴሞክራሲያዊ ስርዓት መጎልበት እና የግለሰብ እና የቡድን መብቶች መጠበቅ ናቸው፡፡ ዶ/ር ሎቪስ አለን እንደሚሉት ማዕከላዊ መንግስቱ የጋራ ሀገራዊ ዜግነትን ለማጎልበት ከሰራ የብሄር ግጭቶች በተሻለ ሁኔታ ሊቀንሱ አልያም ጭራሹኑ ላይፈጠሩ ይችላሉ፡፡ እንደ ዶ/ሩ ሙግት የፓርቲው ሁሉ አቀፍ አካሄድ ከአንድ የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል ጋር በተዛምዶ የሚፈረጅ ከሆነ የጋራ ዜግነትን ለመፍጠር ፓርቲው የሚሄድበት አካሄድ ብዙም አትራፊ አይሆንም፡፡ ህወሓት በዚህ በኩል በቂ የኪሳራ ታሪኮች አሉት፡፡ ሀገራዊ የጋራ ማንነት የለም ከሚለው የታሪክ ተቃርኖው ጀምሮ፤ በ1997ቱ ምርጫ እንዳደረገው ራሱን የትግራይ ብቸኛ ተከላካይ አድርጎ ለመሳል መታተሩ በብሔሮች መሀከል ከፍተኛ የሆነ የቅራኔ ስሜት እንዲፈጠር አስገድዷል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም ፓርቲው የቀድሞውን መስራች አባላትን ጭምር ከ‹‹ነፍጠኞች›› ጋር አብረዋል ብሎ እስከመክሰስም ሄዷል፡፡ ከአመታት በፊት የወጣው የአይሲሲ ዘገባም ኢትዮጵያ ላለፉት ሃያ ዓመታት የገጠሟትን ዓይነት ብሔር ተኮር ግጭቶች ህወሓት በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ልትሻገረው አትችልም፣ ይህም ከባድ ሀገራዊ ጉዳትን እንድታስተናግድ ሊያስገድዳት ይችላል የሚል ሪፖርት እስከማውጣት አስኪዶታል፡፡ አሁን አሁን በብሔር ግጭት የሚታመሱ ብዙ ዜጐችም ኃላፊነቱን በፓርቲው ላይ በመጫን ህወሓት የአተነኳኳሽ ሚና እንደነበረው በይፋ እስከመናገር ሄደዋል፡፡

ከዚህ የአላማ ክስረት በተጨማሪም አመራሩ በአንድ ሰው የብቻ የሁለት አስርታት መሪነት መሰንበቱ በጋርዮሻዊ /Collective/ አመራር ዴሞክራሲያዊነት ሲመካ ለነበረው ህወሓት የራዕይ ድቀት ዜና እንደሆነ ብዙ ፀሐፊዎች ይስማማሉ፡፡ በ1993ቱ የፓርቲው መከፋፈል ወቅት የፓርቲውን ውስጠ ደንብ በመጣስ ተገዳዳሪዎቻቸውን ከመንገዳቸው ያገለሉት አቶ መለስ ህወሓትን በተተኪ አልባነት ለማዋቀር እንዲሞክሩ አስችሏቸዋል፡፡ በወቅቱ የስልጣን መተጋገል የረዷቸው አቶ ስብሃት ነጋም ከፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ የመገለል ዕጣ ገጥሟቸዋል፡፡ እንደብዙ ተንታኞች ክርክር ወ/ሮ አዜብ መስፍን በህወሓት ውስጥ ሁለተኛው ሰው ለመሆን ስልጠናቸውን ማደላደል ከጀመሩ ሰንብተዋል፡፡ ቢያንስ ከ1993ዓ.ም ወዲህ በተካሄዱት የፓርቲው የኮንግረስ ስብሰባዎች አቶ መለስን ሊተካ የሚችል ተገዳዳሪ ሰው ወደአደባባዩ ለመውጣት አለመቻሉ ለ‹‹ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ታግያለሁ›› ለሚለው ህወሓት ወደ ሙት ፓርቲነት መቀየር ማሳያ ይመስላል፡፡ የቀድሞ ጉሬላ ታጣቂ ቡድን በአንድ ሰው ብቸኛ መሪነት መመራት አዲስ አይደለም የሚሉት ኮልበርን በጠባቂነት (Vanguard) መንፈስ ራሳቸውን የሚመለከቱ የሶሻሊስት ታጣቂ ስብስብ መሪዎች በትጥቅ ትግል ዘመኖቻቸው የአመራር ዘያቸውን ርዕዮተ-ዓለማዊ ልባስ በማከናነብ አልፎም ትግሉ ግድ የሚለውን ጠንካራ የስነ-ስርዓት መዋቅር በመዘርጋት የስልጣን መሰረታቸውን ያደላድላሉ፡፡ ፕ/ር ፍሬዴሪክ ኮልበርን ‹‹The Vogue of revolution in poor countries›› በሚለው ስራቸው እንደሚሉት ይህን መሰል ፓርቲ የሚመሩ ፖለቲከኞች ፓርቲው ወደ ስልጣን ከመጣም በኋላ ማዕከላዊ መንግስቱን በብቸኝነት ለመምራት የሚያስችሏቸውን ሁኔታዎች ያመቻቻሉ፡፡ በተለይም በትጥቅ ትግል የጣሉት ስርዓት አምባገነን ከመሆኑ የተነሳ ወደ ስልጣን ሲመጡ የሚመሯቸውን ፖለቲካዊ ተቋማት ዴሞክራሲያዊ ከማድረግ ይልቅ ባሉበት ለማቆየት ይሰራሉ፡፡ እንደ ፕ/ሩ ክርክር የፓርቲው መሪዎች በትጥቅ ትግሉ ዘመን ካዳበሩት ልማድ በተጨማሪ እነዚህን ተቋማት በመጠቀም የፓርቲውም ሆነ

ወደ ገፅ 13 ዞሯል

# ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የመንግሰት ሃላፊ ወይስ አማካሪ?



ግርማ ሠይፉ ማሩ
girmaseifu32@yahoo.com

ጥር 30 በተደረገው የተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ መነሻነት ብዙ ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ ተገቢው መልስ ከመንግሰት እስክንሰማ ድረስ ውይይቶቹ ወደፊትም ይቀጥላሉ ብዬ አስባለሁ፡፡ ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ከምክር ቤት ስብሰባ በኂላ ያደረግነው ውይይት ግን ለዚህ ፅሁፍ መነሻ ሆኖኛል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለምክር ቤቱ ያሰሙት ሪፖርት ተጠያቂ በሆነ ጠቅላይ ሚኒሰትር ሳይሆን አንድ ተቀጣሪ ባለሞያ አማካሪ የሚያቅርበው ሪፖርት ነው የሚመሰለው አለኝ፡፡ ዕውነቱ ነው፡፡ የሰማሁት የመንግሰት ሌባ የሚለው ቃል ብዛት በእርግጥ ከመንግሰት ሃላፊነት በመነጨ ሳይሆን ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ ተቀጣሪ አማካሪ በተደረገ ማጣራት የተገኘን ግኝት ሪፖርት የቀረበ ነው ያስመሰለው፡፡ ይህ ሪፖርት የአማካሪም ይሁን የጠቅላይ ሚኒስትር የስድስት ወር የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ይህንኑ መሰረት አድርገን ግን አስተያየት መሰጠት እንችላለን፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ሪፖርቱን የተሟላ ለማድረግ የመንግስት ሌቦች የሚባሉት ባለው መረጃ መሰረት ተከፋፍሎ በአባል ድርጅትና በአጋር ድርጅት ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ግልፅ ቢደረግ አይጠቅምም ብለው ያስባሉ? ለዚህ ተጠያቂው ማን ነው? ሰርዓቱን ‹‹አጨማልቀውታል›› የተባሉት እነዚህ መንግሰትን የሚወክሉት ሌቦች እነማን ናቸው? መቼም አቶ ያረጋል አይሸሹም እና የሰበታ ማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች ጦስ ብቻ አይደለም ይህንን ጦሰኛ የሊዝ አዋጅ እንዲታዘዝብን መንስሔ የሆኑት፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ይህንን ሪፖርት ለመንግሰት በአማካሪነት በማገልገል አይደልም የደረሱበት እና የነዚህ የመንግስት ሌቦች አለቃ እርሶ መሆኖ ግልፅ ነው፡፡ በግልፅ እንነጋገር ከተባለ የሚሾሙት እርሶ ስለሆኑ ሌቦቹን ያሰማሩብን እርሶ መሆኖን መዘንጋት ያለቦት አይመስለኝም፡፡ መቼም የአባል እና አጋር ድርጅቶች እነዚህን ሌቦች መልምሎ በማቅረብ የተጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ የእርሶ ኃላፊነት ግን ተገቢውን የቁጥጥር ስርዓት ዘርግተው መከታተል እና ሲያጠፉ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ማሰናበት ነው፡፡ ጉዳት ከደረሰ ግን ተጠያቂው እርሶ መሆኖ የግድ ይላል፡፡ አሁን እንደሚነግሩን ጉዳት ደርሷል (የመንግሰት ሥርዓት ተጨማልቆዋል) ለዚህም ዘግይተውም ቢሆን እርምጃ እየወሰዱ አይደልም ሰለዚህ ተጠያቂነዎትና ሃላፊነቱን ይውሰዱ፡፡ ምክንያቱም በመንግሰት ሃላፊነት እንጂ በአማካሪነት አይመሰለኝም የጠቅላይ ሚኒስትርነቱ ቦታ የያዙት፡፡

የግል ሌቦችንም በተመለከተ ከተጠያቂነት ማምለጥ የማይችሉት በግል ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና የጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግሰት መሆናቸው ለክርክር የሚቀርብ አይደለም፡፡ መንግሰት አንዱ ሃላፊነቱ ዜጎችን ከወንጀለኞች መጠበቅ ነውና፡፡ ሌብነት ደግሞ ወንጀል መሆኑ ለሁሉም ግልፅ ነው፡፡ አሸባሪዎች በህንድ አንድ ሆቴል ላይ ባደረሱት ጥቃት የደህንንት ሚኒስትሩ ከስልጣን መልቀቃቸው ለሁላችንም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ በከፍተኛ ሃላፊነት ላይ ያሉ ሃላፊዎች መቼ ነው ለተፈጠረው ጥፋት ሃላፊነት ወስደው ከሰልጣን የሚለቁት የሚለው ሁሌም ያሳስበኛል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ተግባር ለዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ካለው ጥቅም አንፃር ሲገመገም ማለቴ ነው፡፡በኛ ሀገር ከስልጣን ሲወርዱ አብረው የሚወርዱ ብዙ የኤኮኖሚና የማህበራዊ ተግዳሮቶች አሉ፤ ለዚህም ተጠያቂው ወደ ስልጣን የሚወጡና የሚያወጡት ሰዎች የሥልጣን መወጣጫ መሰላሉን እያቆሸሹ ሰለሚወጡ፤ ሲወርዱ መጀመሪያ የሚጨማለቁት እነርሱ እራሳቸው ሰለሚሆኑ ነው፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ሌላው የተምታታውን ምላሽ የታዘብነው የመንግሰትና የግል ሌቦች መኖራቸው እንደ ዋነኛ ችግር ተወስዶ መፍትሔ ተብሎ የተቀመጠው ግን በሊዝ ስም የግል ባለይዞታዎችን ሀብት ዋጋ የሚያሳጣና ኢትዮጵዊነትን ፈተና ላይ የሚጥል የሊዝ አዋጅ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የሊዝ አዋጅ የግል ባለይዞታዎችን ብቻ ሳይሆን በሊዝ ቦታ ይዘው ንብረት ያፈሩ ሰዎችም ቢሆኑ የሊዝ ስምምነት ከፈረሙበት ቀን ጀምሮ ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ ሀብት ነው የሚኖራቸው፡፡ ይህ ኢንቨስትመንት ያበረታታል የሚለው ተጨፈኑ ላሞኛችሁ ማብራሪያ ብዙ ውሃ የማይቋጥር መሆኑን ለመረዳት በሀገራችን የሚኖረውን የውጭ ኢንቨስትመንት በቅጡ መገምገም በቂ ይመስለኛል፡፡

የመንግሰት የመሬት የሊዝ ዋጋ እየጨመረ ሲሄድ በተቃራኒው ከገበያ ህግ ውጭ ዋጋው የሚቀንስን የግል ንብረት ለመታደግ እነዚህ የመንግሰት ሌቦች መንገድ እንደ ማይጠፋቸው ማሰብ አይቸግርም፡፡ በዚህ የመውጫ በር ፍለጋ ድራማ የግል ሌቦችም ትብብር የሚጠፋ አይመስለኝም፡፡ ሌቦችን ለማጥፋት የታቀደው እርምጃ ሌቦችን ከመፍጠር ውጭ ሌቦችን ለመከላከል አያስችልም የምለው ለዚህ ነው፡፡ የእግር ጫማው ለጠበበው ሰው ሰፊ ኮፍያ እንደማዘዝ ነው፡፡ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ እንደሚባለው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሌላ በግልፅ የካዱት እውነት ግን በአዋጁ አንቀፅ 6/1 የተቀመጠውን የግል ይዞታ በሚመለከት የተደነገገውን ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የተሰጠው መልስ ይህ የሊዝ አዋጅ የግል ይዞታን ወደ ሊዝ ስለማዛወር የሚመለከት ነገር የለውም ያሉት ነው፡፡ ይህንን ፍርድ ፍትሐዊ ለማድረግ ይህን ዝርዝር መግለጫ ለአንባቢያን እንዲያነቡት መጋበዝ ነው የምመርጠው፡፡ የተከበራችሁ አንባቢዎች ይህችን አንቀፅ 6/1 አንብቧት፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩን መልስም በልቦናችሁ አስታውሱት፡፡ ከተቻለ በድጋሚ ለማድመጥሞክሩ፡፡ ግን ለምን ይዋሻል ብለን ብንጠይቅ ተገቢ አይደለም?

በሌላ በኩል የማስቀየሻ መልስ የተቸረው ጥያቄ ኢትዮጵያ ጥቅሟን ለማስከበር ምን ዓይነት የመከራከሪያ ነጥብ እንዳነሳች ኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት ምስረታ ከውስጥ ፖለቲካችን ዘለን ምን አደረግን በሚል ለቀረበ ጥያቄ የኩዋሜ ነኩርማ ሃውልት ለምን ቆመ እንዳልን ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህ ትክክል አይደለም፡፡ አሁንም መልስ የሚፈልገው ጥያቄ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመሩት መንግስት ሀውልት ሊቆምላቸው በሚገባ መሪዎች ዙሪያ ምን አቋም አራመደ የሚለው ነው፡፡ ወይስ ቻይናነች የመረጠችው? ሌሎቹን በሌላ ቦታ ስላነሳኂቸው በዚሁ ይብቃኝ፡፡ ቸር ይግጠመን፡፡

---

# እውነቱ ማን ጋ ነው?

ዳንኤል ተፈራ

አቶ መለስ ወደ ፓርላማ ቀርበው ስድስት ገፅ ያለው ድንክዬ ሪፖርት ካቀረቡ አንድ ሳምንት አለፋቸው፡፡ በያዝነው ዓመት ለሁለተኛ ጊዜ ማለት ነው፡፡ መስከረም መጨረሻ ፕሬዘዳንት ግርማ ፓርላማውን በቡራኬ ከከፈቱ በኂላ በማግስቱ ነበር ፓርላማ የተገኙት፡፡ በዚያን ጊዜ ማብራሪያና ማስፈራሪያ ቀላቅለው ማቅረባቸውን የምንዘነጋው አይሆንም፡፡ በተለይ ደግሞ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ባለተራ የነበሩበት ነው፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ እስከ ዶቃ ማሰሪያቸን ነበር የነገሩን፡፡ እግዜር ይስጥልን፡፡

በዓመቱ መግቢያ የፓርላማ ውሎአቸው ከጋዜጠኞች በተጨማሪ አንድነትና መድረክም ዋና ኢላማዎች ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ መቼስ የፖለቲካን ሀሁ የሚያውቅ ሁሉ እነዚህ አካላት የአቶ መለስ ኢላማ መሆናቸው እንዲሁ በብላሽ እንዳልሆነ ይረዳል፡፡ ለወሬ ማጣፈጫ ነው የሚል የዋህም አይኖርም፡፡ ነገርየው የ‹‹ላጥላጥ›› አይነት የካርታ ጨዋታ ነው፡፡ የስማቸውን በየቦታው መደንጉር አስመልክቶ አንድ የአቶ መለስ ፓርቲ ተቀናቃኝ የሆኑ ግለሰብ እንደገለፁት፡- ‹‹አስቀድሞ የመምታት፣ የማስበርገግና ተገዳዳሪነትን የማርገብ ስራ ነው፡፡›› ሲሉ ይተቻሉ፡፡ ቀጥለውም ሀሳባቸውን እንዲህ ያፍታቱታል፡- ‹‹አቶ መለስ ፓርላማ ሲመጡ ደርሰንባችኂል፣ ነቅተናል፣ መቶ ፐርሰንት፣ ክምር ማስረጃ …እያሉ ስጋታቸውን ለማራገፍ ይጥራሉ፡፡ በዚያውም ተቃዋሚዎቻቸውን በማሳጣት ለፓርቲያቸው ጥርጊያውን ያበጃሉ፡፡ ከዚያ የሚቀበል ይቀበላቸዋል፡፡ የተነቃበት ጨዋታ ይመስለኛል፡፡›› ሲሉ ያጠቃልላሉ፡፡ አመሰግናለሁ አስተያየት ሰጭ፡፡ ይሄው ስምዎትንም ደብቄያለሁ፡፡

እንደገና ረቡዕ፣ ጥር 30 ቀን 2004ዓ.ም አቶ መለስ ፓርላማ የቀረቡበት ቀን ነው፡፡ አጭር ሪፖርት አቅርበው ሰፊ ማብራሪያ ከማደናገሪያ ጋር ያቀረቡበት እለት ነው፡፡ የውሃ ብርጭቆአቸውም ስራ በዝቶበት ነበር፡፡ በተደጋጋሚ ውሃ ሲጠጡም አስተውያለሁ፡፡ የስድስት ወሩን ሪፖርታቸውን ስንጨምቀው ስድስት አንኳር ጉዳዮችን እናገኝበታለን፡፡ የኢኮኖሚ እድገቱ እንደተተነበየው መሳካቱና መቀጠሉ፣ የዋጋ ግሸበት መቆጣጠር መቻላቸውን፣ ኪራይ ሰብሳቢነት እየደረቀ መምጣቱን፣ በደቡብ ሱዳንና በሰሜን ሱዳን መካከል ግጭት እንዳይነሳ በአብዬ ግዛት ሰላም ማስፈናቸውን፣ ስለኤርትራ መንግስት የቀንዱን ማተራመስ ስትራቴጂና የሻዕቢያ ተላላኪ ያሏቸውን በማንሳት ነው ሪፖርታቸው የሚጠቃለለው፡፡

የዛሬ ፅሁፌ ዋና ትኩረት የጠቅላይ ሚንስትሩን ሪፖርት መዘርዘር አይደለም፡፡ ያው እንደተለመደው አቶ መለስ ወደ ፓርላማ ሲቀርቡ በርካታ ሊያነጋግሩን የሚችሉ ጉዳዮችን ጫርጫር ያደርጋሉ፡፡ ለዛሬም ከሰጡት ማብራሪያ መሀል አንዱን መዝገፄ በማውጣት እውነቱ የት ጋ እንደሆነ ለማጣራት ወደድሁ፡፡ እናም እነሆ ከግራና ከቀኙ፡-

ግንቦት ወር 2001ዓ.ም፡፡ ኢህአዴግ እጅግ ስራ የበዛበት ዓመት ነበር፡፡ 2002 ምርጫ እየተቃረበ ነው፡፡ በዚህ ላይ ያየ97ቱ የሚባል ምርጫ ከተካሄደ በኂላ የመጣ ምርጫ ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ መንደር ከቆፈኑ የተላቀቀ አይመስልም፡፡ እናም አንድ ነገር መሰማት ተጀመረ “Code of conduct for political parties campaigning in democratic election.” የሚል ነው፡፡ ይሄው ሰነድ የፓርቲዎች የምርጫ ስነ-ምግባር በሚል ተተርጉሞ እንደቀረበ እናስታውሳለን፡፡

አቶ መለስ ‹‹እንከን የለውም›› ስላሉት ኮድ አፍ ኮንዳክት ጥቂት ልበል፡፡ የተዘጋጀው ስዊድን ሀገር ሲሆን የመጀመሪያ ረቂቁ የተዘጋጀው እንደ ነጮች አቆጣጠር በ1998 ነው፡፡ አዘጋጁ ደግሞ በምህፃረ ቃል “International IDEA” በመባል የሚታወቀው “International Institute for Democracy and Electoral Assistance” የሚባል አለም አቀፍ ተቋም ነው፡፡ ዴሞክራሲ ይሰፍን ዘንድ ተፍተፍ የሚል ተቋም፡፡

የስቶኮልሙ ሰነድም የ2002 ምርጫ ከመድረሱ በፊት በእንግሊዝ አምባሳደር አቅራቢነት ተተርጉሞ በኢህአዴግ በኩል ጥሪው ተላለፈ፡፡ ‹‹ኑ የስነ- ምግባር ደምቡን እንፈርም፡፡ የጋራ ም/ቤትም እናቋቁም›› የሚል እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ እንደተለመደው ከነመፈጠራቸው የማናስታውሳቸው ወይም እንድናስታውሳቸው የሚያደርግ አንድ ስራ ያልሰሩ እንዲሁም በባልና በሚስት ብቻ የሚመሩ ፓርቲዎች ከየጉናቸው መውጣት ጀመሩ፡፡ አቶ በረከት በመጽሀፋቸው ‹‹እንደተለመደው እናንተ ካላችሁ ይሁን፣ እናንተ ካዘጋጃችሁት እንስማማለን እያሉ ስንጠራቸው አቤት ስንልካቸው ወዴት ይሉናል፡፡›› ያሏቸው ተንሸራታች ፓርቲዎች እና ‹‹በትልቁ ሰውዬ›› ሲመራ የነበረው ፓርቲም ለመፈረም ተሰለፉ፡፡ ፈረሙ፡፡ ‹‹አያ በሬ ሆይ ሳሩን አየህና ገደሉን ሳታይ›› ወዲያው መተረት ጀመረች፡፡

እኛም እንደጋዜጠኛ ‹‹ይሄ የምርጫ ስነ ምግባር ይዘቱ ምንድን ነው? ከየት የመጣ ሰነድ ነው? የማን ሰነድ ነው?...›› የሚሉ ጥያቄዎችን እናኘርጉደት ገባን፡፡ ወዲያው ደግሞ ‹‹መድረክ ይሄንን የምርጫ ስነ-ምግባር አልፈርምም ብሎ ረግጦ ወጣ›› የሚለው ወሬ ጮማ ዜና ሆኖ ከተፍ አለ፡፡ በዚያውም የመድረክና የኢህአዴግ ፍጥጫ ተጧጡፎ ቀጠለ፡፡ ቀን መጣ፣ ቀን ሄደ፡፡ የ2002 ምርጫም በኢህአዴግ ጠቅላይነት ተጠናቀቀ፡፡

ባለፈው ሳምንት ረቡዕ አቶ መለስ እንደገና የስቶኮልሙን ሰነድ አነሱ፡፡ ምርጫ ደረሰ እንዴ? የሚል ጥያቄ ወዲያው አቃጨለብኝ፡፡ አሀ! ከፊት ለፊታችን የአዲስ አበባ ምርጫ ቆሟል፡፡ ሰውየው ያለነገር አንዲት ነገር አያነሱም፡፡ ፓርላማ ቀርበው ለፓርቲያቸው ጥርጊያ ማበጀቱን አይዘነጉም፡፡ እናም ወደ አቶ ግርማ ሰይፉ እያነጣጠሩ መድረክ ለተባለው ፓርቲ መልእክት አስተላለፉ፡- ‹‹ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ስታንዳርድ የሆነውን፣ ሊያግባባን የሚችለውን የምርጫ ስነ-ምግባር ስትፈርሙ የጋራ ሰነድ ሳይኖረን መናገር አንችልም›› በማለት የመድረክን የእንነጋገር ጥያቄ ውድቅ አደረጉ፡፡ እንደለመዱት መስመር አበጁ፡፡ ይሄ ንግግራቸው ያው ጥያቄ የሚያጭር ነበር፡፡

ቀዳሚው ጥያቄዬ ግን ጠ/ሚኒስትሩ ‹‹ከኤርትራ መንግስት ጋር በሽማግሌም፣ ያለሽማግሌም፤ አደራዳሪ ባለበትም፣ በሌለበትም፤ ታዛቢ ቢኖርም ባይኖርም በፈለጉት ጉዳይ የፈለጉት ቦታ ድረስ ሄደን ለመደራደር ዝግጁ ነን፡፡›› ሲሉ አልሰማሁም እንዴ?

እንዴ! አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ ብሎ ከፎከረ ጋር፤ ድንበር ጥሶ እየገባ ከሚገደልና ከሚያግት ጋር፤ በሱማሌ በኩል እያስታጠቀ ጦር ከሚሰብቅ ጋር ለመደራደር ይሄን ያህል ቀና ከሆኑ ምነው የሀገር ልጅ ከሆነውና በሰላማዊ መንገድ እየተንቀሳቀሰ ካለው መድርክ ጋር ለመደራደር እንዴት ከበደዎት???

ወደ ዋናው ኮድ ኦፍ ኮዳክት ስናልፍ ግን በአቶ መለስ ‹‹ፈርሙ›› እና በመድርክ ‹‹አንፈርምም›› ላይ ወዳለው ልዩነት እናመራለን፡፡ የስዊድኑ ሰነድ ላይ እንዳነበብኩት በ2001ዓ.ም ‹‹የኛዎቹ›› ፓርቲዎች ከተፈራረሙት የምርጫ ስነ-ምግባር ውጭ ሁለት ሰነዶችን ይዟል፡፡ አንደኛው “Code of conduct for the ethical and professional observation of elections.” የሚል ሲሆን በዋናነት የምርጫ ታዛዎች ሊያሟሉ የሚገባቸውን ስነ-ምግባር ያትታል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ “Code of conduct for the ethical and professional administration of elections.” የሚል ሲሆን በምርጫ ሙያዊ አስተዳደር ላይ ያነጣጥራል፡፡ የኢህአዴግ የምርጫ ስነምግባር እነዚህን ሁለቱን ባለማካተቱ ይመስለኛል የፈረሙ አንፈርምም ግብግብ የተፈጠረው፡፡

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ይህንን አስመልክቶ ‹‹የምርጫ ታዛቢነት ስነ ምግባሩና የምርጫ አስተዳደር ስነ-ምግባሩ የት አለ?›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ ጥያቄውን ያቀረቡት ደግሞ የስዊድኑን ኮድ ኦፍ ኮንዳክት በማምጣትና ከመንግስት ጋር በማደራደር ከፍተኛ ስራ በዝቶባቸው ለነበሩት የእንግሊዝ አምባሳደር ነው፡፡ ዶ/ር ነጋሶ እንደነገሩኝ አምባሳደሩ ለአቶ መለስም አንስተውላቸው ‹‹ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ኮድ ኦፍ ኮንዳክት አምጡልኝ›› እንዳሏቸው አምባሳደሩ በትህትና ይገልፃሉ፡፡

ከዚያስ? ‹‹ከዚያማ ይሄ ነገር መልካም ነው ክቡር አምባሳደር፡፡ ነገር ግን የቀሩት ሁለት ሰነዶችም ይካተቱና ሌሎችንም ጉዳዮች ጨምረን እንወያይባቸውና ለሁላችንም የሚጠቅም ነገር እናድርግ›› ብለዋል ብለው ለአቶ መለስ እንዲነግሩልን መልእክት ላክን፤ አምባሳደሩን፡፡ መለስና ኢህአዴግ ግን የለም ሌሎች አያስፈልጉም፡፡ የሚያስፈልገው የፓርቲዎች የስነ-ምግባር ደንብ ብቻ ነው ብሎ እምቢ ስላለ እኛ አይ እሱን ብቻ እማ አንፈርምም ብለን እምቢ አልን፡፡›› ይላሉ ዶክተሩ፡፡

አምባሳደሩስ? ‹‹አምባሳደሩማ የጀመረውን የማደራደር ተግባር አጠንክሮ በመፈፀም ፈንታ እኛን ወደ ማስገደድ አደላ፡፡ በኂላም ከፈለጋችሁ ፈርሙ ካልፈለጋችሁ ተዉት አይነት እንድምታ ያለው መልእክት አስተላለፈልን፡፡ እኛም ተውነው፡፡ ሌሎች አራት ፓርቲዎች ፈረሙትና ፓርላማ ፀድቆ የሀገሪቱ ህግም ሆነ፡፡ በቃ አለቀ፡፡ የሀገሪቱ ህግ ከሆነ እንደገና ያልፈረሙ ምናምን ማለቱ ምን ይጠቅማል፡፡ ፈረንጆች ግን አሁንም ያው ናቸው፡፡›› በማለት ይመልሳሉ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፡፡ ያውም በቁጣ!

ኢህአዴግ በበኩሉ ሌላ የመከራከሪያ ነጥብ ሲያነሳ እንሰማለን፡፡ በ18/01/2002ዓ.ም የኢህአዴግ ጽ/ቤት ኃላፊ በሆኑት በአቶ ሙክታር ከድር በተፃፈ የምላሽ ደብዳቤ ላይ፡- ‹‹..ለመደራደር ያቀረብንላችሁን ጥያቄ ከተቀበላችሁ በኂላ ሌሎች ተቃዋሚዎች ባሉበት አንደራደርም፡፡ የኛ ፍላጐት በተናጠል መደራደር ነው ብላችሁ ሂደቱን ረግጣችሁ፡፡›› ይልና ወደ ድርድሩ እንዲመለሱ ይጠይቃል፡፡ እዚህ ላይ ያለው ልዩነት እንደማስታውሰው የመድረክን አጀንዳ ሌሎች ተቃዋሚዎች ስለማይጋሩት አይመለከታቸውም አይነት ነው የመድረክ መልስ፡፡

ዛሬም ክርክሩ ቀጥሏል፡፡ አቶ መለስም ‹‹ካልፈረማችሁ ድርድር የሚባል ነገር አይታሰብም›› የሚል የደረቀ አቋም የያዙ ይመስላል፡፡ ተቃዋሚዎችም ሌሎች ጉዳዮችስ ወዴት አሉ? እያሉ ይመስላል፡፡ ደውሉ ተደውሏል፡፡ ግብግቡም ይቀጥላል፡፡ ቀን ይመጣል፣ ቀን ይሄዳል፡፡ ምርጫም እንደዚሁ፡፡ የሚጠቅመው ግን ሆደ ሰፊ መሆን ነው፡፡ ኢህአዴግም ሆነ ተቃዋሚዎች ለሀገር እስከቆማችሁ ድረስ የሚጠቅም የሚጠቅመውን ብታደርጉስ? አቶ መለስ ሆይ ተቃዋሚዎ የምንነጋገርበት ጉዳይ አለ ካሉዎት ለሀገር እስከጠቀመ ድረስ ቢነጋገሩ? ብትደማመጡስ? ብትግባቡስ… ምን ታጣላችሁ? ምንም፡፡

# አዲሱ የ‹‹ዴሞክራሲያችን›› ፈሊጥ: ‹‹ሃይማኖትህን ልምረጥልህ››



ኢስሃቅ እሸቱ
(የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት ኮፒ ኤዲተር)

ለዚህ ጽሑፌ መነሻ የሆነኝን ምክንያት አስቀምጬ መጀመሩ ምቹ መስሎ ታዩኛል:: እነሆ! ዐርብ ዐርብ ከዐይኔ ፍጹም የማልለያት ፍትሕ ጋዜጣ በየካቲት ሁለት እትሟ 3ኛ ገጿ ያወጣችው ጽሑፍ ነው ዛሬ ብእሬን እንዳነሳ የጋበዘኝ:: ጽሑፉን የጻፉት የዕድሜ ባለጸጋው የተከበሩ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሲሆኑ ‹‹ከጎሣ ልዩነት ወደ ሃይማኖት ልዩነት? ያዋጣል?›› ብለውታል:: ርእሱ ብዙ የመናገር አቅም ያለው የነፍሰጡር ሐረጎች ውቅር የ‹‹ከፋፍለህ ግዛ››ን አስከፊነት በቅጡ የሚገልጽ! ከምስጋና ልጀምር:: ብዙዎቹ የአገራችን ልሂቃን ደፍረው ሊጽፉበት ያልፈቀዱትን ርእስ አንስተው ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እየተፈጸመብን ያለውን በደል በግልጽ በማንሣታቸውና አጀንዳችንን አጀንዳቸው በማድረጋቸው ታላቅ ምስጋና ይገባቸዋል:: በቀልድ ወዛ እያደረገ ያለንበትን ሁኔታና ችግር ለማሳየት የሞከረው ‹‹አቤ ቶኪቻው››ም እንዲሁ ባለበት ምስጋናዬ ይድረሰው:: አንዱ የኅብረተሰብ ክፍል የገጠመውን ችግር ሁሉም ተባብሮ ማስወገዱ የ‹‹አፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል›› ብሂላችን መገለጫ በመሆኑ ሌሎች ምሁራኖቻችንም እየደረሰብን ያለውን ችግር በማሰማቱ፣ ጽምጻችንን በማድመጡ፣ እንዲሁም በማስተጋባቱ ረገድ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሳላስታውስ አላልፍም:: ‹‹ምሁራኖቻችን ሆይ! የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ችግር የናንተም ችግር ነው! እናም ትኩረት ልትሰጡት ይገባል!›› ብዬ አስታውሻለሁ::

የክቡር ፕሮፌሰሩ ጽሑፍ ላይ የጎደሉ አንዳንድ ነጥቦችን አስተውያለሁ:: መታረም የሚገባቸው ጥቂት ስህተቶችም ይኖራሉ:: ሆኖም እኒህ ስህተቶች የተፈጠሩት ስለጉዳዩ በቂ መረጃ ካለማግኘት እንደሆነ ስለተሰማኝ ጉዳዩን በቋሚነት የምከታተል ጋዜጠኛ እንደመሆኔ መጠን ያለብኝንና ያለኝንም ለመጠቆም ተነስቻለሁ::

ፕሮፌሰሩ ጽሑፋቸውን ሲጀምሩ የጠቀሱት የ 1987ቱ ግርግር የተጠናቀቀው ‹‹ገላጋይ›› ሆኖ የተገኘው መንግሥት በወሰዳቸው የጅምላ እስር እርምጃዎች ነበር:: ብዙዎች ‹‹መንግሥት ጥርስ የነከሰባቸውን ሰዎች በሰበቡ ደቁሷል›› ሲሉ የሚያምኑትም ለዚሁ ነበር:: የሰሞኑ የአሕባሽ ውሸንፍር የብዙ ዜጎቻችንን ቆዳ እየገሸለጠ የሚገኘውም ‹‹የመደቆሻ ሰበብ ፍለጋ ነው›› የሚል እምነት አለኝ፤ ብዙዎችም ይህንኑ እምነቴን ይደግፋሉ::

አሕባሽና ጀሌዎቹ ከመንግሥት በኩል ከፍተኛ ድጋፍ እየተደረገላቸው መሆኑን ያለምንም ማፈር በስብሰባዎቻቸው ሲናገሩ በስፋት ተደምጠዋል:: በድምጽም ጭምር ተቀድተዋል:: መንግሥትም ቢሆን ብዙ ለመደበቅ አልሞከረም:: ይልቁንም አሕባሽን የተቃወሙ ሙስሊሞችን በጅምላ እያሰረ፣ እያንገላታና ቤቶቻቸውንም እየበረበረ ቆይቷል:: አሁንም ወከባው አልቆመም - በተለይ በገጠሪቱ ክፍሎች በየቀኑ ሰዎች በገፍና በግፍ ይታሰራሉ:: ተቃውሞው ግን ተፋፍሞ ቀጥሏል:: ‹‹ሙስሊሞች ለምንድነው አሕባሽን የሚቃወሙት?›› የሚለውን ጥያቄ መመለሱ ነው ወደዋናው የመነሻ ሐሳቤ የሚወስደኝ::

ፕሮፌሰሩ ስለአሕባሽ ኢንተርኔት ላይ ባደረጉት መጠነኛ ዳሰሳ ዐራት ነጥቦችን አስቀምጠዋል:: ሦስቱ ላይ የምስማማ ቢሆንም ‹‹በጣም ሰላማዊና ከሁሉም ጋር የመቀራረብ ዝንባሌ ያለው መሆኑን›› ሲሉ በአራተኛነት ያስቀመጡት ነጥብ ግን ከአሕባሽ እውነተኛ ባሕሪ ጋር ክፉኛ የሚጋጭ መሆኑንና በአገራችን የገጠመው ተቃውሞም በዚሁና በሌሎቹም አመለካከቶቹ ምክንያት መሆኑን በዚህ ጽሑፌ ማስረጃ እያቀረብኩ እሞግታለሁ::

አጭር መጠይቅ ላስቀድም:: ‹‹አሕባሽ ሰላማዊ ከሆነና የ‹ከፋፍለህ ግዛ› ስትራቴጂ አካል ካልሆነ ለምን ዛሬ እንዲመጣ ተፈለገ? ከ‹ሕገ አራዊት› ትችታቸው ጋርስ እንደምን ይስማማል?››

<u>አሕባሽ ሰላማዊ አይደለም! ሆኖም አያውቅም!</u>

የተከበሩት ፕሮፌሰር ኢንተርኔት ላይ ያገኟቸው ስለአሕባሽ ሰላማዊነት የተጠቀሱ ነገሮች ቡድኑ ስለራሱ የሚያሠራጫቸው ሐሰቶች በመሆናቸው ከፕሮፓጋንዳነት በፍጹም የዘለሉ አይደሉም:: ሰዉ ‹‹ሰላማዊ እንደሆኑ እንዲያስብ›› እነሱ ብዙ ጥረዋል:: እኔ ደግሞ የደበቁትን ጸረ ሰላም አስተሳሰባቸውን ከመሥራቹ ዐረብኛ መጽሐፍት (ከዋናው ምንጭ) ቀጥታ ቀድቼ ይኸው አቅርቤላችኋለሁ::

አሕባሽ በገባበት አገር ሁሉ ሃይማኖታዊ ብጥብጥ የማስነሳት ከፍተኛ ዝንባሌና ባሕሪ ያለው ሃይማኖት ቀብ የፖለቲካ አንጃ (pseudo-religious political faction) ነው:: መሥራቹ ኢትዮጵያዊው ሼኽ ዐብደላ ሐረሪ ሲሆኑ በ1948 በእኩይ አስተሳሰባቸው ምክንያት በደረሰባቸው የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የተቃውሞ ግፊት ከአገር የወጡና ወደእስራኤል የሄዱ ሰው ናቸው:: እዚህ ላይ አንድ መጠይቅ አለ:: ‹‹ሰላማዊ ሙስሊም ሼኽ በእርግጥም ሰላማዊ ከሆነ እንደምን በሕዝብ ይጠላል? እንዴትስ የመገለል ተፅእኖ ከአገሩ ያሳድደዋል?››

በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ ሼኹ የከተሙባት ሊባኖስ በቅርብ ጊዜ ታሪኳ የሃይማኖት ግጭት ሰለባ እንጂ የሰላም አገር ሆና አታውቅም:: አሕባሽ የተባለው ቡድን ደግሞ አገሪቷ ውስጥ ትልቅ ተጽእኖ ማሳረፍ የቻለ ድርጅት ነው:: ታዲያ ሰላሙ ወዴት አለ?

<u>ለምን ሰላማዊ አልሆኑም?</u>

አሕባሽና የሰላም ችግሮቹ የሚመነጩት እኒሁ መከረኛው ሼኽ ዐብደላ ሐረሪ ለቡድኑ የደለደሉት የአስተምህሮ መሠረት ቀድሞውኑ ለሰላም ጸር በመሆኑ ነው:: የሼኹ በርካታ መጽሐፍት ከርሳቸው አመለካከት ውጭ ያሉ ሙስሊሞችን በሙሉ ‹‹ሙስሊሞች አይደሉም›› ሲሉ የሚፈርጁ በመሆናቸው ዋና ዋና የሚባሉ የእስልምና ሊቃውንት በሙሉ የሳቸው ዱለኝነት ሰለባ ሆነዋል:: ‹‹ተዐውን ዐለነህይ ዐኒል ሙንከር›› የተሰኘው የሼኽ ዐብደላ ሐረሪ አነስተኛ መጽሐፍ የዘመናችንን የእስልምና ሊቃውንት አንድ ሳያስቀር በ‹‹ኩፍር›› (ከእስልምና በመውጣት) ይፈርጃል:: ይህ ዱላቸው ግን በሙስሊሙ ላይ ብቻ ተወስኖ ቢቀር ቢያንስ አንድ ነገር ነበር:: ችግሩ ግን የሰውየው መጽሐፍት ‹‹ሙስሊሞች አይደሉም፤ ከእስልምና ወጥተዋል›› በሚሏቸው ሰዎች ላይ ሁሉ እንዲሠሩ የሚያበረታቷቸው ፀያፍ ተግባራት ለክርስትያኑም ሆነ ለሌሎች ሙስሊም ያልሆኑ ኀብረተሰቦች ሁሉ የሚተርፉ በመሆናቸው ነው - ከሙስሊሙ አልፈው ማለት ነው:: እጅግ ጥቂቶችን ብቻ መርጬ ላስቀምጥላችሁ::

*ሥርቆት*

የትኛውም ጤነኛ ማኅበረሰብ ሥርቆትን አይደግፍም፤ እንደመልካም ተግባርም አያየውም:: የትኛውም ሃይማኖት ተከታዮቹን ‹‹ሥረቅ›› ሲል አያዝዝም:: ይህን መሠረታዊ እውነታ የዐብደላ ሐረሪ መጽሐፍ ከሙስሊሞች አዕምሮ ‹‹ዲሊት›› ሊያደርግ ሲታገል ይስተዋላል::

ሼኹ ‹‹ቡግየቱ ጧሊብ›› በተባለ መጽሐፋቸው (3ኛ እትም ገጽ 243) ላይ አንድ ሙስሊም ሙስሊም ካልሆኑ ጎረቤቶቹ (ከእስልምና ወጥተዋል ያሏቸውን ሙስሊሞችም ይጨምራል) እንዳይያዝ ተጠንቅቆ መሥረቅ የሚችል መሆኑን የጻፉ ሲሆን በ‹‹ሙሐመድ ኢብን ሱዑድ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ›› የዶክትሬት መመረቂያ ጥናቱን በቡድኑ ላይ የሠራው ዶክተር ሰዕድ ኢብኑ ዐሊይ ይህንኑ የሼኹን ሐሳብ ‹‹ፊርቀቱል አሕባሽ›› በተሰኘው ጥልቅ ጥናቱ በገጽ 1214 ክፉኛ ተችቷል:: የሼኹ አስተምህሮ ‹‹በራስህ ላይ እንዲሠራ የማትሻውን በሌላው ላይ አትሥራ›› ከሚለው የነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) አስተምህሮ ጋር ምንኛ እንደሚጣረስ ያስተውሉ!

አገራዊ ተጽእኖውን ደግሞ ያስተውሉት! በሚሊዮን የሚቆጠሩት ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከክርስትያን ወንድሞቻቸው ‹‹ተጠንቅቆ መሥረቅን›› እንደሚፈቀድ ተግባር (ሐላል) ቢመለከቱ ምን ያህል ቀውስ እንደሚፈጠር ለአፍታ እናስበው! ፕሮፌሰሩ ‹‹ሕገ አራዊት›› ሲሉ በሚገልጹት ሥርዓት የሚመራ ዓለም አይፈጠርምን?

ሌላም ምሳሌ ማየት እንችላለን:: ‹‹ሶሪሁል በያን›› በተባለው መጽሐፋቸው (የዳረል መሻሪዕ 3ኛ እትም/2008) ገጽ 521 ላይ ሼኹ የሚከተለውን ብለዋል፡- ‹‹…እንዲሁም (የሙስሊም ባልሆነ ግዛት ውስጥ) የበከተን (ሥጋ) ቢሸጥላቸው ወይም በቁማር ገንዘብ ቢበላቸው ይህ ገንዘብ ለሱ ንጹህ ነው::››

ይታያችሁ! አንድ ሙስሊም በክርስትያን ጎረቤቶቹ ላይ እንዲህ ዓይነት በደል እንዲፈጽም መገፋፋት ምን ማለት ነው? ቁማር ምኑ ደስ ይላል? ሰዎች ላብ ያላንጠፈጠፉበትን የሰው ንብረት በዘዴና በ‹‹ስምምነት›› የሚቀሙበት፣ በርካታ ቤተሰቦች የሚፈርሱበት ፀያፍ ተግባር አይደለምን? ለክርስትያን ጎረቤት በክት የሆነን ሥጋ መሸጥስ ምን ዓይነት ሙስሊምነት ነው? ለሌላው የተበከለ ሥጋ እያበሉ ‹‹ምርጥ ምርጡን ለራስ›› የሚሉ ‹‹ሙስሊሞች›› ቢፈጠሩ ማነው ተጠቃሚ የሚሆነው? ‹‹ለልማት ቆሜያለሁ›› እያለ ዘወትር የሚደሰኩረው ኢሕአዴግ ስለምን ይሆን ቁማርተኛና ሌባ ሊያደርጉን የሚታገሉ ሰዎችን ‹‹አክራሪነትን በመዋጋት›› ሥም የሚያነግሥብን?

<u>አራጣ</u>

የሼኹን መጽሐፍት ዋነኛ መሠረት አድርጎ የሚንቀሳቀሰው ነውጠኛው የአሕባሽ ቡድን በሃይማኖት ዘረኝነት ጫፍ የደረሰ ቡድን ነው:: አንድ ምሳሌ፡-

ሁላችንም ማለት እችላለሁ ‹‹ሙስሊሞች አራጣ ለመብላት በሃይማኖታቸው አይፈቀድላቸውም›› የሚለውን ነገር በአንድ አጋጣሚም ቢሆን መስማታችን አይቀርም:: እርግጠኛ እውቀት ባይኖረኝም ክርስትናም ቢሆን ብዝበዛ ላይ የተመሠረተውን የአራጣ ሥርዓት የሚደግፍ አይመስለኝም:: አሕባሽ ደግሞ ዛሬ መጥቶ ሙስሊሞችን ‹‹አራጣ መጥፎ እንደሆነ አውቃለሁ:: ግን ደግሞ መጥፎ ቢሆንም ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች ላይ ከሆነ ብታደርጉት ችግር የለም! ብሏቸው!›› የሚለን ይመስላል:: ለዘመናት አብረን የተኗኗርናቸውን ክርስትያን ወንድማሞቻችንን በአራጣ እንድንበዘብዛቸው ይመክረናል:: ታዲያ አሕባሽን መቃወማችን ትክክል አይደለምን?

ሼኽ ዐብደላ ሐረሪ ሶሪሁል በያን በተባለው መጽሐፋቸው (የዳረል መሻሪዕ 3ኛ እትም/2008) ገጽ 521 ላይ የሚከተለውን ብለዋል፡- ‹‹…(ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን) ገንዘብ ሳያስገድዳቸው በአራጣና በቁማር ሊወስድ ይችላል::››

አራጣውን ይተዉና ስሜቱን እንኳን ያስቡት! ሃይማኖት የሚያስተምረን በመልካም ባሕሪና ውለታ አዳዲስ አማኞችን እንድንስብ እንጂ በዘረኝነት ተሸብበን ሌሎችን እንድንበዘብዝ፣ እንደመወጣጫ እንድንረግጣቸው አይደለም:: ለዚያውም ደግሞ ሼኹ አራጣ የሚሉት በወርቅና በብር የጥንት ሳንቲሞች መልክ ያለውን ገንዘብ ነው:: የወረቀት ገንዘብን በተመለከተማ የፈለግነውን ያክል ብንጠቀም፣ ሰዎችን በድርብርብ ወለድ ብንበዘብዝ ወለድ እንዳልሆነ ‹‹ዑምደቱ ራጊብ ፊ ሙኽተሶሪ ቡግየቱ ጧሊብ›› በተባለው መጽሐፋቸው (ዳረል መሻሪዕ አንደኛ እትም/2008) ገጽ 311 ‹‹አራጣ የሚባለው በብርና ወርቅ ከሆነ ነው፤ የወረቀት ገንዘብ ምንም አራጣ የለውም›› ሲሉ ገልጸዋል::

<u>አሕባሽና የሥነ-ምግባር ልሽቀት</u>

ዝሙትን ከነሙሉ ግሳንግሱና መገለጫዎቹ የማይከለክል ሃይማኖት በዓለማችን ላይ ለመኖሩ እጅጉን እጠራጠራለሁ:: ኧረ የለም ብል ይቀለኛል! የአሕባሽ መሥራችና የጡት አባት የሆኑት ሼኽ ዐብደላ ሐረሪ ግን ‹‹ሙስሊም ካልሆኑ ሰዎች ጋር ዝሙት መፈጸም እንደዝሙት አይቆጠርም›› ሲሉ አዲስ ራዕይ ሊያወርዱልን ይከጅላሉ:: በ‹‹ሙሐመድ ኢብን ሱዑድ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ›› የዶክትሬት መመረቂያ ጥናቱን በቡድኑ ላይ የሠራው ዶክተር ሰዕድ ኢብኑ ዐሊይ ይህንኑ የሼኹን ሐሳብ ‹‹ሶሪሁል በያን›› (2ኛ እትም ገጽ 255) ከተባለ መጽሐፋቸው ላይ ነቅሶ በማውጣት ‹‹ፊርቀቱል አሕባሽ›› በተሰኘው ጥልቅ ጥናቱ በገጽ 1214 ክፉኛ ተችቷል::

ይህ በሽታ እንጂ ሌላ አይደለም:: ዝሙት የማኅበረሰብ ነቀርሳ፣ የጋብቻ ጸርና የክፋት መጠራቀሚያ ሆኖ ሳለ እንዴት በእስልምና ሥም እንዲህ ይሉናል? ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እንደምንስ ይህ አዲስ ሃይማኖት ይዋጥልናል? እንዴትስ እንቀበለው? በሙስሊም እኅት ወንድሞቻችን ላይ እንዲፈጸም የማንሻውን ዝሙት እንደምን በክርስትያን እኅት ወንድሞቻችን ላይ ደፍረን እንፈጽመው?

<u>ግብረሶዶማዊነትና አሕባሽ</u>

ስለዝሙት የአሕባሽ አስተምህሮ ከገረመን ይህኛው ደግሞ እጅግ ያስደነግጠን ይሆናል! ‹‹ግብረሶዶማዊነትን ሁሉም ሃይማኖቶች በአንድ ድምጽ ያወግዙታል›› ብዬ መናገር ቃላት ማባከን መስሎ ይሰማኛል:: ይህንን የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝምና:: ‹‹ፀሐይ በምሥራቅ ነው የምትወጣው›› ብሎ ጊዜ እንደመፍጀት ያለ ነው:: በተቃራኒው መስመር አሕባሽ ብቻውን ቆሟል:: ዘወርዋራ በሆኑ አስተምህሮቶቹ የግብረሰዶማነትን አስፀያፊነት ለመሸራረፍ ይሞክራል - ለዘብ ብሎ ማለቴ ነው:: መቼም እንዲህ ያለው ነገር በቀጥታና ባንዴ አይነገርም:: እናም ሼኹ ‹‹ዑምደቱ ራጊብ ፊ ሙኽተሶሪ ቡግየቱ ጧሊብ›› በተባለው መጽሐፋቸው (ዳረል መሻሪዕ አንደኛ እትም/2008) ‹‹…ግብረሶዶማዊነት የሚባለው ሚስት ካልሆነች ሴት ጋርም ሆነ ከወንድ ጋር በመቀመጫ በኩል የሚደረገው ወሲብ ነው፤ ሚስት ከሆነች ግብረሶዶማዊነት ደረጃ አይደርስም›› በማለት ‹‹ለዘብ›› አድርገው ያስተምሩናል:: እንግዲህ በትዳር ጓደኛ ቀስ በቀስ ግብረሶዶማዊነትን ከተለማመዱ በኋላ ወደሌላው ፀያፍ የታሪኩ ክፍል መሸጋገር ብዙም እንደማይከብድ ይታወቃል::

የአሕባሽ አመጣጥ ግልጽ ነው:: መጀመሪያ ያደረገውም የግብረሶዶማዊነትን ትርጉም አንሻፎና አሏዙሮ መተርጎም ነው:: በዚህም ግብረሰዶማዊነት ቀስ በቀስ ተፈጥሯዊ ሆኖ እንዲታይ ያመቻቻል:: ይህ ደግሞ ጸረ ሰላም ብቻ ሳይሆን ጸረ ማኅበረሰብም ጭምር ነው! አንዳንዴ እንደውም ሳስበው ‹‹በቅርቡ በአገራችን የተደረገው የግብረሶዶማውያን ስብሰባ እና የአሕባሽ አገራዊ መምጣት ተዛምዶ አላቸው ይሆን እንዴ?›› የሚል መጠይቅ ይረብሸኛል::

<u>ሙስና</u>

ኢሕአዴግ ‹‹ሙስናን ድራሻባቱ ነው የማጠፋው!›› ሲል መዛት ከጀመረ ቆይቷል:: ለገሐር አቅራቢያ የቆመው ትልቅ ሕንፃም ጸረ ሙስና ኮሚሽን መሆኑን አስታውሳለሁ:: የተመልካች ድርቅ በመታው ኢቴቪ (ኢሬቴድ) በሚተላለፉልን ጸረ ሙስና ድራማዎችና በድርጅታዊ መዋቅር እየተዋጋው ያለው ሙስና በአሕባሽ የሚበረታታ መሆኑን መንግሥት ከቶ ያውቅ ይሆን?

አውቶቡስ ተራ ላይ የተተከለው ግዙፍ የጸረ ሙስና ማስታወቂያ ሰሌዳ ‹‹ጉቦ ሰጪም ተቀባይም የተረገሙ ናቸው›› የሚለውን የነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ንግግር ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር አጉልቶ ለአላፊ አግዳሚው ቢያሳይም፣ ከመንግሥት ጠንካራ ድጋፍ የሚደረግላቸው አሕባሾች ግን ‹‹አይዟችሁ! ለጉቦም መንገድ አለው!›› ይሉናል::

‹‹ዑምደቱ ራጊብ ፊ ሙኽተሶሪ ቡግየቱ ጧሊብ›› በተባለው መጽሐፋቸው (ዳረል መሻሪዕ አንደኛ እትም/2008) ገጽ 396 ሼኹ እንዲህ ይሉናል፡- ‹‹ጉቦ ሰጪው በሐቅ እንዲፈረድለት ወይም ያላግባብ እንዳይፈረድበት ለዳኛው ጉቦ ቢሰጥ ወንጀለኛ አይሆንም፤ (ሐራም አልሠራም::)›› እንደጸሐፊው እምነት እንግዲህ ሙስና ዋነኛ የፍትሕ ምንጭ ነው ማለት ነው! እንግዲህ የዚህን ተግባር አገራዊ አንድምታ አሥሉት:: እናንተ እስክታሠሉ እኔ ልጠይቃችሁ፡- ‹‹ለመሆኑ መንግሥት እየደገፋቸው ያሉትን ቡድኖች ማንነት በትክክል ያውቀዋልን? ነው ወይስ ዐረብኛ የሚችሉ ተርጓሚዎች የሉትም?››

ግራ ይገባል! ‹‹ያውቀዋል›› እንዳልል ሎጂኩ አልገጣጠም ብሎ አስቸገረኝ:: ‹‹አያውቀውም›› እንዳልል ደግሞ ክቡር ሚኒስትር ዶክተር ሽፈራው በግዮን ሆቴል ሰኔ መጨረሻ ላይ ባደረጉት ንግግር በሚገባ ተጠንቶ እየተደረገ ያለ ነገር እንደሆነ ገልጸዋል:: ባለፈው ቅዳሜ የታላቁ አንዋር መስጂድ ኢማም ሐጂ ጧሃ ሙሐመድ በአንዋር መስጊድ ባደረጉት ከፍተኛ ተቃውሞ ያስከተለባቸው ንግግር ላይም ከሚኒስትሩ ጋር አዘውትረው እንደሚገናኙ እና በሚገባ ተጠንቶ የመጣ ነገር እንደሆነ ገልጸዋል:: ስለአሕባሽ አስከፊነት በተለያዩ ሚዲያዎቻችን ደጋግመን ስንጽፍም ከርመናል:: አንድ ወቅት ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ‹‹አዲስ ዘመንንም አዲስ ነገርንም አላነብም›› ብለው ነበር:: አገሪቱ ውስጥ ያሉ ሚዲያዎችን ካላነበቡ እንዴት ብለው ነው የሕዝቡን ብሶት የሚሰሙት? ፓርላማ ውስጥ ያሉ ሰዎች እንደሆነ በብዛት ሲያጨበጭቡ እንጂ የመንግሥትን ፖሊሲ መተቸት ባለበት ቦታ ሲተቹ አናያቸውም:: ሁሌም እንደተስማሙ ነው:: በመሠረቱ 545 ሰዎች ሁልጊዜ እንዴት አንድ ዓይነት ሐሳብ ሊኖራቸው እንደቻለ በራሱ አስገራሚ ነው:: ‹‹ሰው እንደየመልኩ አስተሳሰቡም ይለያያል›› የሚለው ብሂል የማይሠራው በእኛ ፓርላማ ብቻ ይመስለኛል! (በነገራችን ላይ የፓርላማው ብቸኛ ተቃዋሚ የሆኑት የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ ባለፈው ለአቶ መለስ ጥያቄዎችን ባቀረቡ ወቅት ካለፈው ሐምሌ ጀምሮ ሙስሊሞች ላይ እየደረሰ ያለውን ወከባ አለማንሳታቸው በጣም ቆጥቁጦኛል:: ስህተታቸውን አርመው ከሰሞኑ በመጣጥፋቸው እንደሚክሱን ባለሙሉ ተስፋ ነኝ!)

አሕባሾች ‹‹ሙስሊም አይደለም›› ብለው ለሚፈርጁት ሰው ያላቸው ጥላቻ ጸረ ሰላም ሆኖ ቆይቷል:: ቡግየቱ ጧሊብ በተባለው መጽሐፋቸው ጥራዝ 2 ገጽ 330-331 ሼኽ ዐብደላ ሐረሪ ያሠፈሩት አንቀጽ ይህንኑ ጥላቻቸውን የሚያሳብቅ ነው:: በሙስሊም ግዛት ውስጥ አንድ ሙስሊም ያልሆነ ሰው በሰላም እንዲኖር የሚፈቀድለት ወቅት (በሳቸው አጠራር ‹አማኑል ካፊር›) ዐራት ወር እንደሆነ ይነግሩናል:: ይህ እብደት፣ ወፈፌነት ነው! ነቢዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) ‹‹በሙስሊሞች ግዛት ውስጥ ለተበደለ ሙስሊም ያልሆነ ሰው (ዚሚይ) እኔ በምጽአት ቀን ከሳሽ ሆኜ እከራከርለታለሁ:: እረታለሁም›› ብለው ሳለ እንዴት ሼኹ እንዲህ ይሉናል?

የአሕባሽን አስተምህሮ ብዙ ሃይማኖቶች እና ብሔር ብሔረሰቦች ባሉበት አገር ውስጥ ለማስፈን መታገል ከፍተኛ ጥፋት የሚያደርስ መሆኑን ይህ የሚያሳይ ይመስለኛል:: ይኸው አሕባሽ የተባለ ነውጠኛ ቡድን አውስትራሊያ ውስጥ የኤፍ. ኤም ሬዲዮ ጣቢያ ፍቃዱን ለማሳደስ በሞከረ ወቅት 200 የሚደርሱ የአገሪቱ ሙስሊም ሊቃውንት ፔቲሽን በመሰብሰብ ‹‹አሕባሽ እንደአገራችን ብዙ ብሔሮችና ሃይማኖቶች ላሉበት አገር እጅግ ጸር ነው›› በሚል መቃወማቸውን “muslimvillage.com” የተሰኘው ድረ ገጽ በኦክቶበር 10/2011 ዘግቦ ነበር::

<u>‹‹ሐረር የማናት?››</u>

የአሕባሽ አስተምህሮ እምብርት የሆኑት ሼኽ ዐብደላ ሐረሪ ‹‹ቡግየቱ ጧሊብ››፣ ‹‹ኢዝሃር ዓቂደቱ ሱኒያ›› እና በተለይ ደግሞ ‹‹ሶሪሁል በያን›› በተባለው መጽሐፋቸው ጥራዝ ሁለት ገጽ 5 በግርጌ ማስታወሻቸው ሐረር የሶማሌ ግዛት አካል መሆኗን ጽፈዋል:: ይታያችሁ ይህ ምን ዓይነት በአገራችን ሕልውና ላይ የተሰነዘረ ምት እንደሆነ!!! የሶማሊያው ኮሎኔል ዚያድባሬ አገራችንን ካሁን ቀደም የወረረው ከዚህ መሰሉ አስተሳሰብና አቋም በመነሳት ሊሆን ይችላል? አገር በመገነጣጠል ከቶ ማን ይሆን የሚጠቀመው? መንግሥትስ ቢሆን በግድ እየጋተን ያለው የአሕባሽ አስተሳሰብ ሐረር የሱማሌ አካል እንደሆነች ማመኑን አያውቅምን? ካላወቀ ደግሞ ለምንድነው ሲነግሩት የማይሰማው? ለምንስ ይሆን የአሕባሽን ተቃዋሚዎች ‹‹አክራሪ… አመጽ አነሳሽ… ወሐቢያ›› እያለ የሚያሸማቅቀውና የሚያስረው!!? አሕባሽ በእርግጥም ሰላማዊ አይደለም!

ሰላም በአሕባሽ ቡድን ዲ.ኤን.ኤ ውስጥ በጭራሽ የማይገኝ ንጥረ ነገር ነው:: ታሪካቸው ይህንኑ እውነታ በደማቁ ያሳብቃል:: የቡድኑ ዋነኛ ማዕከልና የጽንፈኞች ጉሮኖ የሆነችው ሊባኖስ ለዚህ ቋሚ ምስክር ናት:: 250 ሺህ አባላት እንዳሉት የሚነገርለት የሊባኖሱ የአሕባሽ ቡድን (A.I.C.P) በአገሪቱ የፖለቲካ ተሳትፎውና ተጽእኖው እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑ ሌላ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ የነበሩትን

ወደ ገፅ 14 ዞሯል

## አለም አቀፍ

# መቋጫ ያላገኘው የሶሪያ አመጽ

**በልዑል ሰንደቁ**

ዛሬ በአለማችን ቀዳሚ ሆነው ከሚጠቀሱ አወዛጋቢ አጀንዳዎች አንዱ በሶሪያ 12ኛ ወሩን የያዘው የህዝባዊ ተቃውሞና የአይን ዶክተር በነበሩት የፕሬዚዳንት በሽር አላሳድ ጦር በተቃዋሚዎች ላይ የሚፈፅመው ግድያ ነው፡፡

በአባታቸው በሀፌዝ አላሳድን እግር ተተክተው እ.ኤ.አ. በ2000 ዓ.ም በ34 ዓመታቸው የሥልጣን ርካን ለተቆናጠጡት ለበሽር አላሳድና ለአባታቸው ለሀፌዝ አላሳድ ውስጥ ውስጡን እያመረቀዘ ስር የሰደደ ታሪካዊ ቦምብ ቀብራ የወጣችው በቅኝ ግዛት ታስተዳደር የነበረችው ፈረንሣይ ነበረች፡፡

ብዙዎች በሶሪያ የተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ ከተቀሰቀሰው ህዝባዊ ተቃውሞ ጋር ቢያመሳስሉትም መቼም ቢሆን ጊዜውን ጠብቆ መፈንዳቱ የማይቀር አሻራ እንዳረፈበት ታሪካዊ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

ተቃውሞው ከዛሬ 12 ወር በፊት እንደፈነዳ ተቃዋሚዎቹን በካይ ጀርሞች በማለት ለወረፉት ለበሽር አላሳድ መሰረት የጣለውን የስልጣን እርካብ ያመቻቹት ሀፌዝ አላሳድ እ.ኤ.አ. በ1930 የፈረንሳይን ቅኝ ገገርዎች ይደግፉ ከነበሩ ዱርዝ በተባለው ግዛት ከሚገኙት ከአላዊ ጎሳ ተወለዱ፡፡ በዚሁ በተወለዱበት ግዛት በሚገኝ በሏቷኪያ ከተማ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ሀገራቸው ነፃነቷን ካወጀች ከ10 ዓመት በኋላ እ.ኤ.አ. በ1955 ዓ.ም ከወታደራዊ አካዳሚ ተመርቀው በጦር ውስጥ ተቀላቀሉ፡፡

ፈረንሳይ በቅኝ ታስተዳድራቸው የነበሩት ሶሪያና ሊባኖስ ደም አፋሳሽ በሆነ ጦርነት ለሁለት ተከፍለው መንግሥት ከመሰረቱ በኋላ የአብዛኛውን ሶሪያ ህዝብ የሚወክሉና በገጠር የሚኖሩ የሱኒ ሃይማኖትን የሚከተሉ ሶሪያውያንን ለመበቀል በዘረጋችው ወጥመድ ሶሪያን ለቃ ስትወጣ የሱኒ ተወላጆች በጦር ሃይሉ እንዳይቀጠሩ በማድርግ የሺያት ሃይማት ተከታይ የሆኑ ጦርን አደራጅታ ነበር፡፡

ይህ መገለል የተፈፀመባቸው የሱኒ ሃይማኖት ተከታዮች የአሳሪያ ነፃ አውጪ የሚል አማፂ ቡድን በማቋቋም በጀመሩት የሙስሊም ብራዘር ሁድ እንቅስቃሴ ሶሪያ ነፃ ከወጣች ከሶስት አመት በኋላ በ1949 ዓ.ም የተደረገው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ያሳሰባት ፈረንሳይ በግዛቷ ይኖሩ የነበሩ ሁለት ስመጥር የፖለቲካ ሰዎችን በፖለቲካ አጥምቃ ወደ ደማስቆ እንዲመለሱ አደረገች፡፡

እነዚህ ሁለት ፖለቲከኞች የግሪክ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የነበረው ሚሺል አፍላቅና የሱኒ ሃይማኖት ተከታይ የነበረው ሳላህ አል ዲን አስባታሪ ነበሩ፡፡

ሁለቱ ፖለቲከኞች ወደ ደማስቆ በመመለስ ወጣቶችን አስተባብረው ባዝ የተባለውን ፓርቲ መሰረቱ፡፡ ሀፌዝ አላሳድ በዚህ ፓርቲ ከተቀላቀሉና ፓርቲው በሺያት ሃይማኖት በኩል በስፋት ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ውስጥ ለውስጥ የፖለቲካ ሽፍጥ በመዘርጋት ከመስራቾች አንዱ የነበረው አፍላቅ በ1966 ዓ.ም ከፓርቲው እንዲወገድና አልባተር ደግሞ በፈረንሳይ ፖሊስ ታፍኖ ወደ ፓሪስ እንዲያቀና በማድረግ ለፈረንሳይ ታማኝ ነኝ ላሉት ለሀፌዝ የስልጣን ወንበር ማመቻቸት ተጀመረ፡፡ከነዚህ ሽፍጦች ውስጥ እ.ኤ.አ. በ1963፣በ1966 እና በ1970 በተደረጉት መፈንቅለ መንግስቶች የመጀመሪያውን አነስተኛ ተሳትፎ በማድረግ በሁለተኛው ወዳጃቸውን በመደገፍ በሶስተኛው ለራሳቸው ቀዳሚ ሆነው በመምራት የስልጣን እርከን ተቆጣጠሩ፡፡

በሀፌዝ አላሳድ ፊታውራሪነት ከሥልጣን የተገረሰሱትንና ወህኒ የወረዱትን የቀድሞውን ፕሬዚዳንት እ.ኤ.አ. በ1992 ተለቀው ወደ ፓሪስ እንዲሄዱ በመፍቀድ ሙሉ በሙሉ ፊታቸውን ከምዕራባዊያን ከማዞራቸው በፊት ጡንቻቸውን የሚያጠናክር የፖለቲካ ኸዋኸዌ መጫወት ስራዬ ብለው ተያያዙት፡፡

እንደ መርከብ ጠላፊ በአንድ ወገን ሱኒዎችን በጦር ሃይል አዛዥ በነበሩት በወንድማቸው ሪፋት አላሳድ እያስፈራሩና በጥቅም እየደለሉ በሌላ ወገን ለሰላም የቆሙ መሆናቸውን እየሰበኩ ካደረጓቸው ድርድሮች ውስጥ ከቀድሞ የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሄንሪ ኪሲንተን ጋር በጥር 1973 ዓ.ም ያደረጉት ስምምነት በቀዳሚነት ይጠቀሳል፡፡

ሌላው እስራኤል በስድስቱ ቀን ጦርነት የጎላን ተራራዎችን በኃይል ስትቆጣጠር በድንበር ይወዛገቡ ከነበረው ከሊባኖስ ጋር እ.ኤ.አ. በ1976 ስምምነት በመፈራረምና የሂዝቦላ አማፂ ቡድንን በማስታጠቅ በእስራኤል ላይ ጥቃት እንዲሰነዝሩ የዘረጉት የፖለቲካ ወጥመድ ሀገራቸው በቀጠናው ያላትን ሀይል እንዲጠናከርና በአለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነት እንዲኖራት ከፍተኛ ድርሻ ያበረከተ ነበር፡፡

በፖለቲካው ዘርፍ ጠንካራ ተቃዋሚዎች በሚገኙበትና የሱኒ ሃይማኖት ተከታዮች በሰፈሩበት በሃማ ግዛት 200 ወጣቶችን በመመልመል በብቸኛው የባዝ ፓርቲ እንዲቀላቀሉ በማድረግ ተቃውሞውን ለማብረድ የተጫወቱት ሚና በወቅቱ ከፍተኛ ክብር ያጉናፀፋቸው ነበር፡፡

ሀፌዝ አላሳድ ጠንካራ ሶሪያን ለመገንባት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በማጠናከርና ከሶሻሊስት ሀገራት በተለይም ከሶቪየትና ከቻይና መሳሪያ እየገዙ ጡንቻቸውን በማፈርጠም ዙፋናቸውን ለማስቀጠል የነበራቸው እቅድ አደጋ ውስጥ ሊወድቅ የሚችል መሆኑን የሚጠቁም ስር የሰደደ ሀዘን ውስጥ የገቡት በፖለቲካ ያጠመቁት ልጃቸውን ባሰል አላሳድን/የአሁኑ ፕሬዚዳንት ታላቅ ወንድም/ በመኪና አደጋ እ.ኤ.አ. በ1994 ዓ.ም ከሞተ በኋላ ነው፡፡

በአረቡ አለም ‹‹ናሳብ›› በተባለው ባህል አባት ለልጁ ሥልጣን ማውረስ ከፈጣሪ የቀረበ ፀጋ በመሆኑ ለስልጣን የታጨው ባሳል ከሞተ በኋላ በህገ መንግስቱ በሚደነግገው መሰረት በለንደን የተማረውን የአይን ሀኪም የነበረው በሽር አላሳድ ተተኪያቸው መሆኑን አወጁ፡፡

የሶሪያ ህዝብ በበሽር አላሳድ ላይ ቂም መቋጠር የጀመረው እ.ኤ.አ. በ2000 አባታቸው ሀፌዝ አላሳድ በነፍስ ገዳዮች ከተገደሉ በኋላ ስልጣን እንደያዙ ነበር፡፡ ለዚህ እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሰው ለንደን የመማራቸው እንዲሁም በሀማ የሱኒ ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ የቡርኸ ቤተሰብ ከተወለደችና በለንደን ከተማረች አስማ አል አክሀራስ ጋር ትዳር የመመስረታቸው ጉዳይ ሥልጣኑን ለመረከብ አባታቸውን በለንደን ነፍስ ገዳዮች አስገድለዋል የሚል ነው፡፡

ከዚሁ በተያያዘ ስልጣን እንደያዙ አባታቸው ለህዝቡ የነፈጉትን መብት አጐናፅፋለሁ በማለት ከምዕራብ ሀገራት ሲጋራ እንዲገባ የአርት ጋለሪዎች እንዲከፈቱ ያስተላለፉት ውሳኔ በደማስቆና በሀማ በሚኖሩ የሱኒ ተወላጆች ጥርስ ውስጥ እንዲገቡ አደረጋቸው፡፡

ይህንን ተቃውሞ ለመቀልበስና የህዝቡን ቀልብ ለመሳብ የአሜሪካ ታሪካዊ ጠላት ከሆነችው ከኢራን ጋር ጥብቅ ወዳጅነት በመመስረት ምዕራባዊያንን መወረፍና እስራኤልን እንደጠላትነት መመልከትና ጥላቻቸውን በይፋ ማስተጋባት ጀመሩ፡፡

የሶሪያና የኢራን ወዳጅነት ያስጋት እስራኤል ሶሪያ የኒኩለር ሀይል ግንባታ ጀምራለች በማለት ሶሪያ ለሀይል ማመንጫ እየገነባችው የነበረውን ህንፃና የመሰረተ ልማት አውታሮች በጦር ጀት ወደ አቧራ ለወጠቻቸው፡፡ በሶሪያ ይታወቃሉ የምትላቸውን በሊባኖስ የሚገኙ የሂዝቦላ ታጣቂዎችን ለመደምሰስ በይፋ ጦርነት አውጃ የጠነከረ ጥቃት ሰነዘረች፡፡

ምዕራባዊያንና አሜሪካንም የሶሪያ መንግስት ሽብርተኞችን ይደግፋል በማለት የተለያዩ ማዕቀቦችን በመጣል የውስጥ ቅራኔ እንዲፋፋም የተለያዩ የፖለቲካ አጀንዳዎች በመምዘዝ ውዝግብ ውስጥ በገቡበት አጋጣሚ የአረቡ አለም አብዮት በቱኒዚያና በግብፅ ተቀጣጠለ፡፡

ይህ አብዮት እንደተቀጣጠለ የሱኒ ሃይማኖት በብዛት በሚገኙበት በሆሞስና በዳራ ወጣቶች ወደ አደባባይ በመውጣት በሽር አላሳድን የሚያወግዙ መፈክሮችን ማሰማትና ግርግዳዎች ላይ የተቃውሞ ፅሁፋችን ማስፈር ጀመሩ፡፡

ይህን ተቃውሞ በአሜሪካና በምዕራባዊያን የተጠነሰሰ ሴራ ነው በማለት ተቃዋሚዎችን በሰለጠኑበት ሞያ አያይዘው በካይ ጀርሞች ናቸው አሉ፡፡ ከተወለዱበት ከአላዊ ጐሳ ከተመለመሉ 280 ሺህ ከሚጠጋ ሰራዊታቸው አብዛኛውን በታንክ ታጅበው የደራና የሀማስን ጐዳናዎች በማጥለቅለቅ ተቃዋሚዎችን በገፍ ማሰር ተያያዙት

አስራ አንድ ወሩን ባጠናቀቀው ተቃውሞ ከ6000 ሺህ -7000 የሚጠጉ ተቃዋሚዎች ተገድለዋል የሚለውን የአለም አቀፍ ሚዲያዎች ዘገባ በማስተባበል የሟች ቁጥር ከ2000 አይበልጥም በሚለው የበሽር አላሳድ መንግስት ጋዜጠኞችን ጠራርገው በማስወጣት እንዲሁም ከሟቹ ቁጥር ከግማሽ የሚበልጡት የደህንነት የፖሊስ ባልደረቦች ናቸው የሚል ማስተባበያ ማቅረቡን ተያያው፡፡ በሶሪያ ስር ከሰደደው ተቃውሞ በመነሳት አሁን ወዳለው ተጨባጭ መረጃ ስንሸጋገር በሽር አላሳድ የምዕራብ ቅጥረኞችና አሸባሪዎች ከሚሏቸውና ጀርሞች ብለው ከጠሯቸው ተቃዋሚዎች ጋር ለመደራደር ዝግጁ ነኝ በማለት በአረብ ሊግ አባል ሀገራት የተወከለ አጣሪ ቡድን ወደ ግዛታቸው እንዲገባ የፈቀዱት ሊጉ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድር ውሳኔ ካስተላለፉ በኋላ ነው፡፡

በአረብ ሊግ የተወከለው አጣሪ ቡድን ወደ ሶሪያ ሲዘልቅ ተቃዋሚዎች ለሁለት ተከፍለው የባዝ ፓርቲና በሽር ካልተወገዱ በስተቀር አንደራደርም የሚልና የምዕራባዊያን አጀንዳ ለማስፈፀም የተጠነሰሰ የጣልቃ ገብነት ሴራ እንደሆነ የሚገልፁ መፈክሮችን ያነገበ ተቃውሞ ከመሰማት ውጪ ለድርድር አንሰየምም አሉ፡፡

የሚይዙትና የሚጨብጡትን ያጡት የአረብ ሊግ አጣሪ ቡድን አባላት የማጣራቱ ተግባር ለአንድ ወር እንዲራዘምለት ከጠየቀ በኋላ የመጨረሻ ያለውን የውሳኔ ሰነድ ይዞ በተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት ላይ ተሰየመ፡፡

በአረብ ሊግ የቀረበውየማግባቢያ ሰነድ በሽር አላሳድ ከስልጣን ወርደህ በተቃዋሚዎችና በመንግስት መካከል የሽግግር መንግስት ለማቋቋም ድርድር ያድርጉ የሚል ነው፡፡

ይህ የማግባቢያ ሰነድ እንደተጠበቀው ቻይናና ሩሲያ በፀጥታው ምክር ቤት ድምፅን በድምፅ የመሻር ስልጣናቸውን ተጠቅመው ውድቅ አደረጉት፡፡ ለዚህ ውሳኔ ያቀረቡት ምክንያት በድርጅቱ የመተዳደሪያ ደንብ ማንም በሀገር ውስጥ ጣልቃ በመግባት ፕሬዝዳንቱ ይውረዱ አይውረዱ ማለት አይቻልም የሚል ነው፡፡

የቻይናና የሩሲያ ውሳኔ ያስቆጣቸው ከምዕራባዊያን ጐን ከቆሙ የአረብ ሊግ ሀገራት እንደሳውድ አረቢያ፣ ኳታር ያሉ ሀገራትና አሜሪካ አምባሳደራቸውን ከሶሪያ በማስወጣት ለወሰዱት ርምጃ የሶሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወጪያቸውን ከቻለ ከፈለጋቸው ወደ ጨረቃ ቢልኳቸውም ግድ የለንም የሚል ምላሽ የሰጡት ባለፈው ሳምንት ነበር፡፡

እንደ ፖለቲካ ተንታኞች በሶሪያ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ ከግብፅ በሊቢያና በቱኒዚያ ከተቀሰቀሰው ተቃውሞ ለየት ከሚያደርጉት አበይት ምክንያቶች ውስጥ የመጀመሪያው ጦሩ በጎሳና በሃይማኖት ያልተከፋፈለና ስልጣን ላይ ካለው ከአላዋይት ጐሳ አባላት የመጣ በመሆኑ ከተቃዋሚዎች ጋር የመቀላቀል እድሉ የጠበበ መሆኑ ነው፡፡ሁለተኛው ምክንያት 50 ዓመት በብቸኝነት የገዛው የባዝ ፓርቲ በርካታ ደጋፊዎችን ማፍራቱና የጦር አዛገች መካከል መከፋፈል አለመታየቱ ነው፡፡

ከዚህ በተቃራኒ የበሽር አላሳድ መንግስት በአንድ አመት እድሜ ውስጥ ከስልጣን ሊገረሰስ ይችላል የሚሉት ቀውሱ እንደተቀሰቀሰ ጦሩን ከድተው ወደ ቱርክ የተሰደዱት የጦሩ ጀነራል ሙስጠፋ አህመድ አልሸክ ናቸው፡፡

ለዚህ አባባላቸው የሚያስቀምጡት መረጃ ቀውሱ ከተቀሰቀሰ በኋላ ሮኬቶችና ቀላል መሳሪያዎችን እንደታጠቁ ወደ ተቃዋሚዎቹ የተቀላቀሉት ከ20-30 ሺህ የሚደርሱ የጦሩ አባላት በስድስት አቅጣጫ ጥቃት ለመሰንዘር የሚያስችሉ ስትራቴጂካዊ ቦታዎች ላይ ስለሚገኙ የመንግስትን ሀይል በማመናመን ሊፈጥሩት የሚችሉት ጫና የጎላ ይሆናል የሚል ነው፡፡

## የአብዮቱ ደወል ... ከገፅ 10 የዞረ

የፖለቲካ ስርዓቱ ብቸኛ መሪ ሆነው ይወጣሉ፡፡ ‹‹እናም›› ይላሉ ፀሐፊው ‹‹እንዲህ አይነት መሪዎችን ከፓርቲ ስልጣን ማውረድ አስቸጋሪ የሽቅብ መንገድ (uphill stride) ነው፡፡››

የህወሓት የሰላሳ ሰባት ዓመት ታሪክ ፓርቲው የተነሳበትን መሰረታዊ ግቦች በመጣረስ እንደተደመደመ የሚናገሩ ብዙዎቹ የፓርቲው መስራች ታጋዮች የህወሓት መፃኢ እድል ላይ ያላቸው እይታ ጨለምተኛ የሚባል ነው፡፡ የአቶ ገብሩ አስራት ‹‹ህወሓት ደርግን ከመጣል ውጪ ያሳካው ግብ የለም›› የሚለው አስተያየትም የተጠቀሰውን ሀሳብ የበለጠ ያስረግጣል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከደርግ ውድቀት ወዲህ ፓርቲው ቢያንስ የትግራይ ወጣቶችን እንኳን በሚገባ ለማደራጀት አለመቻሉ ‹‹አለኝ›› ከሚለው ‹‹የትግራይ ህዝብ ድጋፍ›› መቀዛቀዝ ጋር ይያያዛል፡፡ እንደሌሎቹ የሀገሪቱ ክልሎች ሁሉ የትግራይ ክልልም በፓርቲው አምባገነናዊ የአፈና ስርዓት የሚዋትት ከመሆኑ በተጨማሪ ፓርቲው በትግሉ ወቅት የተጎዱ የቀድሞው ታጋዮችን እና ቤተሰቦቻቸውን እየዘናጋቸው መሄዱ ቅሬታቸውን እያባባሰ እንደመጣ የፓርቲው መስራቾች በይፋ ይናገራሉ፡፡ ፓርቲው ከተነሳባቸው መሰረታዊ ግቦች አንደኛው የሆነው የብሄር ጭቆና ጥያቄ አሁንም አልተፈታም የሚሉ የፖለቲካ ሀይሎች መኖር እና የቀድሞው የህወሓት መስራች የነበሩ ፖለቲከኞች ወደ ተቃውሞው መምጣታቸው ሌላኛው የፓርቲው ተግዳሮት ይመስላል፡፡ አንዳንድ ተንታኞች ከላይ የተዘረዘሩት ፖለቲካዊ ችግሮች እና ኢኮኖሚያዊ ድቀቶች የ‹‹ሁለተኛው ወያኔ አብዮት›› ክሽፈት አድርገው የሚያስቡ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ወጣቶችን ወደ ሶስተኛው የ‹‹ወያኔ አብዮት›› እንዲያዘግሙ ሊገፋቸው ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡

ዕንቁ የቤተሰብዎ መፅሔት

ነገ በገበያ ላይ ውሏሰች

የ2ቱ ሲኖዶሶች ድርድር በአሪዞና

“ንክሩማህ በምንም መንገድ አፄ ኃይለሥላሴን አይቀድምም”
ፕሮፌሰር አብይ ፎርድ

“ጥያቄያችን የመጅሊስ አመራር እንዲወገድ ነው”
ዑስታዝ አቡበከር አህመድ

“ጂም የሚያስተምር ሰው ፊልም እየገመገመ ከሱ ምን ትጠብቃለህ?”
አርቲስት ቢንያም ወርቁ

የአባ ሰረቀ አዲስ መፅሐፍና “ስልታዊ ማፈግፈግ”

“አንድነትን በሚሰብክመፅሃፍ የዘር ልዩነት ማጉላት አላስፈለገኝም”
ደራሲና ገጣሚ ይስማዕከ ወርቁ

“ጀነራል አማን ከዶ/ር መስፍን ወ/ማርያም ጋር ወቅሠውኝ ነበር”
ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም




አስደናቂው የፋር ኢንፍራሪድ ጀርመንየም እና ማግኔቲክ ቴራፒ

እንደ ብራስሌት እጅ ላይ በማሰር በሽታን ማዳን እንዲሁም መከላከል ይቻላል




ለአርትራይተስ እና ቁርጥማት
ለጀርባ ህመም ለትከሻ ህመም
ለከባድ ራስምታት ለመተንፈሻ ችግሮች
ለሳልና ለአስም ለሪህ ለማቃጠል ስሜት
ከእንቅልፍ ጋር ለተያያዙ ችግሮች
እና ለሌሎችም በርከታ የጤና ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል

HARNESS

ይደውሉልን
0910 035578, 0911 19 62 51
P.O.Box 26982 code 1000 Addis Ababa

# አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰባብሮ ቀረ እንደ ፓጃን ስኒ

## ከድህረ-ፋሽስት የኢትዮጵያ ተማሪዎች መዝሙር የተወሰደ



ከታዴዎስ ታንቱ

በአንድ ትልቅ የድንጋይ ግንብ አጠገብ ቀጥ ብሎ እንዲቆም ተደረገ:: ኪሊራ ፒቲሲ አጠገቡ ሆነች:: ትናንትና በአንድ ቤት ውስጥ ታሥረው አድረዋል:: እቁባቱ መሆኗን ያዙ:: ሁሉም ነገር ዛሬ ይጠናቀቃል:: ቤኒቶ ሞሶሎኒ ይገደላል:: የትናንትናው የአሥር አለቃ የዛሬው የኢሊያ ቻንስለር ከጥቂት ጊዜአት በኋላ የመጨረሻ ትንፋሹን ይለቅቃል:: የማይሆን ቢመስልም ይሆናል:: በምን ተአምር ያመልጣል? አንዳንዴ በሐሳብ ሩቅ መንገድ ይሄዳል:: ተመልሶ ግን ይመጣል:: ሞት ከፊቱ ቆሟል:: እሱም ከሞት ፊት ቆሟል:: ትላንት ፈላጭ ቆራጭ ነበረ:: ዛሬ ግን ሥልጣኑን ተገፍፏል::

ሞሶሎኒ አንድ አፍታ ኪሊራ ፒቲሲን ተመለከታት ‹‹ሚች ቀናተኛ ሚስቴን አደራ ይላል››ይባልየለ? ይህች የግብረ ስጋ ግንኙነት ንግስት ከሱ ጋር ትገደል ይሆን? አይታወቅም! ኪሊራ ፒቲሲ ሁሉም የግንኙነት ስልት ይጥማታል:: በግብረ ሥጋ ግንኙነትና በጦርነት ሒደት ሕግ እንደሌለ በደንብ አውቃለች:: ሥልጡን ዕንዝርት ኢጣሊያዊት ናት:: ሁሉ ነገርዋ ለአልጋ ጨዋታ ይመቻል:: በግንኙነት ሰዓት በሞሶሎኒ ውስጥ ትቀልጣለች:: እሱም በሷ ውስጥ ይቀልጣል! ከስሜቷ ግለት የተነሣ አንዳንዴ ትጮኻለች:: አንዳንዴ ደግሞ ገላዋ የሞሶሎኒን ገላ ነክሶ አልለቅ ይላል:: ይሄ ደግሞ ሞሶሎኒን በጣም ያስደስተዋል:: ጡቶቿን ጎርሶ ባፍንጫው ይጮኻል::

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አዝማች! አዝማች! አዝማች! አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰባብሮ ቀረ እንደ ጃፓን ስኒ::

አምባገነኖች በታሪክ አጋጣሚ ከትቢያ ይነሣሉ:: ነባራዊ ሁኔታዎችን በደንብ ይፈትሹታል:: የሕሊናዊ ሁኔታዎች ክፍተት ደግሞ ለእነሱ ዳቦ በቅቤ ይሆናል:: በመቀጠል ሕዝብን ይጋልባሉ:: በንብረቱ ብቻ ሳይሆን በነፍሱም ላይ አዛዥና ናዛዥ ይሆናሉ:: ለዚህ ዓላማቸው ካድሬዎችን፤ የፀጥታ ሠራተኞችን የመረጃ አገልጋዮችን ጆሮ ተላላኪዎችን ድብቅ ነፍስ ገዳዮችንና ሥውር ታጣቂዎችን በሕዝብ መካከል ይሰገስጋሉ:: ይህም ሁሉ ተደርጎ ግን በመጨረሻ መራራውን የውድቀት ፅዋ ከመጨለጥ አያመልጡም::

ፋሽስቱ ሞሶሎኒ ሳይወድ ሞቱን ለማስተናገድ ቀርቧል:: ስለዚህ አሁንም ከግንቡ አጠገብ ቆሟል:: ገዳዮች ነጠል ብለው ይወያያሉ:: ወታደሮች ግን እሱን ኪሊራ ፒቲሲንና ሌሎችን ጥቂት የተያዙ ፋሽስቶችን በጥብቅ እየጠበቁ ይገኛሉ:: በእርግጥ ሞሶሎኒን የሚያስመልጥ ኃይል አይመጣም:: ጀርመንም ሆነ ጃፓን በዚያን ሰዓት ደክመዋል:: የኢጣሊያ አርበኞች ደግሞ ሞሶሎኒ ተይዞ ለፍርድ እንዲቀርብ ከጠየቁ ውለው አድረዋል:: በኢጣሊያ ምድር ፋሽዝም ያከትማል:: አሁን ገዳዮቹ ሁሉም በሁሉም ጉዳይ ከስምምነት ላይ ደርሰዋል:: በኒቶ ሞሶሎኒ ይገደላል! ይገደላል! ይገደላል! ገዳዩ አሁን ሽጉጥ ደገነበት! ሞሶሎኒ ተርበተበተ:: ገዳዩ ኪሊራ ፒቲሲ ዞር እንድትል ነገራት:: ግን ፈቃደኛ አልነበረችም:: እንዲያውም ሞሶሎኒ እንዳይገደል ትከራከር ገባች:: ደፋር ሴት ናት:: ከሽጉጥ አፍ ትይዩ ቆማ ወዳጇ እንዳይገደል ተሟገተች:: ከሊራ ፒቲሲ ከኢጣሊያ ሴቶች በቁንጅና አንደኛ እንደሆነች ተነግሮላታል:: ምናልባትም ከጀርመንም ጭምር በመመዘኛ ቀዳሚውን ረድፍ እንደማታጣ ተመልክቷል:: ቆንጆ ብቻ ሳትሆን ታማኝም ናት:: በፍጻሜው ሰዓት እንኳን ከወዳጇ ጎን ተገኘች::

ኪሊራ ፒቲሲ አሁንም ዞር እንድትል ተነገራት:: ግን በእምቢተኛነቷ ገፋችበት:: ምንም እንኳን እንዳትሞት የገዳዮ ፍላጎት ቢሆንም ከሞሶሎኒ ተለይታ ዓለምን ለማጣጣም እንደማትችል የስሜት ሕዋሳቷ ነግረዋታልና:: ገዳዩ ዋልተር አዲሲዮ በጣም ተናደደ:: ሆኖም አጠገቧ ሔዶ ከሞሶሎኒ ለመነጠል አልጎተታትም:: ነገር ግን ቁጥሩ 2830 የሆነ የእጅ መትረየስ የያዘ ወታደር አጠገቡ መቆሙን አስተውሏል:: ወዲያው ሽጉጡን ወደ ማህደሩ መለሰውና ኪሊራ ፒቲሲ ገለል እስክትል ጠበቃት:: እሷ ግን አሁንም የቅድሟ ናት:: ዋልተር አዲሲዮ ንዴቱ ከመጠን በላይ አሻቀበ:: ወዲያው መትረየሱን ከወታደሩ ለቀም አድርጎ በሞሶሎኒና በኪሊራ ፒቲሲ ላይ አርከፈከፈባቸው:: ሁለቱም ወደቁ:: የፍጻሜው የመጨረሻ ደወል ተደወለ:: እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 29 ቀን 1945ዓ.ም.:: አለቀ፤ ደቀቀ:: ሞሶሎኒ ሞተ::

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አዝማች! አዝማች! አዝማች! አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰባብሮ ቀረ እንደ ጃፓን ስኒ::

ፋሽስቱ ቤኒቶ ሞሶሎኒ እ.ኤ.አ. ሐምሌ 24 ቀን 1883ዓ.ም ተወለደ:: እለቱ እሁድ እንደነበር ታሪክ ይናገራል:: አባቱ ብረት ቀጥቃጭ ሲሆን እናቱ ማልቶኔ ደግሞ የትምህርት ቤት አስተማሪ ነበረች:: አባቱ አልሣንድሮ በሰፈር በነገረኝነቱ የታወቀ ሰው ነበር:: ብዙ ጊዜ ታሥሮ ተፈትቷል::

ሞሶሎኒ በትምህርቱ ጎበዝ እንደነበር ታውቋል:: እናቱ አስተማሪ መሆኗ በበኩሉ ለጉብዝናው አስተዋፅኦ አበርክቷል:: መጻሐፍት የማንበብ ልምድንም አዳብሯል:: የዓለም ሁኔታዎችን በንቃት ይከታተል ነበር:: እንዲሁም በኢጣሊያ የነበረውን የፖለቲካ ሁኔታ ከመከታተል የቦዘነበት ወቅት አልነበረም::

የፋሽስታዊው አገዛዝ አምበል ቤኒቶ ሞሶሎኒ ከሕፃንነቱ አንስቶ የሴት ዐመል ክፉኛ የተጠናወተው ሰው እንደነበር ታውቋል:: በሴት ጭን መካከል ካልተጋደመ እንቅልፍ ፈፅሞ አይወስደውም:: እንዲያውም ገና የአሥር ዓመት ሕፃን ሆኖ ሴቶችን ገንዘብ እየከፈለ ይገናኛቸው እንደነበር በታሪክ ተረጋግጧል:: ሴቶቹ ደግሞ በዝሙት ንግድ ላይ የተሰማሩ ለሕፃን ልጅ የማይመጥኑ ትልልቅ ሰዎች እንደነበሩ አንዘንጋ:: የአሥር ዓመት ልጅ በጣም ሕፃን ነው::

ቤኒቶ ሞሶሎኒ ቅንዝረኛ መሆኑን በሥልጣን ላይ በነበረ ጊዜ በአንደበቱ አምኗል:: ሴሰኝነቱ በአጥንቱ ውስጥ ሠርፆ ገብቷል:: ሚስትና ልጆች ነበሩት:: ሆኖም ቅምጦቹ ብዙ እንደነበሩ ታውቋል:: ለኪሊራ ፒቲሲ ቤት ገዝቶ ሠጥቷታል:: ሞሶሎኒ ሴቶችን የወደዳቸው ለግብረ ሥጋ ግንኙነት ብቻ መሆኑን አንጣ! ለሴቶች በሰብዓዊ ተፈጥሮአቸው ተገቢውን ክብር ግን በእጅጉ ይነፍጋል:: እንኳንስ ለሌላ ሴት ለወላጅ እናቱ በእናት እርከን ከልጅ የሚጠበቅ ከበሬታ ሰጥቷት አያውቅም:: እሱ የሚወድደውና የሚያከብረው ሞገደኛ አባቱን ብቻ እንደነበር ታሪክ ይመሰክራል::

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አዝማች! አዝማች! አዝማች! አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰባብሮ ቀረ እንደ ጃፓን ስኒ::

ሞሶሎኒ የኢጣሊያ የፋሽስት ፓርቲ መሪና ቻንስለር እንደ ነበረ ግልፅ ነው:: ሆኖም ጥያቄ! ጥያቄ! ጥያቄ! ፋሽዝም ምንድነው? ፋሽዝም የከበርቴው ሥርዓት በጠቅላላ ቀውስ ውስጥ በተገባበት ወቅት የአድሓርያንና ግፈኛ ኃይላትን ፍላጎት ለማርካት የተመረጠ የሥነ መንግስት መርህ እሳቤ ነው:: ፋሽዝም በሥልጣን ተልዕኮው አሸባሪ አምባገነን መሆኑን እንያዝ! ፋሽዝም ፀረ-ሥልጣነ ሕዝብ ነው:: እንዲሁም ፀረ-የጋርዮሽ ሥርዓት መሆኑን አንጣ:: ፋሽዝም በሕዝብ እንዲሁም በዜጎች የግል ሕይወት ላይ ጭምር ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋል::

የፋሽስት አገዛዝ እ.ኤ.አ. በ1922 ዓ.ም. በኢጣሊያ ተቋቋመ:: በተመሳሳይ መልኩ እ.ኤ.አ. በ1933ዓ.ም በጀርመን ሥልጣን ይዟል:: እንዲሁም በ1939ዓ.ም በእስፔይን የፋሽስት አገዛዝ ተዘረጋ:: እ.ኤ.አ በ1973ዓ.ም ደግሞ በቺሊ ውስጥ ፋሽስቶች ሥልጣን ጨበጡ በተመሳሳይ ሁኔታ በደቡብ አፍሪካ ለጥቂት ነጭ ከበርቴዎች የቆመ ዘረኛ ፋሽስታዊ አገዛዝ እንደነበረ አንዘንጋ:: አሁንም በደቡብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ነፃነት በምሉዕ መልኩ አልተመዘገበም:: በሌሎችም በብዙ ሀገሮች ፋሽዝም ተንሠራፍቶ ቆይቷል::

በአሁኑ ጊዜ ግን የፋሽዝም ትርጉም አድማሱ ሰፍቷል:: በዚህም መሰረት በከበርቴው ሥርዓተ ማህበር የአገዛዝ መርህ ውስጥ ሕዝብን የሚጨቁን አገዛዝ ሁሉ በሥነ መንግስት ጠበብት ከፋሽስት ጎራ ይመደባል:: በሌላ አቀራረፅ ሌላ አባባል ደግሞ አለ! በገበያ መር ኢኮኖሚ ስም ከሥልጣነ ሕዝብ አሰራር በተቃራኒ የሚሄድ መንግስት ሁሉ ፋሽስት ነው:: ፋሽስቶች ሰላማዊ ሰልፍን አይፈቅዱም:: የሕዝብን ብሶት አያዳምጡም:: በሀገር ሀብት ሎሌ ከበርቴዎችን ያደራጃሉ:: አዳዲሱ መደቦችን ይፈጥራሉ:: በፋሽዝም ደኃ ለጦርነት ይመደባል:: ሀብታም ሥልጣንና ሀብትን ያከፋፍላል:: የባንዳ ልጆች የፋሽስቶችን ተግባር ጠንቅቀው ያውቁታል:: ምጥን ለእናት ማስተማር አይገባም:: የጋርዮሽ ሥርዓት ግን ከፋሽስት አምባገነንነት ይለያል:: የግል ሀብት ማከማቸትን አያበረታታም:: ለወዝአደሩ የበላይነት ይታገላል:: በባሕርይው ፀረ-መደብ ነው:: ለሰፊው ሕዝብ ነፃነት የወዛአደሩን ፊታውራነት ያውጃል:: የጋርዮሽ ሥርዓተ ማህበር እሳቤ::

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አዝማች! አዝማች! አዝማች! አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰባብሮ ቀረ እንደ ጃፓን ስኒ::

ሞሶሎኒ እ.ኤ.አ. በ1915 ዓ.ም. ኢጣሊያ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጋር የጦር ትብብር ስምምነት ስትፈርም ወታደርነት ተቀጠረ:: ቀደም ሲል ግን በጋዜጠኛነት ሙያ ተሰማርቶ ነበር:: በጦርነቱ ግን ብዙም አልቀናውም:: እ.ኤ.አ. በ1917 ዓ.ም. ከጀርመኖች በተተኰሰ ጥይት ክፉኛ ቆስሎ ሆስፒታል ገባ:: ድኖ መውጣቱ አልቀረም:: ነገር ግን የአካለ ጎደሎነት ካሣ አልተሰጠውም:: በዚህ ምክንያት የግድ ሥራ አጥ መሆን ነበረበት:: ሆኖም ብዙ ሳይቆይ ወደ ጋዜጠኝነት ሥራው ተመለሰ::

አንድ ቀን ሞሶሎኒን ለመግደል ቦምብ ተወርውሮ ነበር:: በቦምቡ አሥራ ሰባት ሰዎች ሲገደሉ እሱ ግን ምንም ሳይሆን ተርፏል:: የፋሽስት ፓርቲ እየበረታ ሄደ:: በዚህን ጊዜ ሞሶሎኒ ለኢጣሊያ ንጉሥ ለቬክቶር አማኑኤል 3ኛ የበላይነቱን በመግለፅ ደብዳቤ ጻፈ:: እ.ኤ.አ. በ1923 ዓ.ም የግሪክ አልባኒያን ጠረፍ ፋሽስቶች ወረሩ:: በዚህን ጊዜ የሞሶሎኒ ስም ገነነ:: እንዲሁም ፋሽስቶች ከግሪክ ውስን ቦታዎችን ያዙ:: ኢትዮጵያንም እ.ኤ.አ በ1935 ዓ.ም ወረሩ::

በቤኒቶ ሞሶሎኒ የተመራው የኢጣሊያ መንግሥት እ.ኤ.አ. ሰኔ 10 ቀን 1940 ዓ.ም. በብሪታኒያና በፈረንሣይ ላይ ጦርነት አወጀ:: በዚህም ከጀርመን ጎን መቆሙ በግልፅ ታወቀ:: ጦርነቱ ቀጠለ:: እ.ኤ.አ. ከ1943 ዓ.ም አንስቶ ግን ፀረ-ፋሽስት ኃይላት እየበረቱ መጡ:: ሞሶሎኒ ወደ ስዊዘርላንድ ሲሸሽ ተያዘ:: ሬሣው በሚላኖ ከተማ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቁልቁል ተደፍቶ ተሰቀለ:: ሕፃናትም ጭምር ተኩስ ተለማመዱበት:: በነገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ አዲግራት ላይ ተተክሎ ለአምስት ዓመት ሙሉ እንደ ታቦት የተመለከበት የሞሶሎኒ ሐውልት ማን ወሰደው?

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አዝማች! አዝማች! አዝማች! አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰሰባብሮ ቀረ እንደ ጃፓን ስኒ::

አምባገነኖች ከታሪክ ተምረው አያውቁም:: አንገተ ደንዳኖች ናቸው:: ሕዝብን ይንቃሉ:: ጠብመንጃን ያመልካሉ:: በመጨረሻም በጠብመንጃ ይጠፋሉ:: ታሪክ ራሱን ይደግማል:: እንደገናም አምባገነን ይመጣል:: በውርደት ከትቢያ ጋር ይዋሓዳል:: የታሪክ ዑደት በታሪክ ይቀጥላል::

አንዳንዶቻችን በየቤታችን የፎቶግራፍ አልበም ሊኖረን ይችላል:: የገዥዎቻችን የፎቶግራፍ አልበም ግን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መሆኑን አትጡ! ሎሌዎቻቸውም በዚህ ቴሌቪዥን ውስጥ የመንቀሳቀስ መብት አግኝተዋል:: ይህ የቴሌቪዥን አልበም ብሶት ለሚናገር ሰው የባህል አይነኬ ሆኗል:: ያም ሆነ ይህ በዚህ አልበም ውስጥ ሁሉም ነገር ሞልቷል:: እህል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ተርፎ ወደ ቀይ ባሕርና ሕንድ ውቅያኖስ ይደፋል እንዳይባል ተሰግቷል:: የሕግ የበላይነትም ወደ ሰማየ ሰማያት እንዳሻቀበ ተነግሯል:: ፍትሕ ሰፍኗል:: መልካም አስተዳደር ነግሷል:: ከምግብ ለሥራ ጋዜጠኞች ሰምተናል:: ውሻ በበላበት ይጮኻል:: ካድሬ መለከት ይነፋል::

በገሐዱ ምድር ላይ ያለው እውነታ ግን በጣም ይለያል:: በኢትዮጵያ ምድር ጥቂት ከበርቴዎች በሀብት እጅግ መጥቀዋል:: ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን መኖርን ሳይሆን መሞትን መመኘት ጀምሯል:: ነባራዊ ሁኔታዎች ተሟልተዋል:: ሕሊናዊ ሁኔታዎች ጨርሶ ጠፍተዋል:: አረረም መረረ መፍትሔው ትግል ነው! የሞራል ትንሣኤ የግድ ይላል!

አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አንድ! ሁለት! አዝማች! አዝማች! አዝማች! አወይ ሞሶሎኒ አወይ ሞሶሎኒ፤ ተሰባብሮ ቀረ እንደ ጃፓን ስኒ::

## አዲስ የ‹‹ዴሞክራሲያችን››...

ከገፅ 2 የዞረ

ጠቅላይ ሚኒስትር ረፊቅ ሐሪሪ እስከማስገደል ድረስ ደርሷል:: ዩናይትድ ኔሽንስ በወቅቱ ያወጣው ሪፖርት ሁለት በአሕባሽ ቡድን አመራር ውስጥ ያሉ ግለሰቦች በግድያው መሳተፋቸውን መግለጹም ይታወሳል::

በተጨማሪም ቡድኑ ከየት እንደሚያመጣው የማይታወቅ ከፍተኛ በጀት ያለው ሲሆን ዓላማውን ማስፈጸሚያ አድርጎ ሲጠቀመው ቆይቷል:: ‹‹ዳር አል መሻሪዕ›› የተሰኘ የጎትመት ድርጅታቸው ብቻ ዓመታዊ በጀቱ 3.2 ቢሊዮን ዶላር (ቢሊዮን ነው ያልኩት) መሆኑን በርካታ ድረ ገጾች ይገልጻሉ:: ይህን ያህል ገንዘብ ከአባላት መዋጮ መሰብሰብ መቼም የማይታሰብ መሆኑ ግልጽ ነው::

በ 2008 ሊባኖስ ውስጥ የአሕባሽ አባላት ‹‹ቡርጅ አቢ ሐይደር›› በተባለው ቦታ በመኪና ማቆሚያ ባስነሱት ውዝግብ ከፍተኛ የተኩስ ልውውጥ ከሂዝቦላ አባላት ጋር ተደርጓል:: የሄዝቦላውን የአመራር አባል አሕመድ ፋዋዝ ጨምሮ ዐራት ያህል ሰዎች በተገደሉበት በዚህ የተኩስ ልውውጥ ከፍተኛ ንብረት ወድሟል:: በተኩስ ልውውጡ ከተስፈንጣሪ ቦምቦች እስከ ከባድ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ውለው ነበር:: እስቲ ልብ እንበል! የአንድ ‹‹ሰላማዊ›› ቡድን አባላት በዚህ መልኩ እስከ አፍንጫቸው ነፍጥ ታጥቀው የሚዞሩትና ‹‹ምናባክ ታፈጣለህ?››ን በመሳሰሉ ጥቃቅን ጸቦች አገር የሚረብሹት ስለምን ይሆን? ይህንን ቡድን ወደኢትዮጵያ ‹‹ኢምፖርት›› ማድረግስ ለዘመናት ሰላማዊ የነበሩትን ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን ‹‹ሚሊታንት›› (ጦረኛ) ለማድረግ ይሆን ዓላማው?

ፕሮፌሰሩ ‹‹አሕባሾች ሰላማዊ ናቸው›› ብለው ማሰባቸው ስህተት መሆኑን ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች እንደሚረዱ እገምታለሁ::

ጥያቄው የአወሊያ ት/ቤት ጉዳይ አይደለም!

ፕሮፌሰሩ አወሊያ ት/ቤትን ዋነኛ የግጭት ምንጭ አድርገው መጥቀሳቸው ሌላው መታረም ያለበት ነጥብ ነው:: ካለፈው ዓመት ሐምሌ ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው የአሕባሽ ወከባ ገና ከጅምሩ ተቃውሞ ሲያስነሳ ቆይቷል:: የተቃወሙ ወገኖችም እስርና ወከባ ሲደርስባቸው ቆይቷል:: ዋነኛ የወከባው ጋሻጃግሬ የኢትዮጵያ (የአዲስ አበባ እና የክልል ጭምር) እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት (መጅሊስ) ነው:: ላያችን ላይ ያለምንም ሕዝባዊ ምርጫ በጓሮ መጥተው የተቀመጡብን የመጅሊስ ሹሞች ቁልጭ ያሉ ‹‹ካድሬዎች›› መሆናቸውን እኔም ሆንኩ በርካታ ሙስሊሞች እናምናለን:: የገዥው ፓርቲ ሥውር ተጽእኖ በተቋሙ ውስጥ እንደሚገኝ መታመኑንም ‹‹የሙስሊሞች ጉዳይ መጽሔት›› በመጋቢት 2003 እትሟ በስፋት አውስታ ነበር::

ይኸው መጅሊስ ታዲያ አሕባሽን በተቃወሙ ላይ የማሳሰር እርምጃ በመውሰድ ተቃዋሚዎቹን ሲያዋክብ ቆይቶ ነበር:: በዚሁ ግርግር አወሊያ የሚባለውን ት/ቤት ‹‹ወርሶ›› አስተማሪዎቹን ማባረሩ የቅርብ ጊዜ ክስተት ሲሆን ዓላማውም ት/ቤቱን ዋነኛ የአስተሳሰቡ ማስረጫ ማዕከል ማድረግ ነበር:: ይህን ያልወደዱት ተማሪዎች ተቃውሞ ጀምረው ጥያቄዎቻቸውን በሰላማዊ መንገድ አቅርበው ነበር:: ኋላ ላይ ግን ለዓመታት ሲብሰለሰል የቆየው ‹‹የሃይማኖት ተቋማችን በካድሬ መመራቱ ይቁም!›› የሚል ጥያቄ ከሕዝቡ ወጥቶ አሁን ጥያቄው ‹‹ራሳችን የመረጥናቸው መሪዎች ወደሥልጣን ይምጡልን!›› ሆኗል::

አሁን ጉዳዩ የአንድ ት/ቤት ጉዳይ አይደለም! ጉዳዩ የመሪ ድርጅት ጥያቄ ነው! የፍትሕ ጥያቄ ነው! ለዝርዝር መረጃዎች የጥር 25 የ‹‹ፍትሕ ጋዜጣ›› እትም ላይ የወጣውን የዩሱፍ ጌታቸውን ጽሑፍ እንዲያነቡ እጋብዛለሁ::

ሊያስውጡን ታገሉ እንጂ አልዋጥናቸውም!

ክቡር ፕሮፌሰሩ በጽሑፋቸው የአሕባሽ አማኞች ድምጽ ብዙም የማይሰማ መሆኑን ካወሱ በኋላ ‹‹ባለመኖራቸው ነው ወይስ በኃይል ተዳፍነው ነው?›› የሚል ጥያቄ አንስተዋል:: ይህንን ጥያቄ መመለሱ መደምደሚያዬ ይሆናል::

በመሠረቱ የአሕባሽ አማኞች እጅግ አናሳ (በመቶዎች የሚቆጠሩ) ቢሆኑም በአገራችን ብዙ ዓመታት ማንም ሳይነካቸው፣ ማንንም ሳይነኩ ኖረዋል:: ሕገ-መንግሥቱ የትኛውም ሰው የትኛውንም ሃይማኖት መርጦ መከተል መብቱ መሆኑን ያስቀመጠ ሲሆን የአሕባሽ አማኞችም የዚሁ መብት ተቋዳሽ ሆነው ቆይተዋል:: 3 ቁጥር ማዞሪያ (ቶታል) አካባቢ የራሳቸው የትምህርት ማዕከል ነበራቸው፤ አላቸውም:: ለዓመታት በርካታ ሰዎችን እያሠለጠኑ ሲቆዩ ማንም የተቀናቀናቸው፣ የዋጣቸው አልነበረም! አሁንም አልተዋጡም!

አሁን ችግሩ የተፈጠረው እኒህ የሚጎረብጡ አስተምህሮዎችን የሚያራምዱ ፀጉረ ልውጦች ለዘመናት የኖርንባቸውን መስጊዶቻችንንና መድሳዎቻችንን በመጅሊስ ድጋፍ በጉልበት እየቀሙን በመሆናቸው ነው:: የመስጊድ ኢማሞቻችንን በ‹‹ካድሬው›› መጅሊስ አማካኝነት በግድ እያባረሩ አሕባሽ ኢማሞችን መሾማቸው ነው ችግሩ:: ይህ ደግሞ መብታቸው አይደለም!!! ቢፈልጉ የራሳቸውን ተቋማትና ቤተ አምልኮዎች ይገንቡ እንጂ የሰውን መቀማት አይችሉም!!! የሕዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞም ከዚህና ከዚህ ብቻ የመነጨ ነው - ሌላ አይደለም!!!

አንዳንድ የመንግሥት አካላትና ሁሉም የመጅሊሱ አካላት በግድ እየጫኑብን ያለው የአሕባሽ አስተሳሰብ በጉድፍ የተሞላና ዓለማቀፍ ሙስሊም ሊቃውንት ያወገዙት ቢሆንም ‹‹መልከ ጥፉን በሥም ይደግፉ›› እንዲሉ ድጋፍ ለማሰባሰብ የሐሰት ምክንያቶችን እየሰጡ ይገኛሉ - ‹‹ይህንን የምናደርገው ወሐቢያ የሚባለውን ቡድን ለማጥፋት ነው›› የሚል:: ይህ ፍጹም ሐሰት ነው! መጀመሪያውኑ ‹‹ወሐቢያ›› ለሚለው ቃል የሰጡት ተግባራዊ ትርጉም “Non-Ahbash” (አሕባሽ ያልሆነ) የሚል ሆኖ ነው የምናገኘው:: የተቃወማቸውንና ‹‹መንግሥት ሆይ! ስለምን በሃይማኖቴ ጣልቃ ትገባብኛለህ?›› ያለውን ሁሉ በእስር ቤት እያሳጎሩና መስጊድና መድረሳዎችን እያሳሸጉ ነው ያሉት! ጠያቂ የሌለ በሚመስል አኳኋን የፈለጉትን እያዋከቡ ነው:: መስጊድ ውስጥ ለሚካሄድ ፕሮግራም ማስታወቂያ መለጠፍ እንኳ በ‹‹አሸባሪነት›› እያስጠረጠረ ብዙ ወንድሞች እየታሰሩ ነው:: አሕባሽን የተቃወሙ ወጣቶች ሁሉ እንደዘመነ ደርግ በመጅሊስ አባላት ጥቆማ ማዕከላዊ እየተወሰዱ የሥነ-ልቦና ጦርነት ሰለባ ሆነዋል:: እርግጥ 15 ቀን አስረው ሰውየውን ይለቁታል - ፍርሃትና ሥጋት ከለቀቁበት በኋላ!

‹‹የማደርገውን ነገር ሁሉ በደምብ አስጠንቼ እንጂ በዘፈቀደ አይደለም›› የሚለን ኢሕአዴግ ያስጠናውን ነገር ውጤት በተግባር እያየነው ነው:: ይኸው ሐምሌ ከመጣ ጀምሮ ውክቢያ፣ እስር፣ ማስፈራራት፣ ተቃውሞና ብጥብጥ እንጂ ለሙስሊሞች ምንም አልተረፈንም:: በተለይ በየክፍለ አገሩ በርካታ ሙስሊሞች በደላቸውን እያሰሙ ነው የሚገኙት:: በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የፔቲሽን ፊርማዎች የመንግሥትን ደጃፍ ሲረግጡ ሰንብተዋል:: ሰዎች ሲዋከቡና በተደጋጋሚ ጥቃት ሥር እንደሆኑ ሲያስቡ ደግሞ በርጋጋ ይሆናሉ:: ጽንፈኝነት መግቢያ በር ያገኛል:: ይህ ጥሩ አይደለም - ለሕዝብ - ከዚያም ለመንግሥት!

በሰዎች መካከል ብጥብጥ መስፈኑ የሕገ አራዊት ሥርዓት ነው:: ምናልባት ‹‹መንግሥታት በ‹ሽማግሌነት› ተበጣባጮችን እየዳኙ ዕድሜያቸውን ማርዘማቸው ጥሩ ነው›› ካላልን በስተቀር ጥሩ አይደለም!

እባካችሁ አቁሙልን! ሃይማኖት በግድ አይሆንም! ምሁራንና ጋዜጠኞችም ዝም አትበሉ! ምከሩ፣ ዝከሩ! የእኛ ችግር የእናንተም ችግር ነውና!!! አበቃሁ!

# በጎንደር ከተማ ሁለት የአብነት ት/ቤቶች ሙሉ በሙሉ ተቃጠሉ

## - አንዱ ቤተ ጉባኤ በኢትዮጵያ ብቸኛው የመጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ ማኼጃ ነበር ተብሏል

በሰሜን ጎንደር ሀ/ስብከት ጎንደር ከተማ በሳምንት ልዩነት በሁለት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያን በተነሡ የእሳት ቃጠሎ አደጋዎች አንድ ጥንታዊ የመጻሕፍት ትርጓሜ ቤት ሌላ የቅኔ ቤተ ጉባኤ ሙሉ በሙሉ ወደሙ፡፡

በጎንደር ከተማ የሚገኘው የሐመረ ኖኅ ሠለስቱ ምእት መጻሕፍተ መነኮሳት ትርጓሜ ት/ቤት ሙሉ በሙሉ የወደመው ከትላንት በስቲያ፣ ከየካቲት 6 ቀን 2004 ዓ.ም ከቀኑ 11፡30 ላይ መንሥኤው ባልታወቀ አኳኋን በተነሣ የእሳት ቃጠሎ መሆኑን ደቀ መዛሙርቱ ለፍትሕ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ተናግረዋል፡፡ የትርጓሜ ት/ቤቱ በኢትዮጵያ ከአራቱ ጉባኤያት አንዱ የሆነውን መጻሕፍተ መነኮሳትን ብቻ የሚያሄድ ብቸኛ ቤተ ጉባኤ እንደነበር ተገልጧል፡፡

‹‹እሳት አላያያዝንም፤ ከኤሌክትሪክ መስመር ጋራ የተገናኘ ችግርም አላየንም፤›› ያሉት ደቀ መዛሙርቱ በእሳት ቃጠሎው የተማሪዎች ማደሪያዎች እና የመምህሩ መኖሪያ የነበሩ በአጠቃላይ ዘጠኝ ክፍሎች በውስጣቸው ከሚገኙ በ1714 ዓ.ም ከተጻፉ የብራና መጻሕፍተ መነኮሳት(ማር ይሥሐቅ፣ ፊልክስዩስ፣ አረጋዊ መንፈሳዊ) እና ሌሎች የኅትመት መጻሕፍት ጋራ ጨርሶ መቃጠላቸውን አስረድተዋል፡፡ እሳቱን ለማጥፋት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የእሳት አደጋ መከላከል መኪኖች እና የከተማው ምእመናን የተረባረቡ ቢሆንም ጉዳቱን ለመቆጣጠር የተቻለው ወደ ሌሎች አካባቢዎች እንዳይዛመት በማድረግ ብቻ ነበር፡፡

የመጻሕፍተ መነኮሳት ቤተ ጉባኤው በጠቅላይ ቤተ ክህነት እና በማኅበረ ቅዱሳን በጀት የተተከለላቸው በአጠቃላይ 15 መደበኛ ደቀ መዛሙርት እና ከከተማው አድባራት እየመጡ ትምህርቱን በግላቸው የሚከታተሉ በርካታ ተማሪዎች እንደነበሩት ደቀ መዛሙርቱ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በዚያው በጎንደር ከተማ የደብረ ብርሃን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውና በዐፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት(17ኛው መ.ክ.ዘ) በኖሩት የቅኔ ሊቅ መምህር ክፍለ ዮሐንስ የተመሠረተው የገለአድ የቅኔ ቤተ ጉባኤ የካቲት ሁለት ቀን 2004 ዓ.ም በደረሰበት የእሳት ቃጠሎ ሙሉ በሙሉ መውደሙ ተገልጾአል፡፡

በዕለቱ ከቀትር በኋላ ከተማሪዎች ጎጆ የተቀሰቀሰው የእሳት ቃጠሎው መንሥኤ ለጊዜው ያልታወቀ ቢሆንም ተማሪዎች ወደ መኖሪያ ቤታቸው የገባውን ጉንዳን ለማራቅ የተጠቀሙበት እሳት እንደሆነ ተገምቷል፡፡ በቃጠሎው 26 የቅኔ ደቀ መዛሙርቱ መኖሪያዎች የሆኑ ጎጆ ቤቶች በውስጣቸው ከሚገኙ የተማሪዎቹ አልባሳት፣ መጻሕፍት እና ጥሬ ብሮች ጋራ መውደማቸውን የዜናው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ተናግረዋል፡ ፡

# ‹‹ገዢው ፓርቲ ከህግ በላይ ሆኗል››

## ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ሉአላዊነት ፓርቲ

የመድረክ አባል ፓርቲ የሆነው ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ሉአላዊነት /ዓረና/ ከጥር 26 እስከ ጥር 28 ቀን 2004 ዓ.ም. ድረስ በመቀሌ ከተማ ባደረገው መደበኛው ስብሰባ በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጉን ፓርቲው ለፍትህ በላከው መግለጫ አሳውቋል፡፡

በጠቅላላ ሀገሪቱ ድህነት እየተንሰራፋ፣ ረሃብ እየተስፋፋና እየተባባሰ ሄዷል የሚለው ዓረና የዚህ ችግር ምንጭ መንግስት ከኢኮኖሚው ስርዓት ህግጋት ባፈነገጠ መልኩ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት በመፈፀሙ ነው የሚለው የፓርቲው መግለጫ ገንዘብ በብዛት አትሞ በገበያ በመረጨቱ እና ገበያው በቻይና ምርቶች በመጥለቅለቁ የተከሰተ ነው ሲል ገዢውን ፓርቲ ከስሷል፡፡

በቅርቡ የወጣውን የሊዝ አዋጅም አስመልክቶ የከተማን ቦታ በሊዝ ብቻ እንዲያዝ የሚደነግገው አዋጅ መሬት የመንግስት እና የህዝብ ነው የሚለውን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ለጥጦ በመውሰድ መንግስት ማለት ህዝብ ነው በሚል ትርጉም የዜጐችን ንብረት እና ሃብት የማፍራት መብት የሚነጥቅ አዋጅ ነው ሲል ዓረና ይገልጻል፡፡

ኢህአዴግ ይህንን አዋጅ ከማወጁ አስቀድሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ቤቶችን አፍርሷል የሚለው መግለጫው በተለይም በመቀሌ እና አካባቢዋ ገፉህ ገረብና ደብሪ በተባሉ ስፍራዎች የፀጥታ ሃይሎችን እና ከባድ ማሽነሪዎችን በማሰማራት በሺዎች የሚቆጠሩ ቤቶችን ከማፍረሱ ባሻገር መብታችን ይከበር በማለት ሰልፍ የወጡትን ዜጎች በአስለቃሽ ጋዝ እና በጥይት መበታተኑን ይገልጻል፡፡ ይህ ሁኔታም ገዢው ፓርቲ ከህግ በላይ መሆኑን ያሳያል ሲል በመግለጫው ይከስሳል፡፡

የገዢውን ፓርቲ አካሄድ ከዴሞክራሲያዊ መርህ ያፈነገጠ ፣ የመልካም አስተዳደር መርሆዎች ፀር የሆነ፣ ሙያዊ ነፃነትን የሚያጠፋ፣ በገዛ አገር እንደ ባዕድ ተቆጥሮ ተሸማቅቆ መኖርን ያስከተለ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ ሊቃወመው ይገባል ሲል ጥሪ አቅርቧል፡፡ የዓረና ፓርቲ በዚህ መግለጫው ገዢው ፓርቲ በሰባት ነጥቦች ዙሪያ መልካም እርምጃዎችን እንዲወስድ ሲጠይቅ የትግራይ ህዝብም ለሰብዓዊ መብቶቹ መከበር ከፓርቲው ጋር ሆኖ በፅናት እንዲታገል ጥሪውን አቅርቧል፡፡

# ዴርቶጋዳ የእንግሊዘኛው ትርጉም ነገ በፑሽኪን አዳራሽ ይመረቃል

በዩኒቲ አሳታሚ አማካኝነት ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሞ ባለፈው ሳምንት ለንባብ የበቃው ‹‹ዴርቶጋዳ›› መጽሐፍ ቅዳሜ የካቲት 10 ቀን 2004ዓ.ም ከ10፡30 ጀምሮ በሩሲያ ሳይንስና ባህል ማዕከል በፑሽኪን አዳራሽ የምረቃት ስነ ስርዓት እንደተዘጋጀ አዘጋጆቹ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

በምረቃት ስነ ስርዓቱ ላይ ምሁራን መጽሐፉን በሚመለከት ሂስና ግምገማዎችን የሚያቀርቡ ሲሆን መጽሐፉንም የተመለከተ አጭር ዶክመንተሪ ፊልምም ለዕይታ እንደሚበቃ እና የስነ ጽሑፍ ሰዎችም ግጥሞች እንደሚያቀርቡ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

# የዲ/ን ዳንኤል ክብረት ራእየ ዮሐንስ የዓለም መጨረሻ መጽሐፍ ተመረቀ

የዳ/ን ዳንኤል 18ኛ ስራ የሆነው ‹‹ራእየ ዮሐንስ የዓለም መጨረሻ›› መጽሐፍ የካቲት ሁለት ቀን 2004 በድሬደዋ ከተማ በሚገኘው ትሪያንግል ሆቴል ተመርቋል፡፡

በምረቃ ስነ ስርዓቱ ላይም “The Holy patmos/ በሚል እርስ የፍጥሞ /ፓትሞስ/ ደሴት የሚገኙ 365 አብያተ ክርስቲያናትን የሚያስቃኘው ፊልም ለ30 ደቂቃ ያህል እንዲታይ ተደርጓል፡፡

# ከፍትህ ጋዜጣ - የሀዘን መግለጫ

**የፍትህ ባልደረባ የሆነው አበበ ቶላ (አቤ ቶኪቻው) በታናሽ ወንድሙ ድንገተኛ ሞት ለደረሰበት መሪር ሀዘን የተሰማንን ልባዊ ሀዘን እንገልፃለን**

**ለመላው ቤተሰቦቹም መፅናናትን እንመኛለን**

# የየካቲት 12 ሰማዕታት 75ኛ ዓመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ በዓል ዛሬ ይዘከራል

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም በየካቲት 12/1929 ዓ.ም የጣሊያን ጦር በአዲስ አበባ ነዋሪዎች ላይ ያደረሰውን ጭፍጨፋ አስመልክቶ በብሄራዊ ደረጃ የሚዘከረውን የየካቲት 12 የሰማዕታት ቀን በዓል ምክንያት በማድረግ ዛሬ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ 6ኪሎ ግቢ ውስጥ የ75ኛ አመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ በዓል በተለየ ሁኔታ ይከበራል፡፡

በዚህ ታሪካዊ ዝግጅት ላይ በምርምር ስራቸው አንጋፋ የሆኑ ምሁራን እለቱን የሚዘክሩ የምርምር ጥናቶች ሲያቀርቡ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቴያትሪካል ተማሪዎች የካቲት 12 ቀን እልቂት በተፈፀመበት በተቋሙ ህንፃ ላይ በሚገኘው ሰገነት እና ክፍት ቦታ የበአሉን መንፈስ የሚያጎሉ ተውኔቶችን እንደሚያሳዩ አዘጋጆቹ በተለይ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

የየካቲት 12 የሰማዕታት 75ኛ አመት የአልማዝ ኢዮቤልዩ በዓልን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር አባላት የክብር ልብሳቸውን ለብሰው በፖሊስ ማርሽ በመታጀብ ዝግጅቱን እንደሚያደምቁት እና የተለያዩ በዓሉን የሚመለከቱ የዐውደ ርዕይ ዝግጅቶች እንደሚካሄዱ አዘጋጆቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

# ከደቡብ ክልል 78000ሺ በላይ ህዝብ መሬቱን ለመንግስት አስረክቦ እንዲወጣ መደረጉ ተገለፀ

በደቡብ ክልል በቤንች ማጂ ዞን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች የእርሻና የመኖሪያ መሬታቸውን ለክልሉ መንግስት አስረክበው እንዲወጡ እየተደረገ መሆኑን የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት/መኢአድ/ ገለፀ፡፡

ፓርቲው በተለያየ ጊዜ ከተለያዩ ክልሎች የመጣው ከ78000ሺ በላይ ህዝብ በክልሉ ኑሮውን ለረዥም አመታት የመሰረተ መሆኑን ጠቅሶ በቀጥታ በክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ‹‹ከ1999ዓ.ም ነሀሴ 30 በኋላ የመጡ ማናቸውም ዜጎች ወደመጡበት እንዲሸኙ›› ባለው መሰረት በቤንች ማጂ ዞን በጉራፋርዳ ወረዳ ውስጥ በሚገኙት በአለንግ፣በበርጂ፣ በቢቢታ ወዘተ… ቀበሌ በሚኖሩ ዜጋች ላይ ተግባራዊ እንዲሆን መደረጉን ህዝቡ በከፋ ችግር ውስጥ እንደወደቀ እና ብዙዎችን መታወቂያ በመከልከል ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ በማድረግ፤ተንቀሳቅሰው ሲገኙ በየኬላዎች ላይ ከባድ ድብደባና የገንዘብ ዘረፋ በታጣቂዎች እየደረሰባቸው ነው፤ ‹‹ቀደምት ከነበርኩበት ሀገር ከነቤተሰቦቼ መጥቼ መሬት ይዤ ሳርስ የነበርኩ ስሆን የያዝኩትን መሬት በፍቃዴ መልቀቄን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ›› የሚል ወረቀት ላይ እንዲፈረሙ እየተገደዱ እንደሆነ ፓርቲው ጨምሮ ገልጿል፡፡አያይዞም መንግስት ለህዝቡ ምንም አይነት ተለዋጭ ቦታ እንኳን ሳይሰጣቸው በመሬቱ ላይ ለተከሉት ተክል፣ላፈሩት ሀብትና ንብረት እንኳን ግምት ሳያገኙ ከክልሉ እንዲወጡ ከማድረግ ተግባሩ እንዲታቀብ መኢአድ ጠይቋል፡፡

# የሙዚቃ እና የፊልም ሲዲዎች የሚያከፋፍሉ 50 ሱቆች ሊፈርሱ ነው

በጎጃም በረንዳ አካባቢ አንድ መጋዘን ተከራይተው ለ50 በመከፋፈል ሱቆችን በመክፈት ስራ ብንጀምርም የሱቆቹ ግንባታ ፍቃድ የለውም በሚል በሶስት ቀናት እንዲፈርስ የካቲት 6 ደብዳቤ ደርሶናል ሲሉ ቅሬታቸውን ባለንብረቶቹ በተለይ ለፍትህ ገለፁ፡፡

ከአቶ ኤፍሬም ይርጋ የተከራየነውን መጋዘን አድሰን ለ50 በመክፈል የአመት የቤት ኪራይ ከነቫቱ ከፍለን ሱቆችንም በማደስ ስራ ብንጀምር ያደስነውን የቤት ኪራይ የከፈልንበት ሱቅ ከአንድ ወር በላይ ሳንጠቀምበት ግንባታው ህገወጥ ነው ብለው ሱቆቻችን ለሁለት ወራት በማሸግ ውስጥ የነበሩት ንብረቶቻችን ጊዜያቸው እንዲያልፍበት እና እኛም ለኪሳራ እንድንዳረግ ተደርገናል ያሉት ባለንብረቶቹ ለሚመለከተው አካልም አቤቱታችንን ብናሰማም መፍትሄ ማግኘት ሳንችል በሶስት ቀናት ለቀን እንድንሄድ ተገደናል ብለዋል፡፡

የወረዳ 7 ስራ አስኪያጅ እንዳሉት በ3 ቀን እንዲያፈርሱ ተወስኗል፡፡ ግንባታው ህገወጥ ከመሆኑ ሌላ ባለንብረቶቹ በቂ ሰነድ አልነበራቸውም ብለዋል፡፡ በአካባቢ ማስተር ፕላን መሰረትም በአካባቢ መካሄድ ያለበት ግንባታ ከG+3-G+8 መሆኑን ተናግረው አሁን እየተጠቀሙበት ያለው ቦታ ማስተር ፕላኑ ከሚፈቅደው ውጪ የተገነባ በመሆኑ እንዲፈርስ ካቢኔው ወስኗል ብለዋል፡፡

ባለንብረቶቹም እንዳሉት ከ90% በመቶ በላይ የአገሪቷን የሙዚቃ ኢንዱስትሪ እዚሁ አካባቢ እንደሚንቀሳቀስ ተናግረው ችግሩ ሱቆቹ ከፈረሱ ግን ሁሉም ስለሚበታተኑ ህገወጥ ቅጂዎች እንደሚስፋፉ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡ የሚመለከተው አካል መፍትሄ እንዲሰጣቸው ባለንብረቶቹ ጠይቀዋል፡፡

# የአቤ ቶኪቻው ... ከገፅ 1 የዞረ

... ከገፅ 1 የዞረ

አካባቢ ለብቻው ተከራይቶ መኖር የጀመረ እንደነበረ ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

እስከአሁን ድረስ ባልታወቀ ምክንያት በአንድ ሆቴል ውስጥ ሞቶ የተገኘ ሲሆን የአዲስ አበባ ፖሊስ አባዲና ክፍል ሬሳውን ከሆቴሉ አውጥቶ ስለአሟሟቱ ለማረጋገጥ ዳግማዊ ሚኒልክ ሆስፒታል ከላከው በኋላ፤ ማንነቷ ያልታወቀች ሴት ለቤተሰቡ ደውላ ሬሳው ሚኒሊክ ሆስፒታል እንደሚገኝ መጠቆሟን ምንጮቻችንም ገልፀዋል፡፡

የፍትህ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስለአሟሟቱ ለማረጋገጥ በአዲስ አበባ ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ክፍል ለተደጋጋሚ ጊዜ ያደረገው ሙከራ፤ ምክትል ኮሚሽነሩን አነጋግሩ፣ ኮማንደር እከሌን አነጋግሩ በሚል ምክንያት መረጃ ለማግኘት ሳይችል ቀርቶአል፡፡

የወጣት ወንደሰንም የቀብር ስርአት ማክሰኞ የካቲት 8 ቀን 2004ዓ.ም ሽሮ ሜዳ በሚገኘው ስላሴ ቤተክርስቲያን ወዳጅ ዘመድ በተገኘበት ተፈፅሟል፡፡

# ይድረስ ለፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ

## ከአቶ ዳኛቸው ይልማ

## ከአሜሪካን ሀገር

ባለፈው ሳምን ለንባብ በበቃው የጋዜጣው እትም በስደት ከአገር ውጭ መሆኔ ተገልጿል:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ጋዜጣውን ያነበቡ ሰዎች እኔና ዶ/ር ፍስሀ በተመሳሳይ ምክንያት ከአገር እንደወጣንና አሁንም እርሳቸው ባቋቋሙት የሽግግር ምክር ቤት ውስጥ እንደምሳተፍ የራሳቸውን ግምት አሳድረዋል::

በመሆኑም እኔና ዶ/ር ፍስሀ በተመሳሳይ ምክንያት ከሀገር አለመውጣታችን፣ እርሳቸው አቋቋሙት በተባለው ምክር ቤትም ሆነ በማናቸውም ሌላ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ የሌለኝ መሆኑን የሚመለከታቸው ወገኖች ሁሉ እንዲያውቁ እንድታደርጉልኝ በማክበር እገልጻለሁ::

በተያያዘ ዜና የማይክሮሊንግ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቶ ዳኛቸው ይልማ ከመስራቾቹ አንዱ ባለቤት እንጂ ብቸኛ ባለቤት አይደሉም፤ ስራ አስኪያጅ እንጂ ፕሬዝዳንትም አይደለም ሲሉ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡ ኮሌጁ ለፍትህ ጋዜጣ በላከው ማስተባበያ አቶ ዳኛቸው በፈፀሙት ከፍተኛ ጥፋት የኮሌጁ ባለሀብቶች ጠቅላላ ጉባኤ ከኃላፊነታቸው ከማስወገዱ በተጨማሪ ጥፋታቸው በፍ/ቤት ሁለት ፋይሎች መረጋገጡንም በመግለጫቸው ላይ አሳውቀዋል፡ ፡

ጊዜ ለኩሉ

# “ለማን ነው የምንገዛው?” ለመንግሥት ነዋ!

**ጳውሎስ ፈቃዱ**
paulosvictory@yahoo.com

ፍትሕ ጋዜጣን ብዙ ጊዜ አነብባታለሁ፡፡ ማንበብ ብቻም ሳይሆን ቢስ እንዳያያትም እሳሳላታለሁ (“ቢሱ ማነው?” ብሎ የሚጠይቀኝ ይኖር ይሆን?)፡፡ አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ መሳተፌ ነው፡፡

መነሻዬ በጋዜጣዋ የጀርባ ገጽ ላይ በሚወጣው “ጊዜ ለኩሉ” ዐምድ ላይ የካቲት 2 ቀን 2004 ዓ፣ም ላይ የተጻፈው ጽሑፍ ነው፡፡ ስማቸው የማይታወቀው ጸሓፊ “ለማን ነው የምንገዛው?” በሚል ርዕስ ሮሜ 13ን ጠቅሰው ሐሳባቸውን አስነብበዋል፡፡ እንደ ጸሓፊው ከሆነ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል “ተገዙ” የሚለው ለምድራዊ መሪዎች ሳይሆን፣ ለሰማያዊው መንግሥት (ወኪሎች) እንደ ሆነ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ከጠቃቀሷቸው ምክንያቶች አንዱ ጋዳፊ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ለጋዳፊ ዐይነቱ መሪ መገዛት እንዳለብን እንዴት ሊነግረን ይችላል? የሚል ነው ጥያቄአቸው፡፡ እውነቱን ነው፤ ሐሳባቸውን ወድጄዋለሁ፡፡ ሰዎች ለጋዳፊ ዐይነት ጨቋኝና ግፈኛ መሪዎች መገዛት ሳይሆን፣ እምቢ አልገዛም በማለት መነሣት ነው ያለባቸው፡፡

ጥያቄዬ ሐሳባቸው ላይ አይደለም፤ ሐሳባቸውን ሮሜ 13 ላይ መመሥረታቸው ላይ ነው፡፡ ለመሆኑ ሮሜ 13 ለማን እንድንገዛ ነው የሚነግረን? ለመንግሥት አይደለምን? በዚህ ዘመን ብዙ ግፍ ከሚፈጸምባቸው አካላት አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ አንዳንዶች መጽሐፉ ለራሱ መናገር እንደሚችል ባለመቀበል የራሳቸውን ሐሳብ በቅዱሱ መጽሐፍ ሸጉጠው ለማሳለፍ ሲጥሩ ብዙ ይታያል፡፡ ንግግራቸው ከዐውድ ውጭ ተወስዶ ሰዎች ውግዘትና ክስ ሲመሠረትባቸው እየተቃወምን፣ እኛም መልሰን መጽሐፉ የሚናገረውን ከዐውዱ ውጭ የምንተረጉም ከሆነ ተግባራችን ከምንቃወማቸው ሰዎች በምን ተለየ?

መጽሐፍ ቅዱስ ሲተረጐም ዐውዱ ይታያል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፎች፣ በምዕራፎችና በቍጥሮች የተከፋፈለ መጽሐፍ ነው፡፡ ዐውዱን በሚመለከት የቍጥሩ ዐውድ፣ የቍጥሩ ቀዳሚና ተከታይ ቍጥሮች ናቸው፡፡ ከዚያ ሲቀጥልም አንቀጹ ነው፡፡ አንቀጹ አልገልጥ ካለን ደግሞ፣ ምዕራፉን እናያለን፡፡ ምዕራፉ አልገልጥ ካለን ደግሞ መላውን መጽሐፍ (ለዚህ ርዕስ፣ የሮሜ መጽሐፍ)፣ እርሱ በቂ ካልሆነ ደግሞ፣ ኪዳኑን (ለዚህ ርዕስ፣ አዲስ ኪዳን)፣ ኪዳኑ በቂ ካልሆነ ደግሞ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ይኖርብናል፡፡

እስቲ ሮሜ 13፥1-7ን እንመልከት (ቀለል ያለ ትርጒም ነው የምጠቀመው)፤
(1) ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት ሹማምት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው፡፡ (2) ስለዚህ በባለ ሥልጣን ላይ የሚያምፅ በእግዚአብሔር ሥርዐት ላይ ማመፁ ነው፤ ይህን የሚያደርጉትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ያመጣሉ፡፡ (3) ገዦች ክፉ ለሚሠሩ እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና፡፡ ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትፈልጋለህን? እንግዲያስ መልካምን አድርግ፤ እርሱም ያመሰግንሃል፤ (4) እርሱ ለአንተ መልካሙን ለማድረግ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና፡፡ ነገር ግን ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ምክንያቱም ሰይፉን በከንቱ አልታጠቀም፤ ክፉ የሚያደርገውን ለመቅጣት የቍጣ መሣሪያ የሆነ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው፡፡ (5) ስለዚህም ቅጣትን በመፍራት ብቻ ሳይሆን፣ ለኅሊና ሲባል ለባለ ሥልጣን መገዛት ተገቢ ነው፡፡ (6) ግብር የምትከፍሉትም ደግሞ ለዚህ ነው፤ ባለ ሥልጣናቱ፣ በዚህ ተግባር ላይ የተሠማሩ የእግዚአብሔር አገልጋይ ናቸውና፤ (7) ለእያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ፤ ግብር ከሆነ ግብርን፣ ቀረጥ ከሆነም ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ (ሮሜ 13፥1-7 - አ.መ.ት)

እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች ሦስት ተቋማትን መሥርቷል፤ እነዚህም ጋብቻ፣ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ናቸው፡፡ ሆኖም ሰዎች ፍጹማን ባለመሆናቸው እነዚህ ሦስት ተቋማትም ፍጹማን መሆን አልቻሉም፡፡ ከዚህ በመነሣት ግን “ተቋማቱን የመሠረተው እግዚአብሔር አይደለም” ልንል አንችልም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም እንደሚነግረን መንግሥትን የፈጠረው እግዚአብሔር ነውና መንግሥት የሚባል ተቋም እንዳይኖር ማሰብና መሞከር ጤና ማጣት ነው፡፡ ክፉ ባል ወይም ሚስት ያሉበትን ትዳር ስላየን ብቻ ጋብቻን የመሠረው እግዚአብሔር አይደለም ማለት እንችላለን? ታዲያ የጋዳፊ ዐይነት መሪዎች ስላየን ብቻ የእግዚአብሔርን ሿሚነት እንዴት መቃወም ይቻለናል? ባይሆን እግዚአብሔር ሕዝቡን በመልካም እንዲያስተዳድሩ ሾሟቸው፣ ተሿሚዎቹ ኀላፊነታቸውን ማበላሸታቸው ነው መነገር ያለበት፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ለሰዎች ልጆች ነጻ ፈቃድን ሰጥቷልና ያንን ያከብራል፤ እያስገደደ መልካም መሪዎች አያደርጋቸውም፡፡ መልካም መሪ መሆን ሲሹ ያግዛል እንጂ፡፡ መጨረሻም ሒሳባቸውን እንዲያወራርዱ ያደርጋቸዋል፡፡ (ጋዳፊ ላይ የደረሰው እየታሰበ)፡፡

የሮሜ መጽሐፍ ተገዙ የሚለው ለምድራዊ መሪዎች መሆኑ እስከ ዛሬም ለጥያቄ ቀርቦ አያውቅም (በመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘንድ)፡፡ ባይሆን መገዛት ማለት ምን ማለት ነው? ምንስ ማለት አይደለም? ለምን ዐይነት ምድራዊ መሪዎች ነው መገዛት ያለብን? የምንገዛውስ እስከ መቼ ነው? የሚሉ ጥያቄዎች በየወቅቱ ተነሥተዋል፡፡ ለመንግሥት መገዛት እንዳለብን ጥያቄ የማይነሣው ምንባቡ በግልጽ ስለሚያስቀምጠው ነው፡፡ ቢያስፈልግ አዲስ ኪዳን በተጻፈበት ወርጅናሌ ቋንቋ፣ በግሪኩ ምንባቡ ምን እንደሚል በማየት ጥያቄውን በአጭሩ መቋጨት ይቻላል፡፡ ሆኖም ዐውዱን ብቻ በማየትም ሐሳቡን መረዳት እንደሚቻል አስባለሁ፡፡

እርግጥ ነው የሮሜ መጽሐፍ የተጻፈው በሮም ከተማ ላሉት አማኞች ነው፡፡ ሆኖም መልእክቱ በቀጥታ ክርስቲያኖችን ብቻ የሚመለከት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ሌሎቹስ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት የተጻፉት ለማን ነው? በተለይ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሙሉ የተጻፉት ለአማኞች ነው፤ ተፈጻሚነታቸው ግን በክርስቲያኖች ላይ ብቻ አይደለም፡፡

ለምሳሌ በሮሜ 13 ቍጥር 1 ላይ “ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ” ነው የሚለው፡፡ ነፍስ ሁሉ (ማንኛውም ሰው) የሚለው ክርስቲያኖችን ብቻ ነው የሚመለከተው ለማለት እንዴት ይቻላል?

ቍጥር 4 “ሰይፉን በከንቱ አልታጠቀም” ይላል፡፡ ለመሆኑ ሰይፍ የሚታጠቀው ማነው? ምድራዊ መሪ ወይስ የሰማዩ መንግሥት ወኪሎች?

ቍጥር 4 ደግሞ፣ “ግብር የምትከፍሉትም ደግሞ ለዚህ ነው” ይላል፡፡ ግብር የምንከፍለው ለማን ነው? ለመንግሥት ወይስ ለእግዚአብሔር መንግሥት ወኪሎች? ቤተ ክርስቲያን ግብር እንድትሰበስብ አንድም ቦታ አልታዘዘችም፡፡ መብቷም አይደለም!

ቍጥር 7ም “ለእያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ፤ ግብር ከሆነ ግብርን፣ ቀረጥ ከሆነም ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ” ይላል፡፡ ግብርና ቀረጥ ለማን ነው የሚከፈለው? መልሱ ግልጽ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስም ለቄሳር ግብር መክፈል ተገቢ ስለ መሆኑ ተናግሯል፤ ራሱም ግብር ከፍሏል (ማቴ. 17፥24-27)፡፡

ለእነዚህ ጥያቄዎች የምንሰጠው መልስ፣ ለማን መገዛት እንዳለብን ይነግሩናል፡፡ “ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው” ሲል መቼም ስለ እግዚአብሔር ሥልጣን እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ እግዚአብሔር የራሱ ሥልጣን ከየት እንደ ተገኘ እየነገረን ይሆን?

ለመሆኑ ለሃይማኖት መሪዎች መታዘዝና ክብር መስጠት እንጂ መገዛት እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናልን? ለመሆኑ እነዚህ የሰማዩ መንግሥት ወኪሎች ከምድራዊ መንግሥት ወኪሎች የተሻሉ ተደርገው የሚወሰዱት ለምንድን ነው? ከሙስና የጸዱ ስለሆኑ? በሥልጣን ስለማይባልጉ? ሕዝቡን በቅንነት ስለሚያገለግሉ? በጽድቅ ስለሚፈርዱ? እንዲያውም ፈላስፋው ሲ ኤስ ሌዊስ እንደሚለው፣ “ከክፉ ሰዎች ሁሉ፣ የሃይማኖት ክፉ ሰዎች እጅግ ይብሳሉ”፡፡ እኛም እንዳየነው፣ ሰው ባለበት ሁሉ ችግር አለ! የችግሩ ምንጭ የሰዎች ልብ ነውና!

እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ለመንግሥት እንዲገዙ ይፈልጋል፡፡ ለምን? ምክንያቱ በዝርዝር ተቀምጧል፡፡ ሥልጣን ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለሆነ (ቍጥር 1)፣ ገዦች ሕግ አክባሪዎችን ሲሸልሙ ቅጣት የሚሰነዝሩት ደግሞ በሕገ ወጦች ላይ ብቻ እንደ ሆነ ስለሚታሰብ፡፡ ስለዚህም መንግሥትን የሚፈሩት ሕገ ወጦች ብቻ ሊሆኑ ይገባል (ቍጥር 3)፡፡ ስለዚህ ለመንግሥት መገዛት አለብን፡፡

ሮሜ 13 ለምድራዊ መንግሥት ስለ መገዛት ነው የሚናገረው፡፡ አማኞች ለመንግሥት መገዛት አለባቸው፡፡ ክፍሉ ስለዚህ ማውራቱ አከራካሪ ሊሆን አይችልም፤ ሆኖም ተያይዘው የሚነሡ ጥያቄዎች መኖራቸው አይቀርም፡፡ የተወሰኑትን ላንሣቸው፤

1. ለመንግሥት መገዛት መንግሥት የሚባለውን ተቋም መቀበል ማለት ቢሆንስ? ክርስቲያን በየጊዜው ሥልጣኑን የሚይዙትን ጌቶች ሳይሆን፣ መንግሥት የሚባለውን ሥርዐት መቃመም የለበትም፡፡ መንግሥት ከሌለ እንደ ሶማሊያ ነው የሚኮነው፡፡ መንግሥት ከሌለ በሰላም ወጥቶ መግባት፣ ሥራ ሠርቶ ቤተ ሰብን ማስተዳደር፣ ልጆችን ወልዶ ማሳደግ አስቸጋሪ ይሆናል፤ እውነት ነው! ስለዚህ ለመንግሥት ተገዙ ማለት የተቋሙን ሕልውና አትቃወሙ ማለት ብቻ ቢሆንስ?
2. እርግጥ ነው፤ “ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለም” (ቍ. 1)፡፡ ግን ለባለ ሥልጣን ተገዙ ማለት ዐልጋውን የያዘውን ወገን ሲደግፉ መኖር ማለት ነው? ሥልጣን ላይ ያሉት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቈረጠላቸው የሥልጣን ዘመን ሲያበቃስ? ቀጥለው ወደ ሥልጣን ከሚመጡት ጋርስ የእግዚአብሔር ይሁንታ አይኖርም?
3. ለመንግሥት መገዛት (ባለ ሥልጣናትን መታዘዝ) ያለብን በነገር ሁሉ ነውን? ከእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ ጋር የሚጋጭ ነገር ብንታዘዝስ? እንደ ሐዋርያት፣ “ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል” (የሐዋ. 5፥29) ልንል የምንችልበት ሁኔታ የለም? መገዛት የሚያስፈልገውን ያህል የማንገዛባቸው ነገሮችስ አይኖሩም? ይህ ምንባብ መንግሥት ፍትሕን፣ ነጻነትን፣ እኩልነትን፣ የሕግ የበላይነትን ሲጥስ “እምቢ” ከማለት ይከለክላል?
4. “ተገዙለት” የተባለው ባለሥልጣን ክፉ አድራጊዎችን እንጂ መልካም አድራጊዎችን የሚያስፈራ እንዳልሆነ ተገልጿል (ቍ. 3)፡፡ እንዲህ ካልሆነስ? ባለ ሥልጣኑ የራሱን የኀላፊነት ድርሻ ካልተወጣስ? መልካም አድራጊዎችን እየበደለ፣ ክፉ አድራጊዎችን ቢሸልምስ? በቅንነት ለእውነት የሚሠሩ ተበድለውና ተገፍተው፣ ሙሰኞችና አድርባዮች ሲከብሩና ከፍ ከፍ ሲሉ ስናይስ መገዛታችን መቀጠል አለበት? የሂትለር፣ የስታሊን፣ የፖል ፖት፣ የኢዲ አሚንና የጋዳፊ ዐይነት መሪዎችስ እንዴት ሊታዩ ነው? ክርስቲያን ዜጎቻቸው ለእነርሱም በነገር ሁሉ እየተገዙ መኖር አለባቸው? እነዚህን መሪዎች መቃወም ነው ኀጢአት የሚሆነው ወይስ አለመቃወም?
5. ግብር፣ ቀረጥ፣ ክብርና አክብሮት እንደሚጠበቅብን ተነግሯል (ቍ. 6-7)፡፡ መገዛት ማለት ግብር መክፈልና አክብሮት መስጠት ብቻ ቢሆንስ? ይህ መቃወምን ይከለክላል?
6. “ከኅሊና የተነሣ ተገዙ” ማለት ምን ማለት ነው? ክርስቲያኖች የመንግሥት ነገረ ሥራ ከኅሊናቸው ጋር ሲጋጭ ምን ያድርጉ? ከገዛ ኅሊናቸው ጋር እየተጣሉ ለመንግሥት መገዛት አለባቸው?

ስለዚህ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ መሞከር ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ ለመንግሥት መገዛት እንዳለብን እየተናገረ መሆኑን አሌ ማለት አይቻልም፡፡

ግን መገዛት ማለት አለመቃወም ማለት ነው? ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕግ ሰዎች ተቃዋሚ ፓርቲ የማቋቋም፣ መንግሥትን በሕጋዊና ሰላማዊ መንገድ የመቃወም፣ በምርጫ አሸንፎ ሥልጣን የመያዝ መብትን ለዜጎች ይሰጣል፡፡ ታዲያ በዚህ መንገድ መንግሥትን መቃወም አለመገዛት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል? ሰው ክርስቲያን ስለሆነ ብቻ ይህንን መብቱን ያጣል? በጭራሽ! እንዲያውም እንዲህ አታድርጉ በማለት የሚሰብኩ የሃይማኖት ሰዎች ሲገኙ፣ የአገሪቱን ሕግ እየጣሱ በመሆኑ በሕግ ሊጠየቁ ይገባል፡፡ መገዛት ይህን አይከለክልም፡፡ ስለዚህ ለመንግሥት (ለሕግ) እየተገዙ መንግሥትን መቃወም ይቻላል ማለት ነው፡፡

ለዚህ ምስክር ካስፈለገ ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ኪንግ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ነበር፡፡ ነገር ግን ነጻነት ለሰዎች የሰጠውን ነጻነትና እኩልነት የሚከለክሉ ሕግጋትን በመቃወም በሰላማዊ መንገድ ታግሎ አሸንፏል፡፡ ማርቲን ሉተር ለመንግሥት ይገዛ ነበር፤ መንግሥትንም ይቃወም ነበር፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የነጻነትም ሆነ የሥልጣን ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ይናገራል፡፡ ሰዎች ግን ሁለቱንም የክፋት መጠቀሚያ ሊያደርጓቸው ይችላሉ፡፡ ይሄ የሚፈጸመው ባለሥልጣናቱ በጦርነትና በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ስለያዙ ብቻ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ሂትለርና ሙሶሎኒ በሕዝብ ድምፅ በዴሞክራሲያዊ መንገድ መመረጣቸው ይታወቃል፡፡ የተመረጡበት መንገድ ግን ክፉ ከመሆን አላገዳቸውም፡፡ በመፈንቅለ መንግሥትና በጦርነት ሥልጣን ይዘው መልካም መሪዎችም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

እግዚአብሔር ለሰለሞን ሥልጣንና ጥበብን ሰጠው፤ ውጤቱስ? ግብር ቆልሎ ሕዝብ የሚያማርር መሪ ሆነ (1ነገ. 11፥41 - 12፥4)፡፡ የሚስቶቹ ብዛትም እስካሁን ክብረወሰን ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አልሾመውም ልንል ነው? እግዚአብሔር ሳኦልን፣ ኢዮርብአምን ... ሾሟል፡፡ ሁሉም ግን እግዚአብሔርንም ሆነ ሕዝቡን የሚያሳዝኑ ነገሥታት ነበሩ፡፡ ምድራዊ ሥልጣን መቼም ቢሆን እንከን አያጣውም፡፡ ሰማያዊ መንግሥት ያስፈለገውና እግዚአብሔር እንከን የለሽ ልጁን ለሌላ መንግሥት ምሥረታ ወደ ምድር የላከው ለዚህ ነው፡፡

ጸሓፊው እንደ ፈሩት ሳይሆን፣ የአሕዛብንም ነገሥታት እግዚአብሔር ይሾማል፡፡ ለምሳሌ አዛሄል በሶርያ ላይ እንዲነግሥ እግዚአብሔር አዝዞ ነበር (1ነገ. 19፥15)፡፡ ሰውዬው ሲነግሥ ግን የእርጎዞችን ሆድ እንኳን ሳይቀር በሰይፍ የሚቀድ መርገምት ነው የሆነው (2ነገ. 8፥7-15)፡፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠውን ነጻ ፈቃድ ሁሌም ያከብራል፡፡ ሰዎችን እንደየሥራቸው የሚከፍላቸው ለዚህ ነው፡፡

ቂሮስ የአሕዛብ ንጉሥ ነው፤ ነገር ለንግሥና የቀባው እግዚአብሔር ነው (ኢሳ. 45፥1)፣ “እረኛዬ”ም ይለዋል (ኢሳ. 44፥28)፡፡ የባቢሎን ንጉሥ የነበረው ናቡከደነጾርም የእግዚአብሔር አገልጋይ ተብሏል (ኤር. 25፥9፣ 27፥6፣ 43፥10)፡፡ የትኛውም መንግሥት ክፉ አድራጊዎችን እየቀጣ፣ መልካም አድራጊዎችን እንዲሸልም እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ፍትሕና፣ ሰላምንና መልካም አስተዳደርንም ማስፈን አለበት፡፡ በሥልጣን መባለግ የለበትም፡፡ አዎን፣ እንዲህ ከሆነ መንግሥት የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው! አሊያም ሒሳቡን ያወራርዳል - በዚህኛው ሕይወትም ሆነ በዚያኛው ዓለም!

ለማንኛውም የሳምንቱ ጸሓፊ ያነሡት ሐሳብ ደስ ብሎኛል፡፡ ተቃውሞዬ ሐሳባቸውን በሮሜ 13 ማስታከካቸው ላይ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ለራሱ የመናገር መብቱን አንንፈገው፤ ያላለውን እንዲልልን እጁን አንጠምዝዘው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚናገረው ዜጎች ሁሉ (ክርስቲያኖችን ጨምሮ) ለመንግሥት መገዛት አለባቸው፡፡ ግን መገዛት ምን ማለት ነው?

ክብረት ይስጥልኝ!